# አሰሩ ደናግል፡ እና መቶ
# አርባ-አራት ሺዎቹ አይሁዶች

እንዴት አደራችሁ። ዛሬ ጠዋት በጌታ አገልግሎት እዚህ በመገኘቴ ደስ ብሎኛል። ውጭ ላይ መጥፎ የአየር ሁኔታ አለ፡ ውስጥ ግን፡ ኦህ፡ በጣም ጥሩ ነው። ከውስጥ ሆነን ውጪውን እያየን ደስ የሚል ጊዜ ነው ይምንለው አጋጣሚ ይሄ ነው፡ አይደል´ዴ? ከውጭ ሆነን ወደ ውስጥ ማየት።

2 ትናንት ማታ በደንብ አርፌአለሁ እና ዛሬ ጠዋት ጥሩ ስሜት ተሰምቶኛል። እና ትላንት ማታ ጥሩ ጊዜ አሳልፈናል፡ አይደል? እጅግ አስደሳች ጊዜ! ይህንንም አደንቃለሁ። ያን ጊዜ የነበረን... አገልግሎቱ በሼቭሬፖርት ላይ እንደነበረው ይመስላል፡ ከሞላ ጎደል—የመንፈስ መከተል ቀጣይ ሂደት ነበር። ኧሃ-ሃም። በጣም ደስ ብሎናል እግዚአብሔርንም ስለ ቸርነቱ እና ምህረቱ በጣም እናመሰግናለን፡ ስለ እናንተም... እናንተ ሰዎችም እሱ እንዲቀድመን እና እንዲመራን መንፈሳችሁን ለእርሱ ሰጣችሁ።

3 አያችሁ፡ ቅር የሚሰኝ ጉባኤ ከሆነ፡ መንፈስ ቅዱስ እንኳ አይገልጥም። አብሮ የሚያሰራ፡ አንዳች ነገር ሊኖራችሁ ያስፈልጋል። “በአንድ ቦታ እና በአንድ ልብ ነበሩ፡” እነሆም እንደሚናጠቅ ድምጽ ከሰማይ መጣ። አያችሁ፡ እንዲህ ስትሆኑ ግን... በጌታ ፊት ወድቄ፡ ቀንና ሌሊት እያጠናሁ እየጸለይኩ ምንም ያህል ብጸልይ፡ ምናልባትም ቅባቱ በእኔ ላይ ሆኖ፡ ወደዚህ ብመጣ እንኳ፡ ወደዚህ መጥቼም የቅሬታ ነገር ቢሰማኝ፡ አያችሁ፡ እሱን—እሱን... ወዲያውኑ ያሳዝነዋል፡ ምንም ነገር አይገልጥም። በቅባት ስር ሆናችሁ ወደዚህ ስትገቡ እና ጉባኤውም በቅባት ስር ሆኖ ስታገኙት ግን፡ መንፈስ ቅዱስ መስራት ይጀምራል፡ ያኔ ይንቀሳቀሳል ታላላቅ ነገሮችም ሊያደርግልን ይጀምራል። አሁንስ፡ አያችሁ?

4 ያን ጉዳይ ከፓስተር ጋር ገና አልተነጋገርኩም... **እመን ብቻ** ሲሉ ሰምቼ ሮጬ ገባሁ እና ምን እንደነበረ—አየሁት... ለዛሬ ጠዋት አቀናጅቶታል። አሁንም፡ ወንድም ኔቪል፡ እንዲህ ልበልህ፡ በዚህ አነስተኛ ጉባኤ እጀምራለሁ እና እስከ አሰራ አንድ ሰዓት ከጨረሰኩ፡ መልካም፡ ትረከበኛለህ ከዚያም ሰብከት ትጀምራለህ። እንዴት ነው? [ወንድም ኔቪልም መለሰ፡ “ይሁን፡ ቅባቱን አትረብሽ፡ እንዲሁ አንተ ቀጥል።”—አርታዒ።] ኦህ፡ እዚያ ጋር ያለው ቅባት፡ እንዲሁም፡ ይህ ቅባት ያው እንደሆነ አምናለሁ። እሱ´ኮ...

5 ወንድም ኔቪል ሁሌም እንዲህ ነው... ከዚህ በፊት እዚህ መጥታችሁ ለማታውቁ እንግዶች፡ እሱ (በፊቱ መናገር እንዳይሆንብኝ፡ ግን) ደግ ሰው ነው፡ ሁሌም እንዲህ ነው። “እርስ በርሳችሁ ተዋደዱ፡” ሁል ጊዜ በክርስቶስ ሁል ጊዜም **ተከባበሩ**፡ የሚለውን የሚያነበው ቃሉን—ሁል ጊዜ... ይኖረዋል። እና እሱን ካወቅኩት ጊዜ ጀምሮ ሁሌም ያው ነው፡ እዚህ ተበርናሰክል ከመጣ ወዲህ ሳይሆን፡ ካወቅኩት ከብዙ ጊዜ ወዲህ ዘመኑን ሁሉ በዚህ አውቀዋለሁ። ትዝ ይለኛል ለመጀመሪያ ጊዜ ወንድም ኔቪልን ያየሁት፡ እሱን ያወቅኩት፡ አንድ ጊዜ በሜቶዲስት ቤተክርስቲያን እሱ ሲሰብክ

ለመስማት ሄጄ፡ ነበር… በሃዋርድ ፓርክ ውስጥ፡ ከብዙ፡ ብዙ አመታት በፊት ነው። ይመስለኛል፡ ከሃያ ዓመታት በፊት፡ ወይም ከዚያ በላይ የማውቀው (ይመስለኛል)። ያኔ እሱ… እንዲሁ ነበረ፡ እሱም፡ ስራ ይሰራ ነበር፡ እሱ… ኡህ፡ ይመስለኛል፡ እስከ ቅርብ ጊዜ፡ በትውልድ አገሩ፡ በሄንሪቫይል፡ በደን አጠባበቅ እና መሰል ሰራዎች ይሰራ ነበር፡ ለኑሮው ስራ እየሰራ፡ በጎን ሰብከት ይሰብካል። እኔም፡ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ፡ ሕይወቴ እንዲሁ ነበር፡ በኋላ ግን ከዚህ በቀር ሌላ መሰራት የማንችልበት ጊዜ ደረሰን። ስለዚህ ደሰ ብሎኛል። በአዲሱ አለቃችን፡ በወንድም ኔቪል ደስ ብሎኛል፡ እናንተስ? አዎን፡ ወዳጄ! በትክክል ተመችቶኛል። አዎን፡ ወዳጄ። በሱ እጅግ ረክቻለሁ!

6 እና አሁን የሰንበት ትምህርት ክፍሎችን እንደሚቆርጡት አምናለሁ። አዎን። የህጻናት የሰንበት ትምህርት ክፍል፡ በክፍሉ ምክንያት ይቆርጡታል… ፓርቲሽኖቹን ያሰወግዱታል፡ ስለዚህ ቤተክርሰቲያኑ ወደ ኋላ በኩል እንዲሆን ያደርጉታል።

7 አሁን፡ ዛሬ ማታ የዚህ የመጨረሻው ታላቅ ዘመን፡ የሎደቅያ ዘመን እናያለን። ትናንት ማታ የፊላዴልፊያን ዘመን አይተናል እንዲሁም ሁለቱም የሚደራረቡበትን የሎዶቅያ ዘመን ጅማሬም አይተነዋል። ከዚያም በእነዚያ ዘመናት መካከል እግዚአብሔር ለእኛ መግለጥ የጀመራቸውን ታላላቅ ምሥጢራት አይተናቸዋል፡ “የተከፈተው በር፡” “ታናሽ ኃይል፡” እና “ቃሌን ጠብቀሃል፡” “ሰሜን አልካድክም።” እና በዚያ ውስጥ የነበሩ ታናናሽ ነገሮች እንኳ ሳይቀር፡ እግዚአብሔር በመካከላችን በሚደንቅ መንገድ ህያው አድረጋቸው፡ በዚህም ምክንያት እጅግ፡ እጅግ እናመሰግናለን።

8 እና በመካከላችን የታመመ ቤተሰብ የያዙ ሰዎች ካሉ፡ ይህን እንዳትረሱ፡ ከዛሬ አንድ ሳምንት በኋላ፡ በሚቀጥለው እሁድ ለታማሚዎች ጸሎት እናደርጋለን። ጌታ ቢፈቅድ… ያ ይሆናል። ያ ይሆናል… ሁል ጊዜ “ጌታ ቢፈቅድ” ብዬ ነገሮችን እንዴት እንደማሰቀምጣቸው፡ ታሰተውላላችሁን? መፅሃፍ ቅዱስ “ጌታ ቢፈቅድ፡” በሉ ይለናልና። እሰካሁን ገና አላወቅንም፡ አንተ እዚህ ትሆናለህ፡ቤተክርሰትያንም እዚህ ትሆናለች፡ እኛ ሁላችንም እዚህ እንሆናለን፡ ወይም ሌላ ነገር አልነገረኝም። እንግዲህ ፈቃዱ ከሆነ፡ እዚህ እንሆናለን፡ እያችሁ። ፈቃዱ ካልሆነ ግን፡ እዚህ አለመሆናችን፡ የማይቀር ነው።

9 ወንድም ኔቪል እና ሌሎች፡ በሰርጭት ጣብያው ላይ ያለማቋረጥ ያስታውቀዋል፡ ሌላኛው ወንድማችን እና ሌሎች ባለ ሰርጭት ጣብያዎችም ጭምር፡ እንዲሁ ይመስለኛል። እና እሁድ ጠዋት በተቻላችሁ መጠን ቀድማችሁ ግቡ፡ ምክንያቱም የምንጸልይለት ብዛት ያለው ህዝብ እንፈልጋለን፡ መግባትም እንፈልጋለንና። እኛም… እንግዲህ፡… እንዲህ ያለ… ታላቅ ጉባኤ ከተሰበሰበ፡ እሰኪ እናየዋለን፡ ህዝቡ እጅግ ሰለሚበዛ አንዱ በሌላው ላይ ሰለሚረጋገጡ፡ እና መሰል ነገሮችን… ሰለምታበዙ ሁል ጊዜ የጸሎት ካርዶችን ማዘጋጀት ጠቃሚ ነው። በሰርዓት ሰታደርጉት እና አንድ በአንድ እንዲመጡ ከተደረጉ ነገሩን ያስተካክለዋል… ታውቃላችሁ፡ በህዝብ መካከል የሚፈጠረውን ግራ መጋባት ይቀንሳል።

10 እና—እና ደግሞ… ካርዳችሁ እስኪጠራ ድረስ ተነሰታችሁ መቆም አያሰፈልጋችሁም። የታመማችሁ ከሆናችሁ እና መጥፎ ሰሜት እየተሰማችሁ

ከሆነም፡ በረጅም ወረፋ አትቆሙም ባላችሁበት ቁጭ በሉ። ካርዳችሁ ሲጠራ፡ ቶሎ ብላችሁ ኑና ተጸልዮላችሁ ትወርዳላችሁ፡ ሌላውም፡ እንደዚያው ይመጣል። ያን እጅግ ደስ ይለኛል። ብዙ ጊዜ በአንዴ የሚጠሩ ጥቂቶች ስለሆኑ፡ ወረፋ ላይ እያለን ጫን የሚለው ሰው ሲያጋጥም፡ ወንበር በማምጣት የሚያስተናግዱ ወጣቶች አሉ፡ ከባድ ህመም ስለሚሰማቸው፡ በቃ፡ አንድ ነገር እስኪሆን—እዚያው ወንበራቸው ላይ ይጠብቃሉ... ወይም ቁጥራቸው እስኪጠራ ድረስ፡ እስኪጸለይላቸው ድረስ ወንበሩ ላይ ይቀመጣሉ።

11 ከመጽሐፍ ቅዱስ ታላላቅ ትምህርቶች አንዱ ነው፡ በመለኮታዊ ፈውስ አምናለሁ። መለኮታዊ ፈውስ ግን ከመለኮታዊ ፈውስነቱ የበለጠ ነገር አለው። መለኮታዊ ፈውስ "ዳግመኛ የሚመጣ አምላክ አለ" ብቻ ይላል። መለኮታዊ ፈውስ ስለ ምን ይናገራል? የትንሳኤአችን ቀብድ ነው። መለኮታዊ ፈውስ ከሌለ ትንሣኤ የለም፡ አያችሁ። እኛን የሚያጠምቅ መንፈስ ቅዱስ አሁን ከሌለ፡ በመጭው ዓለም የዘላለም ሕይወት አይኖርም። መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር "የመዳናችን ቀብድ ይህ ነው፡" ይለዋልና። **ቀብድ** ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ? "ቅድመ ክፍያ" ነው፡ አያችሁ። ሄዳችሁ ቅድመ ክፍያን ስትፈጽሙ... ለምሳሌ የእርሻ ቦታ ስትገዙ፡ ምናልባት አስር ሺ ዶላር ይጠይቋችኋል እንበል፡ ከዚያ ውስጥ ሁለት ሺ ከከፈላችሁ፡ ያ ለእናንተ የገንዘባችሁ "ቀብድ" ነው፡ የዋናው ቀብድ ይሉታል። እንግዲህ፡ ይህ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በሚመጣው ነገር ላይ ቀብድ ብቻ ከሆነ፡ ኦህ፡ ሙሉ ክፍያ በሚሰጠን ጊዜስ—እንዴት ሊሆን ይሆን? እጅግ ታላቅ ይሆናል!

12 አሁን፡ ዛሬ ጥዋት፡ ጌታ ቢፈቅድ፡ እነዚያን ነገሮች አንዳንዶቹን በእነዚህ ውስጥ ለማስተሳሰር፡ እንሞክራለን... በቤተክርስቲያኑ ዘመናት መካከል (እነዚህ **እዚህ** ውስጥ) ውስጣቸው የሆነ ነገር አለ። **መቶ አርባ-አራት ሺዎቹ፡ ቅሪት፡ ሰነፎቹ ደናግል፡ ልባሞቹ ደናግል፡** እና **የመንፈስ ቅዱስ ማሕተም፡ የአውሬው ምልክት መደረግ፡** እነዚህ ሁሉ ነገሮች... ይህ የዘመኑ መጨረሻ ስለሆነ፡ ሁሉም ነገር እዚህ አንድ ቦታ ላይ ይወድቃል፡ እንግዲያስ ይህን ለማውጣት የክረምቱን የዕረፍት በሙሉ ጊዜውን ልንጠቀመው ይገባል፡ እኛም... የራዕይ መጽሐፍን ለመረዳት፡ እንዴት አንድ ላይ እንደሚተሳሰር ተመልከቱ።

13 ሚስተር ዉድ፡ ስልጣኔ በተመሳሳይ መንገድ ጉዞ አድርጓል። ይሄን አስተውላችሁ ታውቃላችሁ? ነገሩ እንዲህ ነው... ይህም፡ ሰው የራሱ ስሜት አለው፡ ስድስት ስሜቶች አሉት፡ ወይም፡ አምስት ስሜቶች አሉት፡ ይህም ከዚያ ጊዜ ጀምሮ—ወደ ምድር ከመጣ ከስድስት ሺህ ዓመታት ጀምሮ ነው። አሁን ግን ባለፉት፡ ባለፉት ጥቂት፡ መቶ ዓመታት ውስጥ... ይገርማል! በበሬ ጋሪ ቀስ ብሎ እያዘገመ፡ መጣና፡ በዚያ ደረሰ። ነገር ግን ባለፉት መቶ ዓመታት፡ ከዚያ የበሬ ጋሪ፡ ከዚያው ከበሬው ጋሪ ተነስቶ—በሰዓት ወደ ሁለት ሺህ ማይሎች መብረር ወደሚችል ሮኬት ደረሰ። ከበሬ ጋሪው እስከ ሮኬት ድረስ እንደተነሳ፡ በዚያ ፍጥነት ልክ እየተነሣ ነው። አሁንም፡ ተመልከቱ፡ ያለፉት ጥቂት አመታትን ብቻ፡ ኧረ፡ ከሃምሳ አመታት በሚያንስ ደረጃ ማለት እችላለሁ።

14 እዚህ በዩቲካ ፓይክ ላይ ገና ህጻን ልጅ ሳለሁ፡ እንደዚህ ነገር ነበራቸው... ኤልመር ፍራንክ የተባለ ሰው እዚህ ይኖር ነበር። እሱም የሕግ ጠበቃ ነበረ። ይህ ሰው አባቴ ይሰራበት ለነበረው ሰው፡ ሉሽር የተባለች—ወጣት ልጅ ነበረችው

እና እሷን አገባ። እነርሱም... ሰውዬውም፡ የሆነች አይነት የቤት መኪና ነበረችው፡ በጎን በኩል በእጅ የሚሽከረክር የሞተር ማንሻ ነበራትና፡ **እንዲህ** ያሽከረክሩት ነበር፡ ባለ አንድ ማርሽ ብቻ ነበረች። እና ያኔ የነበረው—ክላክስ ክትልቅ ጎማ የተሰራ፡ **እንዲህ** አርጋችሁ የምታሰጮኹት ነበር። “ያቺ ነገር በሰአት አስራ ዘጠኝ ማይል በጣም በአስፈሪ ፍጥነት ትሮጣለች፡” ይሉ ነበር። አሁን፡ አባቴ ወርዶ መኪናው ላይ ትኝሽ አሸዋ ያመጣል፡ ይህም ለ—እናም ያንን ነገር አምጥቶ ማዳበሪያ ውስጥ ያደርገው እና እንደ ፍሬን ለመጠቀም፡ በሰዓት አሥራ ዘጠኝ ማይል እንደሚሄድ ለማየት ይፈልጋልና። አያችሁ? መንገዶቹ ደግሞ ማየት አለባችሁ፡ ኧሃ-ሃህ፡ **በዚህ** በኩል አሰር ይሄዳል፡ **በዚህ** በኩልም ከፍ-እና-ዝቅ እያለ ዘጠኝ ብቻ ይሄዳል። አያችሁ? ስለዚህ አንድ ላይ ደምራችሁ፡ በሰዓት አሥራ ዘጠኝ ማይል ታገኛላችሁ።

15 ልጆች ሳለን እስታውሳለሁ፡ እናቴ ሁላችንንም ታጥበናለች፡ ያኔ ወደ አምስት ልጆች እነሆናለን፡ ያንን ለመስማት አጥር ላይ እንንጠላጠል ነበርን። መምጣቷን፡ ከብዙ ማይሎች ርቀት እንሰማዋለን፡ ገና ከርቀት፡ ሮር፡ ሮር፡ ሮር፡ ሮር። ሁሉም ሰው ፈረሶቻቸውን ይዘው ያቆማሉ፡ ከተንጠለጠለው ልብሴ ሰወጣ፡ **እንዲህ** አድርጌ እይዘዋለሁ፡ ታውቃላችሁ። መኪናው መንገድ ላይ እየመጣ ነው፡ ይገርማል፡ አሰደማሚ ነገር ነበረ። እና—ያኔ ሳሰበው፡ ያኔ ድሮ፡ የሰባት አመት ህጻን ነበርኩ፡ አያችሁ። እንዴት... ያ 1914 አካባቢ ነበር፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ነገሮች እንዴት እንደተቀያየሩ አሰቡ። እና ተመልከቱ፡ ባለፉት አርባ አመታት ብቻ ወይም የሆነ ነገር ነው። እናም፡ እዩት፡ አሁን የተደረሰበት ሁሉ ያደርግ ዘንድ ሰድሰት ሺህ ዓመት ፈጀ፡ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ እንደሚያደርግ ተናግሯል፡ “በመጨረሻው ዘመን፡ ሰው ወዲያ ወዲህ ይመረምራል፡ እውቀትም ይበዛል።”

16 ከአራት ሺህ ዓመታት በፊት—በቺካጎ የሚገኘውን፡ የውጭ ድልድይ ያየውን፡ ሰለ ናሆም አሰባችሁ ታውቃላችሁ? እሱ... የተናገረው፡ “በሰፊ መንገዶች ይሽቀዳደማሉ።” እንግዲህ... እንደ ኦስሎ እና የተለያዩ ቦታዎች ጥንታዊ አገሮች ውስጥ ሄጄአለሁና... መንገዶቻቸው፡ ለመተላለፍ ራሱ ሰፍራ አይገኝም፡ በከተሞቻቸው ለማለፍ አንድ ሰረገላ ብቻ—የሚያሳልፍ መንገድ አላቸው። ምናልባት ሰፋቱ ከዚህ እሰከዚያ ግድግዳ ይደርሳል፡ የጎዳናዎቻቸው ሰፋት ያን ያህል ብቻ ነው፡ በዚያ ጎዳና አንድ ሰረገላ ብቻ የሚያሳልፍ ሰፋት ነው። እንግዲህ፡ ተመልከቱ፡ ናሆም ግን “ሰፊ ጎዳናዎች፡” በማለት ተናገረ። ሰረገሎቹ፡ “እንደ መብረቅ ይፈጥናሉ፡” አለ። “እንደ ፋናም ይበራሉ፡” ይህም በፊታቸው ላሉ መብራቶች ነው። ሰለ ግጭት ሲናገር፡ “እርስ በርሳቸውም ይገጫጫሉ፡” አለ። ነብይው ከዚያ ተንሰቶ ከፍ በማለት ሩቅ አየ፡ ከአራት ሺ አመታት በፊት፡ ያንን እንደሚመጣ ተመለከተ። እሰቲ አሰቡት! ኧሃ-ሃም። ምሪት ነው።

17 ወዳጆች ሆይ፡ እኛ ግን በዘመን ፍጻሜ ላይ ደርሰናል። እንዲህ ነው... ቅዱስ ቃልም እንዲሁ ነው፡ ሁሉም ነገሮች የሚሆኑበት ከመኑ አንጻር፡ በዚህ በመጨረሻው ዘመን ሁሉም ቅዱሳት መጻሕፍት እዚህ ተነጥፈዋል። እኔም በዚህ ማለዳ፡ እግዚአብሔር ቢረዳን፡ እነዚህ ነገሮች፡ የቻልነውን ያህል፡ አንዳንዶቹን እንገጣጥማቸዋለን፡ ብዬ አሰብኩ። ከዛ በኋላ የሎዶቅያ ቤተ ክርስትያን፡ ይህ የመጨረሻው ታላቅ ዘመን፡ መልእክቱን እንዴት እንደተቀበለ

እና ከዚያም እግዚአብሔር ከአፋ እስኪተፋው ድረስ፡ ለብ ወዳለ ሁኔታ እንዴት እንደጠፋ እና መልዕክቱን እንደተወ እናያለን። እያችሁ፡ በሌላ አባባል፡ ሲያሰበው እንኳን ሆዱን ያቅለሸልሸዋል። "ከአፌ ልተፋህ ነው፡" አለ።

18 አሁን፡ ዛሬ ጥዋት መጥቀስ የምፈልጋቸው ጥቂት የተጻፉ ቅዱሳን ቃላት ይዣለሁ። ከዛ በፊት ግን ለአፍታ ያህል፡ ለጸሎት ቃል ለመነሣት ይከብደን ይሆን ወይ፡ እላለሁ፤

19 ቸር የሰማይ አባታችን ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት በዚህ የሰንበት ቀን እንደገና መጥተናል። ከውጪም፡ ዝናቡ መውረድ ጀምሯል፡ በረዳማ ቀዝቃዛ ነፋሰም እየነፈሰ ነው፡ ዛሬ ግን ከራሳችን በላይ ጣሪያ፡ እና ትንሽ ቦታ ሰላለን በጣም ደስ ይለናል፡ ሌላም ሳሊናችን በሚነግረን መንገድ እግዚአብሔርን ማምለክ የምንችልባት አገር አለን።

20 እንግዲህ ይህ ብዙም እንደማይቆይ በቃልህ ተገንዝበናል፡ ሰለዚህ፡ አባት ሆይ፡ ዛሬ፡ በልዩነት **እንድትቀባን** እንጸልያለን፡ ይህም እንድናገኘው ከተመደበልን ነገር ሁሉ የተሻለውን ማግኘት እንድንችል፡ እና በፊታችን ሊመጡ ላሉ ይህን ማድረግ ለማንችልባቸው ዘመናት የተዘጋጁ እንሆን ዘንድ ነው። ለምን ያህል እንደሚቆይ አናውቅም፡ ለሳምንታት፡ ለወራት፡ ወይም ለዓመታት ሊሆን ይችላል፡ አናውቅም፡ ወደፊት ይሄን ነገር የማናደርግበት ጊዜ ግን ይመጣል። ሰለዚህም አባት ሆይ፡ በመለኮታዊ መመሪያህ እንድትጠብቀን፡ እና አሳባችን በአንተ ላይ እንዲሆኑ፡ እንጸልያለን፡ አቤቱ ጌታ ሆይ፡ የልባችን አሳብ በፊትህ የተወደደ ነው።

21 ኃጢአታችንን ይቅር በለን። ኃጢአት እንደሠራንና ከመንገድህ እንደሳትን፡ በፊትህ ሰንናዘዛቸው ይህን እንጠይቃለን። ጌታ ሆይ፡ ቅጥር አገልጋዮች አድርገን ብቻ እንጂ፡ የአንተ ለመባል የማይገባን ነን። አድርጉ የምትለንን ማንኛውንም ነገር፡ የተጣለብንን ማንኛውንም ተግባር ለመፈጸም ፍቃደኞች እንሆናለን። ጌታ ሆይ፡ በመንግሥትህ ብቻ ተቀበለን እንጂ፡ በዓለም ፊት በተጋረጠው፡ ታላቅ እና አስከፊ ዘመን፡ እንዲህ ለመሰራት እና ለማድረግ ፈቃደኞች ነን።

22 አሁን በመገኘትህ ባርከን፡ በመንፈስ ቅዱስህ አስተምረን፡ አብረን በመሆናችን ክብር ይሁንልህ። በኢየሱስ ስም እንጠይቃለን። አሜን።

23 ከሁሉ በፊት ማለት የምፈልገው፡ አስቀድሜ፡ ዛሬ ከማለዳው ጀምሮ ሳያቸው የነበሩት፡ እዚህ የተገኙ ወዳጆቼን ሁሉ እንኳን ደህና መጣችሁ ማለት እፈልጋለሁ። በማታ ክፍለ ጊዜ እዚህ ትንሽ ያሰቸግራል፡ መብራቶቻችን ከተሰቀሉበት ቦታዎች በሰተጀርባ ሁሉ ህዝቡ እንዳይታይ ያሰቸግራሉ። እና እዚህ ምሽት ላይ ከዚህ መድረክ ላይ ማየት በጣም ከባድ ነው፡ በቀን ውስጥም እንዲሁ ነው። ከተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የመጡ ብዙ ጓደኞቻችንን አይቻለሁ፡ በምሽት ከምችለው በላይ በቀን ዛሬ ለይቻቸዋለሁ። ሁሉንም ለመጥራት መሞከር ያሰቸግራል፡ በእውነት እንደማደንቃችሁ እንድታውቁልኝ ግን እፈልጋለሁ። በቅዱስ ቃል የማደርገው፡ ከባባድ መቆራረጥ እና ልዩ ልዩ ነገር ሁሉ፡ አንድን... እውነት ለማውጣት ያክል ነው። እኔ ማድረግ የፈለኩትን ሳይሆን፡ እግዚአብሔር እዚህእንዲሆን የጻፈውን፡ እያችሁ። ሌላ ነገር የለውም። አሁንም በብዙ ድርጅቶች ውስጥ ያሉ እና ሌሎችም ወንድሞቼ፡ ከእኔ ጋር ቁጭ

ብለው አይቻለሁና፡ እጅግ፡ እጅግ አድርጌ አመሰግናችኋለሁ። ስለ እናንተ... ጸሎቴ እግዚአብሔር አብዝቶ እንዲባርካችሁ እና እንዲረዳችሁ ነው።

24 አሁንም... [ወንድም ሰቲከር "ወንድም ብራንሃም?" አለ፡—እርታዒ።] ወዬ፡ ወንድሜ። ["እዚህ ያሉትን ሰዎች ሁሉ ወክዬ ለመናገር የቤተ ክርስቲያን ፈቃድ ካገኘሁ፡ እንደምናደንቅህ እንድታውቅልን እንፈልጋለን።"] አመሰግናለሁ፡ ወንድም ሰቲከር። ["እንዲሁም እንወድሃለን።"] አመሰግናለሁ፡ ወንድም ሰቲከር። ["እንዲሁም ልታልፋቸው በሚገባ ነገሮች ማለፍ የምትችልበት ጸጋ እንድታገኝ እየጸለይንልህ ነው፡ ይህም ከጎንህ እንድንቆም ነው።"] አመሰግናለሁ፡ ወንድም ሰቲከር። አመሰግናለሁ፡ ቤተ ክርስቲያን፡ ይህን ስትናገሩ በጣም ደስ ይላል። ስለዚህም አብዝቼ አመሰግናለሁ።

25 አንድ ሰው ትናንት ማታ ሲናገር ነበር፡ ወንድም ፍሬድ ይመስለኛል የደወለልኝ ትናንት ማታ ከመሄዱ በፊት፡ አንድ ወንድም ስላየው ራእይ ወይም ሕልም ተናገረ፡ በምድር ክበብ ላይ ቆሞ ጥቁር ደመና እየተንከባለለ ሲከተለው ያያል። እኔን እንደሆነ አውቃለው። ያ ግን፡ ምንም ቢሆንም... እግዚአብሔር እስኪጨርስ ድረስ አይ—አይሳካለትም፡ ከዛ—ከዛ በኋላ የእኔ—መሄጃ... ጊዜዬ ይሆናል። ስለዚህ...

26 ነገር ግን እኔ—እኔ ይህን፡ በፍጹም "እንደ ታላቅ ነገር" አላሰበውም። አይ፡ መሆን አልፈልግም፡ አያችሁ። ነገር ግን ስለ **ሕይወት መዝሙር** አስባለሁ፡

የታላላቅ ሰዎች ሕይወት ያስታውሰናል

ጳውሎስ ምን እንዳደረገ፡ ኢሬኔዎስ ያደረገውን፡ ሉተር ያደረገውን፡ ዌስሊ ያደረገውን፡ ወይም ቅዱስ ማርቲን ያደረገውን፡ እና ያደረጉትን ሁሉ፡ ተመልከቱ።

የታላላቅ ሰዎች ሕይወትም ያስታውሰናል
ህይወታችንን ከፍ ከፍ ማድረግ እንድንችል፡
መሸኛችንን፡ ከኋላችን ትተን
የእግር አሻራዎች በጊዜ አሸዋ ላይ አኑረን፣

የእግር አሻራዎች፡ ወይም ሌላ፡
በህይወት ዋና ነገር በጉዞ ላይ ሆነን፡ (ከሄድኩ በኋላ፡ አያችሁ፡ እና ከሄድኩ በኋላ።)
የፈራ እና መርከቡ የተሰበረበት ወንድም፡ (ከእነዚህ መጻሕፍቶች አንዱን አንስቶ ያነብ ዘንድ፡)
እሱን በማየት፡ ዳግም ልቡን እንዲገዛ። (ያ ነው።)

እንግዲህ፡ እንነሣና፡ እንሥራ፡
ለሰልፍ ለተዘጋጀ ልብ፡ (እኔ ተመችቶኛል፡ እናንተስ? )
እንደ ዲዳዎች፡ እንደሚገፉ ከብት አትሁኑ! (ወደ እሱ መወሰድ አለብን።)
በሰልፍ መካከል ጀግኖች ሁኑ! (እኔ—ተመችቶኛል።)

27 አሁን፡ ይህ ታናሽ ወንድማችን፡ ጆርጅ፡ የሚወደው ነበረ፡ በቀብሩ ሥነ ሥርዓት ላይም ተጠቅሜበታለሁ። አብረን... ተቀምጬ **የሕይወትን መዝሙር** እጠቅሳለሁ፡ ታውቃላችሁ፡ እሱም ቁጭ ብሎ **ከሞት ባሻገርን** ይጠቅሳል። አያችሁ? ይህን ሰምታችኋል፡

የፀሐይ መጥለቅ እና የምሽት ኮከብ፡
ለእኔ እንደ አንድ ግልጽ ጥሪ!
ሞት ማዶ ላይ ምንም አይለቀሰልኝ፡
ወደ ባህር ሰወሰድ፡ (ደጋግማችሁ ሰምታችሁታል።)

ሁሉ በጊዜ እና በቦታ ሳይታሰር የሚንቀሳቀሰበት፡
ግጎርፉም አርቆ እኔን የሚወልድበት፡
እኔ ግን አብራሪዬን ፊት ለፊት ለማየት ተሰፋ አደርጋለሁ
ሞትን በተሻገርኩ ለት። (ሞትን በተሻገረ ጊዜ እንዲሁ
እንደሆነለት እርግጠኛ ነኝ።)

28 እንዲሁም፡ የእኔም እንዲሁ ነው፡

ቻው መባባል ከኋላዬ ቀረ
የእግር አሻራ በጊዜ አሸዋ ላይ ትቼ፡
ሌሎች፡ ያን አይተው፡ ይከተሉበታል፡
አይዞህ በርታ ቀጥል።

29 ኢየሱስ በታላቅ ቀን፡ ይመጣልና (በዚህ ጠዋት ላይ የምናጠናው ይህ ነውና)፡ ያኔ ሁሉም ነገር ያበቃል።

30 አሁን፡ በእነዚህ የቤተክርሰቲያን መልእክቶች እንዳንችል፡ ዛሬ ጠዋት አሰብኩ… አሁን፡ ምናልባት፡ ጌታ ከፈቀደ፡ በቅርቡ፡ **እውነተኛይቱ እና ሐሰተኛይቱ ቤተክርሰቲያን** በሚል ርዕሰ ሌላ ትንሽ ተከታታይ ሰብሰባዎች ሊኖሩኝ ይችላሉ፡ ከኦሪት ዘፍጥረት ጀምሮ፡ መጽሐፍ ቅዱስ በመሉ እየዳሰሰን እሰከ ራዕይ ድረሰ እናየዋለን። ሁለቱም አብያተ ክርሰቲያናት፡ ምን እንደሚያደርጉ እናያለን። ከዛ በኋላ ምናልባትም አንድ ቀን… ጌታ ቢፈቅድ፡ የተሻለ ሰፊ ቦታ እንድታገኙ ቤተክርሰቲያኑ እንዲሰራ እናደርጋለን… ምን ያህል ደውለው እንደዚያ እንደነገሩን ትገረማላችሁ፡ እያሽከረከሩ ተጉዘው ሞልቶ ያዩታል፡ ሰለዚህ፡ ዝም ብለው ይቀጥላሉ። እኛም እንግዲህ… ቦታ የለንም።

31 እና ምናልባት በ-… በጋ ወቅት ሞቃታማ የአየር ጠባይ ወይም ሌላ ነገር ከሆነ፡ የሁለተኛ ደረጃ ጂም ወይም ሌላ ነገር እንጠቀማለን፡ እርፈን፡ የራዕይ መጽሐፍን፡ ወይም የሆነ ነገር እንማራለን፡ ወይም መጽሐፈ ዳንኤል እና ራዕይ፡ አንድ ላይ አጣምረን ማየት እንችላለን።

32 አሁን፡ ከአይሁድ ሕዝብ ጋር ማገናኘት ፈጽመን አይገባንም። አይሁዳውያን…

33 አሁን፡ እንዳልኩት፡ በ—በ1500 የጨለማ ዘመን ላይ፡ የካቶሊክ የሰልጣን ተዋረድ፡ ምሰረታ ላይ በነበሩ ጊዜ፡ የመንግሰት እና የቤተ ክርሰትያንን አንድ እንዲሆኑ አድርገዋል፡ ያም “ድኅረ-ሺ አመት” አሉት። ቤተ ክርሰቲያኒቱ ምሰለኔዋን ሰለተቀበለች ሙሉ በሙሉ በሺኅ አመት ውሰጥ—የነበሩ መሰላቸው፡ ይህም በክርሰቶሰ ፈንታ ዙፋን ላይ ተቀማጭ ነው። እሱም ቤተ ክርሰትያን ከመንግሰት ጋር አንድ እንዲሆን ያደርጋል፡ ይህም “ታላቁ ሺ አመት ሆኗል፡” ሁሉም ተመችቷቸዋል። እሰከ አሁን ድረሰ እንዲህ ያምናሉ። ነገር ግን ሰህተት ነው። ምክንያቱም ያለ ክርሰቶሰ መምጣት፡ ሺ አመት አይመጣም፡ ሊመጣ አይችልም።

34 ሺ አመቱ መንግስት የሚያስገባው ክርስቶስ ነው፡ እሱም የብልጽግና ልጅ ነው፡ እሱ ሲመጣ፡ ያኔ ሺህ አመት ይሆናል። እናም ይህ ሲሆንም፡ የቤተክርስቲያኑ ወደ ላይ መነጠቅ ይሆናል፡ ከዚያም የክርስቶስ መምጣት ይሆናል። አሁንም አስታውሱ፡ ይህ ሲሆን... ቀጣይ የምንፈልገው ነገር ምንድን ነው? የቤተክርስቲያን መነጠቅ።

35 አሁን፡ የቤተክርስቲያኑ መነጠቅ እና የነጩ ዙፋን ፍርድ እንዳይቀላቀልባችሁ። ምክንያቱም፡ የቤተክርስቲያን መነጠቅ፡ ፍርድ የለበትም፡ ተመልከቱ፡ እዚህ ጋር በግልጽ ይታያል። ትክክል ነው፡ "በክርስቶስ ያሉት ከፍርድ ነጻ ናቸውና።" ኢየሱስም፡ "ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ፡ ወደ ፍርድ ከቶ አይመጣም አለ።"

36 ያን ማድረግ እንዴት እንችላለን? ወደ ክርስቶስ ገብተን አንድ አካል እንድንሆን በመጠመቅ፡ አንደኛ ቆሮንጦስ 12 ላይ፡ "አንድ አካል።" ከኢየሱስ ክርስቶስ አካል ጋር እንድንሆን ዘንድ ተጠምቀናል፡ ያንን አካልም በእግዚአብሔር ዘንድ ተፈርዶበታል። አስቀድሞ በዚያ አካል ላይ ፈርዶበታልና፡ ዳግመኛ ለፍርድ ሊያቆመን አይችልም። በክርስቶስ ጸጋ እና በበጎ ፈቃድም ወደ እርሱ አገባን፡ አንደኛ ቆሮንቶስ 12 ላይ፡ "በአንድ መንፈስ ሁላችንም አንድ አካል እንድንሆን ዘንድ ወደዚያ ተጠምቀናል፡ ፍርድ ሁሉ ስለተቀበለ ከፍርድ ሁሉ ነጻ ነን።" አቤት፡ በሱ ምክንያት ደስ አይላችሁምን! ፍርድ ሁሉ ሰለ እና ተቀበለ። ከእንግዲህ ፍርድ የለም! ወደ እርሱ፡ ወደ አካሉ፡ ወደ ምሥጢራዊው አካሉ ለመምጣት ፈቃደኛ ያልሆኑት ግን... እኛ እንዴት እንገባበታለን? እጅ በመጨባበጥ ነውን? አይደለም። በደብዳቤ ነውን? አይደለም። በልዩ ጥምቀት፡ ውኃ? አይደለም። "በአንድ መንፈስ፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ሁላችንም ወደዚያ አካል እንጠመቃለን!"

37 አሁን አስታውሱ፡ ዛሬ ጠዋት በዛ ርዕስ ላይ በደንብ እናየዋለን። ወይ በአካሉ ውስጥ ወይም ከአካሉ ውጭ ናችሁ እንጂ፡ መካከለኛ የለም። የተሻሉ-ክርስትያኖች ብሎ ነገር የለም። እና—እና በዚህም ምክንያት... ወይ ክርስቲያን ናችሁ ወይ ክርስቲያን አይደላችሁም። ጥቁር-ነጭ ወፍ የለም፡ ንቁ-ሰካራም የለም። ሊኖር አይችልም። ወይ ክርስቲያን ነህ ወይም ክርስቲያን አይደለህም። ወይ በክርስቶስ ውስጥ ነህ ወይም አይደለህም።

38 እንግዲህ፡ ይህ ነገር ትምህርት ሊመስልብኝ ይችላል፡ አይደለም... አስተማሪ ከመሆን ገና ሩቅ ነኝ። ማስተማር ግን መከርከም ነው፡ በክርስቶስ አካል ውስጥ—የተለየ ስጦታ ነው። በመጀመሪያ ሐዋርያት፡ ከዚያም ነቢያት፡ ቀጥሎ አስተማሪዎች፡ እና ወንጌላውያን፡ እረኞች አሉ፡ በአካሉ ውስጥ አምስት የአገልግሎት ስጦታዎች አሉ። ማስተማር ደግሞ ከመንፈስ ስጦታዎች አንዱ ነው። አሁን፡ ትክክል ሆኖ ያየሁትን ጨምሬ ወደ ህዝቡ ለማምጣት ብቻ እሞክራለሁ፡ ቅዱስን መጻሕፍትን እያጠናሁ የክርስቶስ አካል ለማስታወቅ ብቻ ነው። አሁን፡ ይህ በክርስቶስ ብቻ፡ የክርስቶስ አካል እንዲታወቅ ማድረግ ብቻ ነው።

39 አሁን፡ የመጀመሪያዎቹ ሦስት የራዕይ ምዕራፎች ስለ ቤተ ክርስቲያን ይናገራሉ። አህዛብ፡ አይሁዳዊ፡ ኢትዮጵያዊ፡ አፍሪካንስ፡ በአለም ላይ ያሉ

ሁሉም አይነት ሰዎች ይህንን አካል ለመመስረት ወደ አሕዛብ ይሄዳሉ፡ ጥቁር፡ ነጭ፡ ቡናማ፡ ሁሉም፡ እንደ ጉንጉን አበባ ናቸው፡ እግዚአብሔር በመሠዊያው ላይ የሚያኖረው፡ ትክክለኛ ነገር፡ ከሁሉም አይነት አገሮች፡ ወገኖች፡ ቋንቋዎች፡ እና ህዝቦች የተሰራች ናት።

40 አሁን፡ ግን፡ ከ 3ኛው ምዕራፍ በኋላ (ከቤተ ክርስትያን ዘመን በኋላ)፡ እግዚአብሔር ተመልሶ ይመጣል አይሁዶችን ያነሳል፡ በዚያ ዘመን ከእንግዲህ ቤተክርስቲያን አትታይም። አይሁዶች ናቸው። እግዚአብሔርም ከአይሁዶች ጋር፡ ከእስራኤል ጋር እንደ ሀገር፡ ሁልጊዜም እንደ ሀገር እንጂ በግለሰብ ደረጃ አይሰራም።

41 ባለፈው አንዱ የተቀበለው በዚህ መንገድ ነበር። በዚያ፡ **በዲቃላው ኃይማኖት** ላይ—ብዙ ደብዳቤዎች ተልከውልኛል፡ ይህም በዚያ አስተያየት በመስጠቴ ነው… መጽሐፍ ቅዱስ "ዲቃላ ልጅ" የሚለው፡ ከሕግ ውጪ የሆነውን፡ ለአስር ትውልዶች ወደ ጌታ ጉባኤ መግባት አይችልም ይለዋል፡ ይህም ዲቃላ ልጅ ወደ ጌታ ጉባኤ ለአራት መቶ አመታት ሊገባ አይችልም ማለት ነው። ማዳቀል ይሄን ያህል መጥፎ ነበረ፡ ይህ ማለት አንድ ሴት ልጅ መውለድ ፈልጋ ከሌላ ወንድ ጋር ከተኛች፡ በአባቱ ሳይሆን በሌላ ወንድ ሲሆን፡ የሚወለደው ህጻን ዲቃላ ይባላል። አያችሁ? ያም በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ነው፡ በእግዚአብሔር ፊት፡ እንደገና ይዋለድ ዘንድ አስር ትውልዶችን ይጠይቀዋል።

42 ያ ግን በዚህ ዘመን አይሰራም። አሁን አዲስ ልደት አግኝታችኋልና። እነርሱ… በዚያ ዘመን አንድ ልደት ነበረቻቸው፡ ያም ደግሞ በስጋ የሚደረገው መራባት ነው። አሁን ግን አዲስ ልደት አለን እርሱም መንፈሳዊ የሆነ፡ ከብዙዎች መካከል የሚያወጣ። እኛ ደግሞ በእግዚአብሔር መንፈስ ዳግመኛ የተወለድን፡ በክርስቶስ ኢየሱስ አዲስ ፍጥረቶች ነን። አዲስ ፍጥረታት! **ፍጡር** በሚለው ቃል ላይ፡ እንዳንዶቻችሁ ምሁራን ይህን ከተረዳችሁት (ካልተረዳችሁት፡ አሁን ተረዱት።)፡ **ፍጡር** የሚል የመጣው "አዲስ ፍጥረት" ከሚለው ከግሪክ ቃል ነው። ኦህ፡ ልክ እናንተ አሁን በስጋ ተወልዳችሁ፡ እዚህ ፍጡራን እንደሆናችሁ ሁሉ፡ በዚያም በሰማይ የተወለዳችሁ፡ አዲስ ፍጥረት ናችሁ። በ… እግዚአብሔር አዲስ ሰው አዲስ ፍጥረት ውስጥ ናችሁ። አዲስ ፍጥረት፡ በመወለድ ጊዜ። ነገር ግን ልክ እንደ ተፈጥሯዊ ልደት፡ በመወለድ መሆኑ ግድ ነው፡ መንፈሳዊው ልደት ልክ እንደ ተፈጥሯዊ ልደት እንዲሁ መሆን አለበት።

43 ወጣት ባልና ሚስት አግብተው "የመጀመሪያ ልጃችን፡ 'ዮሐንስ፡'" እንለዋለን ይላሉ። ፈጽሞ ካልተወለደ ግን፡ ዮሓንስ ብሎ ነገር አይኖርም። በቃ። ተመሳሳይ ነው፡ ምንም ያህል… ስለ ሰማይ ብዙ ተረታዊ አስተሳሰብ ብትገነቡም፡ ምንም ታላቅ ቢሆን፡ ዳግመኛ ካልተወለዳችሁ አትገቡባትም። አለቀ፡ አያችሁ። ልደት መሆን ስላለንበት፡ በዚያ መንገድ መሆኑ ግድ ነው። እግዚአብሔር ሕጎቹን አስቀምጧልና ሁሉም ነገር እንደ ህጎቹ ይሰራል። አያችሁ?

44 እንግዲህ፡ እዚህ ጋር፡ የሚድኑ የአይሁድ ቅሬትያዎች ይኖራሉ። በመጀመሪያ እነሱን እናያቸዋለን፡ ምክንያቱ እንደ አቀማመጡ… አሁን፡ ሁል ጊዜ፡ በተደጋጋሚ ሰዎች በሶስት ምድብ ይከፈላሉ። እና ይህን… በአእምሮአችሁ ያዙ፡ እነዚህም፡

አ—አማኝ፡ አስመሳይ-አማኝ፡ እና የማያምን ናቸው። እነዚህ ሶስቱ ናቸው። አይሁድ አለ፡ ይህም ስለ እኛ ሲባል የተወገዘ-ነው፡ ቀጥሎ ለብ ያለች ቤተ ክርስቲያን አለች፡ ከዚያም በመንፈስ-የተሞላች ቤተ ክርስቲያን ናቸው።

45 አንድ ጊዜ፡ ቻርሊ ቦሃኖን የማን ፕረዚዳንት በነበረ ጊዜ... ወይም እኔ በዚያ በምሰራበት ጊዜ፡ በሕዝብ አገልግሎት ኩባኒያ ውስጥ የደቡብ ዲስትሪክት ኃላፊ ነበረ። ያኔ እንደ ታዳጊ፡ እንዲሁ መጽሀፍ ቅዱስ አጠና ነበር። እርሱም፡ “ቢሊ፡ ማንም... ” እንዲህ አለኝ፡ “ዮሓንስ በፍጥሞ ደሴት—በነበረ ጊዜ ከባድ ሚጥሚጣ ቃርያ በልቶ ሕልም ሳያይ አይቀርም።”

46 አለቃችን፡ ተቆጣጣሪ ነበረ። እኔም “ሚስተር ቦሃኖን፡ እንዲህ ማለት አልነበረብህም፡” አልኩት።

እሱም አለኝ፡ “እንዴ፡ ታዲያ ይሄ በአለም ላይ ማን ሊገነዘበው ይችላል? ”

እኔም አልኩት፡ “የሚገባ ነው። መንፈስ ቅዱስ ሊገልጠው ከወደደ ይገባል።” እውነት ነው።

47 እና “ወይ፡ ጉድ!” አለ፡ አለኝም፡ “እኔም ለማንበብ ሞከርኩ ፓስተሬም ሞከረ፡” “በሚሰቀጥጥ ደረጃ ላይ ደርሰናል፡” አለኝ። “ሙሽራይቱ—በሲና ተራራ ላይ አይተናል፡” አለኝ። አያችሁ? እና እንዲህ አለኝ፡ “በመቀጠል ዘንዶው ከአፉ የሚወጣ ጎርፍ ባወጣ ጊዜም ሙሽራይቱ እናያታለን፡ ይህም ከሴቲቱ ዘር ቅሪት ጋር ጦርነት ለማድረግ ነው። ሙሽራይቱን በገነት እናያታለን። ሦስቱም፡ በተመሳሳይ ጊዜ።”

“ይህ የመንፈሳዊ መረዳት ጉድለት ነው፡” አልኩት። አያችሁ?

እርሱም “እንዴ፡ ይኸው አሉልህ፡ ሶስቱም... ሁሉም በአንድ ጊዜ፡” አለኝ።

48 እኔም አልኩት፡ “እዎን፡ ወዳጄ፡ ይሁን እንጂ አቀማመጣቸው እንደዛ አይደለም። እየህ፡ መቶ አርባ-አራት ሺዎቹ እንዲሁ ሳይሆኑ ‘ሙሽራይቱ፡’ ብለህ ጠራሃቸው፡ አይሁድ ናቸውና። ዘንዶውም ይዋጋቸው ዘንድ ከአፉ ውሃ ያፈሰሰባቸው ደግሞ ቅሬታዎች ናቸው፡ ማለት የኢየሱስ ምስክር የነበራቸው፡ ትዕዛዛቱንም የሚጠብቁ ከሴቲቱ ዘር ወደ ኋላ የቀሩት ናቸው። ሙሽራይቱ ግን ወደ ክብር ተወስዳለች።” አያችሁ?

49 በዮሐንስ ራእይ ምዕራፍ 14 ላይ፡ በሲና ተራራ ቆመው ያየሃቸው፡ መቶ አርባ-አራት ሺዎቹ ናቸው፡ (በትክክል እውነት ነው።) የአባታቸውን ስም በግንባራቸው ውስጥ የታተመባቸው። ትክክል ነው። አይሁድ፡ የአይሁድ ቅሬታዎች።

50 በመቀጠል እነሆ ዘንዶው መጣ፡ ይህም የሮማውያን የስልጣን ተዋረድ ነው። (ይህም፡ ቤተክርስቲያኒቱ ተነጥቃ፡ በሠርግ እራት ለሦስት ዓመት ተኩል በክብር የነበረችበት ጊዜ ነው።) ከዚያም ዘንዶው፡ አያችሁ፡ **ዘንዶው** ሲባል፡ ቀዩ ዘንዶ ሁል ጊዜ “ሮም” ነው። አሁን ያንን ለእናንተ ለማረጋገጥ፡ በ—በራዕይ 12 ላይ፡ ዘንዶውም አሕዛብን ሁሉ በብረት በትር ይገዛቸው ዘንድ ያለውን ወንድ ልጅ በምትወልድ ሴት ላይ ተቈጣ፡ ከአፉም ውኃ አጎረፈ... ወይም—ወይም ከዘሩ ቅሬታዎች ጋር ጦርነት ለመግጠም ማለት ነው። አስቀድሞ ግን፡ ይህ ቀይ ዘንዶ፡ በሴቲቱ ፊት ቆመ። ሴቲቱ ይህን ሕፃን እንደወለደች፡ ልክ እንደ ተወለደ ህጻኑን መዋጥ ይፈልጋል። እንግዲህ፡ ልጇን

(ኢየሱስን) እንደተወለደ ሊውጠው፡ በእስራኤል ቤተ ክርስቲያን (በሴቲቱ እስራኤል) ፊት የቆመ ማን ነው? ሮም! ሄሮድስ ከሁለት-አመት-በታች ያሉትን ህጻናት እያንዳንዱን ልጅ መገደል እንዳለበት—አዋጁን አወጣ፡ በመላ አገሪቱ ያሉትን የዕብራውያን ልጆች ሁሉ ያስገደለ ግድያ ተፈጸመ። እርሱም የሱ ጥላ ነበርና፡ ፈርዖን ሙሴን ለመያዝ ያደረገውም ያው ነበር፡ ልጆችን ሁሉ አረደ እሱን ግን አላገኘውም። አቤት—አቤት—አቤት—አቤት፡ እንዴት እንደሚሰውራቸው እግዚአብሔር አዋቂ ነውና።

51 አቤት፡ እናንተስ መሰወራችሁ ደስ አይላችሁምን? አቤት፡ መደበቂያ ስፍራ! መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፡ “እናንተስ እንደሞታችሁ ህይወታችሁም በክርስቶስ እንደሆነች ቁጠሩ፡ በክርስቶስ ተሰውራችሁ በመንፈስ ቅዱስ ታትማችኋልና።” ዲያብሎስ ቢፈልግም አያገኛችሁም። አያችሁ፡ ሊያገኛችሁ አይችልም። በክርስቶስ ተሰውራችኋልና! እንደሞታችሁ ቁጠሩ! ህይወታችሁም በክርስቶስ ተሰውራለች፡ በክርስቶስ በእግዚአብሄር ዘንድ ተሰውራችሁ፡ በመንፈስ ቅዱስ ታትማችኋል።

52 አሁን፡ አሁን፡ እነዚህ ቅሬታዎች ሞኞቹ ደናግል ናቸው፡ ከሴቲቱ ዘር የተረፈውን ይዋጋ ዘንድ ውሃውን ከአፉ ያጎረፈባቸው ናቸው። አሁን፡ እስኪ ቅሬታዎች ምንድነው? አሁን፡ እናንተም—እነዚህ አይነት ጥላዎች አንድ ላይ ማያያዝ አለባችሁ። ቤተ ክርስቲያን **ስጋዊት** የሆነች ቤተ ክርስቲያን አለች።

53 ምናልባት አሁን... በተሻለ መልኩ ግልጽ ለማድረግ እዚህ ጋር በስዕል ማስፈር እችላለሁ። አሁን፡ ወንድም ኔቪል፡ አንዴ ጊዜህን ልሻማብህ፡ እባክህ ከይቅርታ ጋር። [ወንድም ኔቪል “አሜን። የኔ የምለው የለኝም፡” አለ።—አርታዒ።]

54 አሁን፡ ምን ነበር... ምን ነበር እስቲ አስታውሱኝ? እምነት አልባው፡ “እአ” ብዬ እስይመዋለው፡ እምነት አልባው፡ ኃጢአተኛ ነው። ሌላው ደግሞ ተራ የሆነውን፡ ተራ ቤተ ክርስቲያንን፡ “ተቤ” ብዬ ልሰይመው። ሌላኛዋ ደግሞ እነሆ የዳነች ቤተ ክርስቲያን፡ “የቤ፡” የዳነች ቤተ ክርስቲያን ልበላት። እንግዲህ፡ በአእምሯችሁ ውስጥ ይህን ያዙ።

55 አሁን፡ በዚህች በዳነች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሁለት ጎራዎች አሉ፡ **እዚህ** ጋር እና **እዚህ** ባለች ቤተክርስቲያን፡ በክርስቶስ ጥላ ምሳሌ የሆነች፡ አንዳቸው ስነፏ ድንግል ስትሆን፡ ሌላኛዋ ግን በመብራቷ ዘይት የያዘችዋ ነበረች። አሁን፡ እናንተ—ሁላችሁ... ስንቶች ታሪኩን ታስታውሳላችሁ? ከእፍታ በኋላ ወደዚያ እንመጣበታለን።

56 አሁን ግን፡ ያን ከማድረጋችን በፊት፡ በመጀመሪያ፡ በራዕይ 7 ላይ ወዳሉት፡ አንድ መቶ አርባ-አራት ሺዎቹ እናልፋለን፡ በትክክል መረዳት ይቻል ዘንድ ነው። አሁን፡ ይህን ማስታወስ አለባችሁ። ለእናንተም ማስታወሻ ለምትይዙ፡ ራዕይ 7 ላይ።

57 በሉ እስኪ አሁንስ ጊዜአችን እንጠቀምበት። (እና—እስከ—የ ዛሬው ጠዋት አገልግሎት... ድረስ—የጥምቀት ስርዓት አታደርጉም፡ በጣም ጥሩ።) ቶሎ ለ... ለመውጣት እና ስንት ሰዓት እንደሆነ ለማየት ሰዓቴን እዚህ አደርገዋለሁ። አሁን የቀረን—ወደ ሁለት ሰዓት ያህል ነው፡ እና ይህን ጥናት ለማድረግ ጌታ ይርዳን።

**... ከእነዚህ ነገሮች በኋላ...**

58 እኛም፡ አሁን... 6ኛው ምዕራፍ—ስለ ነጭ ፈረስ ያትታል፡ እርሱም መንፈስ ቅዱስ ድል እየነሣ፡ ድል ለመንሣት ወጣ። ከዛ ሐመር ፈረስ፡ ሞት፡ እና ሲኦል ተከተለው። እና በፈረሶቹ ላይም ፈረስ ጋላቢዎች ነበሩ።

59 አሁን፡ "ከነዚህ ነገሮች በኋላ፡" ከታልቁ ጥፋት በኋላ ነው። በመጀመሪያ መንፈስ ቅዱስ በምድር ላይ ወጣ፡ "ድል ለማድረግ ድል እያደረገ"፤ ከዚያም የታላቁ ረሃብ ዘመን የሚመጣው መጣ፡ "አንድ መሰፈሪያ ስንዴ በዲናር፡ ሁለት መሰፈሪያ ገብስ በዲናር፡ ወዘተረፈ፡ ዘይቴን እና ወይኔን ግን አትጉዳ"፤ ከዚያም ማሕተሞች እስኪከፍታቸው ድረስ—እንዲህ እያለ ይቀጥላል።

> **... ከዚህም ነገር በኋላ በአራቱ በምድር ማዕዘን ቆመው አራት መላእክት አየሁ፡** እነርሱም... **ነፋስ በምድር** ቢሆን፡ **ወይም በባሕር፡ ወይም በማንም ዛፍ... እንዳይነፍስ አራቱን የምድር ነፋሳት ያዙ።**
>
> **የሕያው አምላክ ማኅተም ያለውም ሌላ መልአክ ከምስራቅ** ሲወርድ **አየሁ፡** ምድርን**ና** ባሕርን**ም... ሊጐዱ... ለጎዱ ለተሰጣቸው ለአራቱ መላእክት፡ በታላቅ ድምፅ እየጮኸ፡**
>
> **የአምላካችንን ባሪያዎች** ግምባራቸውን **እስክናትማቸው** ድረስ **ምድርን ቢሆን፡ ወይም ባሕርን፡** ወይም... ዛፎችን፡ **አትጉዱ፡ አላቸው።**

60 አሁን፡ አይሁዶች፡ ሁል ጊዜም ባርያዎች... የእግዚአብሔር ባርያዎች እንደነበሩ አስታውሱ። አብርሃምም ባርያው ነበረ። አሕዛብ ግን ባርያ ሳይሆን፡ ሙሽራ ነው፡ ልጅ ነው። ልጅ ይህ ነው፡ ቤተ ክርስትቲያን። አይሁድ ባርያዎች ናቸው። አቤት፡ እነዚህ ቃላት በደንብ ማበጠር... በቻልን ኖሮ። እኔ ራሴ ክፍሌ ውስጥ እንዲህ አደርጋለሁ፡ ማጣቀሻዎቹን በሙሉ አጋላብጣለሁ ከዚያ አገኘዋለሁ። አይሁድ ባርያዎች ናቸው። እዚህ ቆሜ ጊዜውን በሙሉ ስለ "ባርያ" ከጨረስኩት፡ ሌሎች ነጥቦችን አልዳሰሳቸውም፡ አያችሁ። ስለዚህ አስታውሱ፡ መጽሐፍ ቅዱስን መርምራችሁ፡ አይሁድ የእግዚአብሔር ባርያ መሆናቸውን ትደርሱበታላችሁ።

61 እዚህ ጋር በጥሩ ሁኔታ ማነጻጸር እንችላለን፡ ወደ ሕዝቅኤል 4 ላይ ብንመለስ፡ እንዲህ ተናግሮ እናገኘዋለን፡ "ከዚህ በፊት እንደዚህ ያለ ነገር ተከሰቷል? " ረጃጅሞቹን ግንቦች ተመለከተ፡ ባያቸው ጊዜም፡ በከተማው ውስጥ ርኩሰት ሲደረግ አየ። በዚያም እነሆ... ማረጃ ስለት የያዙ አራት ሰዎች መጡ። በኢየሩሳሌምም በከተማይቱ የሚያገኙትን ለማረድ ወጡ።

62 ከዚያ በፊት... እነሱ ወደ እርድ ሲወጡ፡ ቆም አሉ፡ በፍታ የለበሰ ሌላ መጣና፡ አስቆማቸው፡ በወገቡም የጸሐፊም ቀለም ቀንድ ይዞ ነበር፡ (ያን ስንቶች እንብባችሁታል? ) ሕዝቅኤል 4 ላይ። ከዚያም በፍታ ለብሶ፡ የጸሐፊም ቀለም ቀንድ በወገቡ የያዘ ሰው፡ እንዲህም አለ፡ "የእግዚአብሔርን ባሪያዎች በግምባራቸው እስኪታተምባቸው ድረስ፡ ወደ ከተማይቱ አትግቡ ማንምም አትረዱ።" እርሱም ወጣ እና አተማቸው፡ እንዲህም አለ፡ ሕጻናትን እና ሌሎችም፡ አተማቸው።

63 ከዚያም ማረጃ ስለት የያዙትን፡ አራቱ እነሆ መጡ፡ ያለ አንዳች ርህራሄ፡ ገብተው ፈጽመው አጠፏት። ወንዶችን፡ ሴቶችን፡ ሕጻናትን ጨፈጨፉ፡ የዚህ ፊተኛው የጸሐፊም ቀለም ቀንድ ይዞ የሚያትም ሰው ማኅተም የሌላቸውን ሁሉ አረዷቸው። እና ታላቁ...

64 እንግዲህ ጌታችን በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 24 ላይ፡ ካስጠነቀቃቸው በኋላ ባሉ ቀናት ይህ ሆነ፡ ምን ነበር "ኢየሩሳሌም በሠራዊት ተከባ ሰታዩ፡ ከ... ከጣራ ላይ አትውረዱ፡ ወይም በእርሻ ያለው ወደ ይሁዳ ይሂድ እንጂ፡ ልብሱን ለመውሰድ አይመለስ።" ጆሴፈስ እንዴት እንደሸሹ፡ ጽሑፉን አሰፍሮታል። የጌታ ኢየሱስ ቃል የተቀበሉ ሁሉ ያመለጡትም እነሱ ብቻ ናቸው። በ 96 **ዓ.ም**.፡ ሰራዊቶች፡ እና እነ ቲቶ ከበዋት ባዩ ጊዜ፡ ቲቶ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ከበባት በዚያም አጠረባቸው፡ ያን ሲያዩ የዛፍ ቅጠል መብላት ጀመሩ... የዛፍ ቅርፊት—ቅርፊት በሉ፡ የምድር ሣር በሉ፡ እርስ በርስ ልጆቻቸውን ቀቅለው በሉ። በረሃብ ቀጧቸው፡ ዘጋግተው አቆዩአቸው፡ በመጨረሻም ደማቸው ደጅ አልፎ እስኪፈስ ድረስ ገብተው ሁሉንም አረዷቸው—እንደሚፈስ ገንዳ ወረደ፡ የደም ጎርፍ ደጁን አልፎ ፈሰሰ። ቤተ መቅደሱን አቃጠሉ፡ ግንቡን ሁሉ አፈራረሱ፡ እስከ ዛሬ ድረስ በዚያ አለ።

65 መቅደሱ በነበረበት ሰፍራም ኦማር መሰጊድ አሁን ቆሟል። ኢየሱስም ስለዚህ ነገር በማቴዎስ 24 ላይ ተናግሯል፡ እንዲህ አለ፡ "ጥፋትን የሚያመጣውን ርኩሰት በተቀደሰ ሰፍራ ቆሞ ሰታዩ፡ ስለዚህ ነገር፡ ነብይ ዳንኤል እንዳለው፡" በቅንፍ ውስጥ፡ እንዲህ ብሏል፡ "(አንባቢው፡ ያስተውል፤)" እያችሁ፡ "በተቀደሰው ሰፍራ፡ ይህ እርኩሰት የኦማር መሰጊድ ርኩሰት ቆሞ ሰታዩ።" ዛሬም በተቀደሰው ሰፍራ በትክክል ቤተ መቅደሱ በነበረበት ቦታ ላይ፡ ይህ መሰጊድ ቆሟል። ኢየሱስ ይሆናል እንዳለው የመሐመዳውያን መሰጊድ ቆሟል፡ አዎን፡ ዳንኤል አሰቀድሞ ይሆናል ያለውን፡ ኢየሱስም እንዲሁ እንዲሆን አረጋግጧል።

66 ነብያት እና እግዚአብሔር እነዚህ ነገሮች እንደሚፈጸሙ በትንቢት ሲናገሩ ተመልከቱ፡ ወንድሜ ሆይ፡ በዘመን ፍጻሜ እንዳለን በማወቃችን ብቻ በአንገታችን ጀርባ ያለውን ጸጉር እስኪቆም ድረስ ሊያደርሰን ይገባል። መጨረሻ ላይ ነን! ምንም የቀረ ነገር የለም። ይሆናል ብሎ እንደተናገረላቸው እየተፈጸሙ ይገኛሉና፡ ይህም፡ ሊያበረታን ይገባል፡ እንዲሁም ሊያዘጋጀን ይገባል። እንዲህ አለ፡ ኢየሱስ እንዲህ በማለት፡ አሰጠንቅቆናል፡ "እነዚህ ነገሮች ሲፈጸሙ ሰታዩ፡" ማለትም አሁን እንደምናወራው፡ "አይናችሁን አንሰታችሁ፡ ቤዛችሁ እንደቀረበ ተመልከቱ፡" ብሎናል።

67 ዓለም ሁሉ ብናተርፍሰ ምን ይጠቅመናል? እንዲሁ፡ እንደምናጣው የታወቀ ነውና። በዛ—መልኩ ማሸነፍ አንችልም። ማሸነፊያው አንድ ብቻ ነው፡ እርሱም በክርሰቶሰ ነው። ክርሰቶሰን ያዝ፡ ያኔ ሳትወድ በግድህ ባለ ድል ትሆናለህ። ከዚህ መውጣታችሁ ግድ ነው፡ ይህ ጉባኤ ከማለቁ በፊት ልትሞት ትችላለህ፡ ጸሐይ ከመጥለቋ ዛሬ ልትሞት ትችላለህ፡ እንዲሁም እ-... ጠዋት ከመውጣቷ በፊት ልትሞት ትችላለህ፡ ከቀጣይ እሁድ በፊት ልትሄድ ትችላለህ፡ ሁላችንም እንዲሁ። መቼ እንደምንሄድ አናውቅም፡ መሄዳችሁ እንደማይቀር ግን ታውቃላችሁ። ታዲያ ይሄን ለማለፍ መሞከር ሞኝነት

አይደለምን? እየ—እየተቅበዘበዛችሁ፡ ከሞት ጋር እየ—እየተሽኮረመማችሁ ነው።

68 ልክ ተቦጋን እንደሚባለው ተንሸራታች መጫወቻ። ተቦጋን ላይ ተሳፍረው ዙርያውን እንዲህ ይዞሩታል፡ ምን ያህል ጫፍ እንደሚደርሱ ተመልከቷቸው፡ ገና ምንኑም ሳያውቁት፡ በድንገት፡ ዘው ብለው ይሄዳሉ። እናንተ የምታደርጉትም እንዲሁ ነው፡ ዙርያ ዙርያውን መንሸራተት። በየትኛው ደቂቃ ምናችሁ እንደሚቆጣ አታውቁትም፡ ወድያው ትወሰዳላችሁ፡ የልብ መቆም፡ የመኪና አደጋ፡ ማንኛውም ነገር ይከሰትና፡ ትሞታላችሁ። ከዚያም የዘላለም መዳረሻችሁ ፊት ለፊታችሁ ይጋረጥባችኋል። ወዳጄ ሆይ፡ አስብበት።

69 "አሁን፡ የጥፋትም ርኩሰት በተቀደሰው ስፍራ ስታዩ።" እንግዲህ፡ ያኔ፡ ኢየሱስ ከሄደ በኋላ ቲቶ በመጣበት ዘመን፡ ያ የጸሐፊም ቀለም ቀንድ በወገቡ የያዘ ሰው መንፈስ ቅዱስ ነበረ። በኢየሩሳሌምም አለፈና በሕዝቡም ላይ ምልክት አደረገ። እና አሁን የቤተ ክርስቲያን አባላት ሆይ፡ አንድ ነገር እንድታስተውሉ እፈልጋለሁ። መንፈስ ቅዱስ ተሞልቻለሁ ትላላችሁን? "በከተማይቱ ውስጥ ስለተደረገው ርኩሰት ከሚያለቅሱትና ከሚያዝኑት በቀር ለማንም ማህተም አታድርግ፡" አለ። አሁን፡ እንግዲህ ስለ አለም እና ስለሁኔታዎቿ ሽክም የተሰማው ሰው የት አለ?

70 እንዴታ፡ "እኔ'ኮ ሜተዲስት ነኝ፡ እኔ'ኮ ባፕቲስት ነኝ፡ ፕረስባይተሪያን ነኝ፡ ታዲያ ምን ልዩነት አለው? " ይላሉ።

71 አቤት፡ ያ መልካምነት፡ ስለ ጠፉት ነፍሳት ሸክም አይደለም። ምንም ነገር እንዲነሳ እና በነፍሳችሁ ውስጥ ምሬትን እንዲዘራባችሁ አትፍቀዱ። ማንም ሰው ክፉ ቢሆንባችሁ የቱንም ያህል በመጥፎ ቢያስተናግዳችሁም፡ በፍጹም አትፍቀዱ! ያ ነገር በነፍሳችሁ ውስጥ እንዲሰካ በመፍቀድ ጥፋተኛ አትሁኑ። መንፈስ ቅዱስን እንዲያዝንባችሁ ያደርጋልና። በትክክል ያደርጋል።

72 ከሁለት ወይም ሶስት አመት በፊት ትዝ ይለኛል የተናገርኩት ስህተት ነበረ። ጠበቃው ደወለልኝና፡ ጠጋ አልኩኝ... ሚስቴም እዛ ቁጭ ብላለች። ጭንቅላቴን... እንዲህ አረግኩት፡ የተላከው... እየመጣ እንደሆነ ተሰማኝና፡ ወደ—ኋላ ተመለስኩ። ስልክ ላይ ደውለው—እንግዲህ "ዛሬ ከሰዓት እንዲመጣ ንገሪው፡" አሏት።

ሚዳም "ጠበቃው ነው፡" አለችኝ።

ከበሩ ወደ ውጭ ወጣ አልኩና፡ "እዚህ የለም በይው፡" አልኳት።

ምነው "ቢል!" አለችኝ፡

"አሁን እዚህ የለም በይው፡" አልኳት። እና ወደ ውጭ ወጣሁ።

73 ከዚያ ወደዚያ ወጣሁ እና በጣም መጥፎ ስሜት ተሰማኝ፡ እና ተመለስኩ። እርስዋም ነገረችው፡ እና ሲከፋት አየኋት።

74 ከዛ ለመጸለይ ወጣሁ... የታመመ ሕፃን ልጅ የነበረው፡ አንድ ሰው ወደዚህ መጥቶ ነበርና። እናም ለሕፃኑ ልፀልይለት እጄን መጫን ስጀምር፡ አንድ ነገር "አንተ ግብዝ ነህ፡" አለኝ። አያችሁ? "ያደረግካትን ታውቃለህ።"

75 እንዲህ አልኩት፡ “ጌታዬ፡ እኔ ለልጅህ ለመጸለይ አልበቃም። እነሆ፡ መንፈስ ቅዱስ አዝኖብኛል እጆቼን በህፃኑ ላይ ማድረግ አያስፈልግም። አንድን ነገር እስካስተካክል ድረስ ጠብቅ።”

76 ሄድኩኝ እና... ለጠበቃዬ፡ “እ—እጥፍቻለሁ” ብዬ፡ ነገርኩት።

“የሄድክ መስሎኝ ነበር፡” አለኝ።

“አይደለም፡” አልኩት። “ነገሩ እንዲህ ነው... ባለቤቴ የተሳሳተ ነገር እንድትናገር አደረኳት፡” አልኩት። “ይቅርታ—አርግልኝ፡ ያንን—ያንን ነገር ለማለት ፈልጌ—አልነበረም፡” አልኩት። አልኩትም፡ “ስላደረግኩት ነገር ይቅር ትለኛለህ? ”

ባለቤቴንም ይቅርታ ጠየቋት።

77 ሐምሌ ወር ነበረና፡ ወዲያው ወደ ግሪን ሚል ወጣሁ። አቤት፡ ጫካው እጅግ ጸጥ ያለ ነበር፡ እና ከሰዓት በኋላ ሙሉውን ጊዜ ዋሻ ውስጥ፡ በጸሎት አሳለፍኩ። ሄጄም እዚያ ባለው አለቱ ላይ ቆምኩኝ እና ኮረብቶቹን አሻግሬ አየሁ፡ በጣም ያምራል፡ በበጋ ወቅት፡ ከሰዓት አምስት፡ ወይም፡ ስድስት ሰዓት ይሆናል፡ ቅጠሎች እና ሌላው ሁሉ፡ ጸጥ ብሏል። ምንም ነገር የለም፡ ጸጥ ያለ፡ ሞቃት ቀን። እኔም “የሰማይ አባት ሆይ፡ አንድ ጊዜ፡ ሙሴን በዓለት ላይ አቆምከው እና በፊቱ አለፍክ፡” አልኩት። እንዲህ አልኩት፡ “ለሰራሁት ክፉ ነገር ይቅርታ አርገህልኝ እንደሆንክ፡ አሁን እንደገና አልፈህ እንዳይህ ትፈቅድልኛለህን? ” እና በኮረብታው በግራዬ በኩል ትንሽ አውሎ ንፋስ በቅጠሎቹ መካከል በቀላሉ መሽከርከር ጀመረ፡ **እንዲህ** እየተሽከረከረ አጠገቤ ድረስ መጣና በጫካዎቹ መካከል አለፈ። በቃ ልክ እንደ ህጻን አለቀስሁ።

78 ተመልሼ ወረድኩና፡ “ኃጢአቶቼን አሁን ይቅር ተብያለሁ፡” አልኩኝ። አያችሁ?

79 አያችሁ፡ ሁል ጊዜ መራራ ስሮችን ከውስጣችሁ አስወግዱ። አያችሁ? ማንም ሰው ምንም ቢያደርጋችሁ፡ እንዲህ ይሁን... ክፉውን ሁሉ ከእናንተ የሚያርቅ አምላክ ከእናንተ ጋር ይሁንላችሁ።

80 እንግዲህ፡ እነዚህ የክርስቶስ ማስጠንቀቂያ የተቀበሉ ክርስቲያኖች፡ ዛሬ ጥዋት የምንናገርለትን የነገሩ ጥላ፡ አሁን ተመልከቱ። ማስጠንቀቂያውን የተቀበሉ ክርስቲያኖች፡ ይህ እንደሚሆን አውቀው ነበርና ከኢየሩሳሌም ወጡ።

81 ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄያጆች ሰዎች፡ የቤተ ክርስቲያን አባላት የነበሩ ተመልከቷቸው፡ ቤተ ክርስቲያንን ተቀላቀሉና፡ ሁሉም እንዲህ አሉ፡ “እነሆ፡ ሰራዊት እየመጣ ነው፡ ጦርነት እየመጣ ነው፡ አሁንም እንሂድ ወደ እግዚአብሔር ቤት ገብተን እንጸልይ።” ይሁን እንጂ በጣም ረፈደባቸው። ምንም አልረባቸውም፡ አያችሁ።

82 ደቀ መዛሙርት ግን፡ ኢየሱስ የተናገረውን አውቀው፡ ማስጠንቀቂያው ላይ ተግተው ስለጠበቁ፡ አመለጡ። (የታሪክ ተመራማሪዎች “‘የሰው ስጋ በላዎች’ የሚባሉ” ይሏቸዋል፡ “ይህ ይፈውሳቸው የነበረውን ‘ኢየሱስ’ የሚሉትን ሰው—ስጋውን በሉት፡” አሉ። አያችሁ፡ ስለ ጌታ እራት ማለታቸው ነው። አልገባቸውም... ምን እንደነበረ አያውቅምና፡ አያችሁ፡ ስጋዊ ሰው ስለሆነ፡ አማኝ

አይደለም፡ ተራ የታሪክ ምሁር ነው። እርሱም... ) እነዚያ ግን በምድርም ላይ ከሚመጣው ቊጣ አመለጡ።

83 አሁን፡ እዩእት፡ ኢየሩሳሌም ሙሉ ለሙሉ ፈራረሰች። አሁን አንግዲህ... ይህ ከራዕይ 7 ጋር፡ ፍጹም ተመሣሣይ ነው። አሁን ተመልከቱ! ቲቶ ኢየሩሳሌምን ከከበባት ጊዜ ጀምሮ፡ በዓለም ውስጥ፡ እስከ 1914 ድረስ ዓለም በሙሉ ወደ ጦርነት የገባበት ጊዜ በታሪክ አልታየም። አሁን በደንብ አዳምጡ! አሁን ሚስተር ራዘርፎርድ ያዳለጠው እዚህ ጋር ነው፡ እዚህ ጋር እንደሆነ፡ እርግጠኛ ነኝ። አሁን ተመልከቱ፦

> **ከዚህም ነገሮች በኋላ** ሌላ መልአክ ቆሞ-... **አራት መላእክት በምድር በአራቱ ማዕዘን ቆመው አየሁ፡** (**ይህ** በአራቱ የምድር ማዕዘኖች ላይ፡ **እንደዚህ** የቆመ ነው።) **አራቱን የምድር ነፋሳት ያዙ፡** (አሁን፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ **ነፋሳት** ምን ማለት እንደሆነ ማንም ሰው ያውቃል፡ **ነፋሳት** ማለት “ጦርነት፡ ግጭት፡” የአየር ላይ አለቃ፡ ሰልጣን ዲያብሎስ ነው፡ አያችሁ።)... **ነፋስ... በምድር ቢሆን፡** ወይም... **በባሕር፡ ወይም በማንም ዛፍ** እንዳይነፍስ **አራቱን የምድር ነፋሳት ያዙ...**
>
> **እና... ሌላ መልአክ ከምሰራቅ** ሲወርድ **አየሁ** (ከዚያም ኢየሱስ ይመጣል)፡ **የሕያው እግዚአብሔር ማኅተም ነበረ፤** በግንባሩ፡ በእጁም፤ **በታላቅ ድምፅም ወደ አራቱ መላእክት ጮኸ፡** ዓለምን ሊያጠፉ የነበሩ፡ እንዲህ አላቸው፡ እነዚያም... ባሕርንና **ምድርን ሊጎዱ ተሰጣቸው፡**
>
> **የአምላካችንን ባሪያዎች፡** ግምባራቸውን **እስክናትማቸው** ድረስ፡ **ምድርን ቢሆን፡ ወይም ባሕርን ወይም... ዛፎችን አትጉዱ፡ አላቸው።**

84 አ ሁን፡ በእግዚአብሔር ዘንድ ጊዜ የለም፡ የእሱ ዘለአለማዊነት ነው። እኛ በጊዜ እንለካለን፡ የምናውቀው ብቸኛው ነገር ኢንች እና ካሬ፡ እና ማይሎች፡ እና የመሳሰሉት ናቸው። እግዚአብሔር ዘላለማዊ ነው፡ መጀመሪያም መጨረሻም የለውም። አያችሁ፡ እሱ—ዘላለማዊ ነው።

85 አሁን፡ በ1914 መላው ዓለም ለዓለም ጦርነት ወደ ጀርመን እየዘመተ ነበር፡ እውነት ነው፡ መላው ዓለም ወደ የዓለም ጦርነት ዘመተ። አስተውላችሁታልን? በእርግጥ እንግዳ ነገር ነበር።

86 እነዚህን ግልጽ እንዲያደርጋቸው፡ ጥሩ ወዳጄ እዚህ ጋር ተቀምጧል፡ የወንድም ውድ አባት ነው። አያችሁ፡ ሁሉም ዘመቱ... አያችሁ፡ የተለወጠ ጅሆቫ ዊትነስ ነው።

87 እናም ያኔ እነዚህ ሁሉ፡ ወደ ጦርነት ዘምተው ነበር። በደንብ ታስታውሱታላችሁ፡ በ1914 ነው። አሁን፡ አይገርምም ወይ (**በዘ ዲክላይን ኦቭ ዘ ወርልድ ዋር ላይ፡** ዕትሙ አለኝ፡ ሁለተኛው ዕትም ላይ፡ በገጽ አርባ-አራት) ያንን ጦርነት ማን እንዳሰቆመው እስከ ዛሬ ድረስ አያውቁም! ኬይሰር ዊልሄልም ምንም አይነት ትዕዛዝ አላስተላለፍኩም ብሏል። በድንገት ግን፡ ቆመ፡ እና ለምን እንደሆነ ማንም አያውቅም። ሲዋጉ ቆዩ፡ እነሆም... ፊት

ለፊት፡ እና... ሁሉም መጡ፤ “ሁሉም ነገር አለቀ፡ ጦርነቱ አበቃ።” እና ምን እንደተፈጠረ ሳያውቁ፡ አሰቀድመው የሰላም ሰምምነት ተፈራርመዋል።

88 እንግዲህ፡ በርግጥ፡ ይሄን ሁሉ ለመግለጽ ሁለት ሶሰት ቀን ይፈጃል። አላወቁም ነበር፡ ብቻ ጠርሙሱን አሰቀምጠን ከፍ ከፍ ያሉትን እንዳሰሰ። ቃሉን ይፈፅም ዘንድ፡ ያቆመው እግዚአብሔር ነው! ያቆመው ያንን መልአክ ነው። እነዚያ መላእክቶች የሚያርድ መሣሪያ ይዘው ወጡ (ምን? ) ዓለምን ሁሉ ለማጥፋት፡ ሌላ መልአክ ግን፡ “እንዴ ቆዩ! ይህን አታድርጉ፡ በመጀመሪያ፡ የአምላካችንን ባርያዎች ግምባራቸውን ማተም አለብን አለ።”

89 ያ ልክ በ1906፡ 1914 ላይ፡ በጴንጤቆሰጤ መለቀቅ አካባቢ ላይ ነበር፡ ያኔ ነበረ። ሰንቶቻችሁ ታውቃላችሁ? እነዚያን ቀናት የሚያሰታውሰ ከ-ድሮዎቹ ጴንጤቆሰጤ አማኞች የሆነ ሰው፡ እዚህ አለ? አዎን። ያ፡ በዚያ መጀመሪያ ዘመን፡ መንፈሰ ቅዱሰ ገና መውረድ ሲጀምር ሰዎችም መንፈሰ ቅዱሰን ይቀበሉ እና በልሳኖች ይናገሩ እና ለታመሙ እና ለሌሎችም ይጸልዩ ጀመር፡ ገና መሆን መጀመሩ ነበር፡ ወይም በእነዚህ በሁለቱ ዘመናት መካከል፡ ልክ እንደታዘዘው፡ ቤተ ክርሰቲያን እውነት ነበረች። ከዚያም በኋላ ጴንጤቆሰጤው የኃይማኖት ተቋም መመሰረት ጀመረ፡ አሴምብሊሰ ኦቭ ጋድ፡ ቸርች ኦቭ ጋድ፡ ወዘተረፈ፡ ልክ አሁን እየሆነ እንዳለ ሁሉም ወደየ ኢዝሞቻቸው ተወሰዱ። ሰለዚህ... ተመልከቱ፡ በዘምኑ ፍጻሜ ላይ ነን። ሁሉም የመጨረሻ ተሰፋቸው ተሟጠጠ፡ ነገር ሁሉ መጨረሻው ደርሷል።

90 አሁን፡ በእነዚህ፡ በአራቱ... እንዳሰተዋልነው፡ ነገሩ የቆመው—በኅዳር አሥራ አንደኛው ቀን፡ በአሥራ አንድ ሰዓት፡ በዓመቱ አሥራ አንደኛው ወር፡ በወሩ አሥራ አንደኛው ቀን፡ በቀኑ አሥራ አንደኛው ሰዓት ላይ ነበር። በዚህ ጉዳይ ኢየሱሰ የተናገረውን ታሰታውሳላችሁ? “አንዱ ወደ ወይኑ አትክልት ሥራ አንድ ሰዓት ላይ ገባ፡ አንድ ሳንቲም ተቀበለ፡ ሌላውም ሄደ፡” የአሥራ አንደኛው-ሰዓት ሰዎች መጡ። ልክ ነው? በዚያም፡ ኋለኞች ሆነው የነበሩ፡ የአሥራ አንደኛው-ሰዓት ሰዎች ናቸው። አሁን ግን የሚገቡበት ጊዜ ደረሰ፡ ከእነዚያ ከአይሁዶች ዘንድ፡ አገር ለመሆን እየተሰበሰቡ ይገኛሉ። ኢየሱሰ በምድር ላይ እንዳለ እንኳ ሰለ አዲሰ ኪዳንም ሆነ፡ ሰለ ምንም ነገር ኢያውቁም ማወቅ በማይችሉባቸው በኢራን እና በተለያዩ አገሮች፡ ወደ ሩቅ ወርደው በአለም ላይ ተበታትነው ነበር።

91 አሁን ግን ወደ አገራቸው እየተመለሱ መሆናቸውን የሚያሳይ ምሰሎች፡ **ከሉክ** መጽሄት፡ **ከላይፍ** እና ከመሳሰሉ መጽሔቶች መመልከት ትችላላችሁ። ኢየሱሰ እንዲህ አላለምን? “በለሰም ሰታቆጠቁጥ ጫፍዋ ሲለሰልሰ ሰታዩ”? የበለሰ ዛፍ ማለት ሁሌም አይሁዶች ናቸው። “ይህ ሁሉ እሰኪፈጸም ድረሰ ይህ ትውልድ አያልፍም።” አሁንም ተመልሰዋል፡ አገር ሆነዋል፡ የራሳቸው ሰንደቅ እና የራሳቸው ገንዘብ አላቸው፡ ሁሉም ነገር አላቸው፡ በ U.N. ውሰጥ፡ እውቅና አግኝተዋል። ተረጋግታለች! ዝግጁ ነች! ዝግጁ ማለት፡ ለምን? የመቶ አርባ-አራት ሺህ መታተም (አሁን፡ በአንድ ደቂቃ ውሰጥ እንመለሰበታለን።) እነዚያ በዋል ሰትሪት ዘወትር የሚያታልሉትን እና የሚዘርፉትን ቡድን ሳይሆን፡ የእሰራኤልን፣ የአይሁድን፡ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት የሚጠብቁ እውነተኛ አይሁዶች፡ ንጹሕ፡ እና እውነተኛ አይሁዶች ማለቴ ነው።

92 አሁን፡ እውነተኛዎቹ አይሁዶች፡ ልክ ነቢዩ እንደተናገረው እንደገና ወደ

ፍልስጤም እየተሰበሰቡ ነው፣ እስማኤል እና ይስሐቅ እንዳቸው በሌላው ጉሮሮ ውስጥ ሆነው፡ ሁል ጊዜ ሲጣሉ እንደኖሩ፡ በመጨረሻው ቀን እንደሚገናኙ ትንቢት ተነግሯል፡ እነሆም አብረው ተቀምጠዋል። እስማኤል እዚህ ጋር፡ የአንዲት መንደር ርቀት ላይ ይስሓቅ እዚያ ተቀምጠዋል፡ ሁለቱም (ሙሐመድና አይሁዶች) በ-ባዶ-መሬት እርስ በርስ ይጣላሉ።

93 አሁን ይህ ያለን መልእክት ከሱ ጋር የተገናኘ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለማየት። እስራኤል እንደ ሕዝብ አገር ለመሆን የፈረመችበት ሰዓት ላይ፡ በዚያች ሰዓት ላይ፡ በዚያች ቀን፡ በዚያች ወር፡ ሁሉ ሲሆን፡ በግሪን ሚል፡ ኢንዲያና ነበርኩ፡ ያን መልአክም ተገለጠልኝና ይህ መልእክት ይዤ እንድወጣ አዘዘኝ፡ በወንዙ ላይ ካገኘኝ በኋላ እና የሚሆነውን ከነገረኝ በኋላ፡ ከዚያም ከአስራ አንድ አመት በኋላ እስራኤል እንደ ሀገር በፈረመችበት ሰአት ተልዕኮ ሰጠኝ። ሁሉም አንድ ላይ የተያያዘ ነው።

94 አያችሁ፡ የጌታ መልአክ አሁን በምድር ላይ አለ፡ አያችሁ፡ ለጌታ መምጣት ሁሉንም ነገር እያስተካከለ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ወደ ሰዶምም ወርደው በዚያም የገጠማቸውን ኃጢአት የሰሙ መላእክት እነዚያ ናቸው... ወርደውም “የሰማነው ነገር፡ እንደሰማነው እንደሆነ ለማየት ወርደናል፡” አሉ።

95 ታስታውሳላችሁ? መልአኩም ወረደ... (አንደኛው ከተመረጠው ከአብርሃም ጋር ቆየ።) ሶዶምም **እዚህ** ጋር ነበረች፡ ሎጥም በሶዶም ነበረ፡ ሁለት መላእክቶች ወደዚያ ወርደው ሰበኳቸው ያቺን ታናሽ፡ ሰነፏን ድንግል፡ ታናሺቱ መንጋ ይዘዋት ወጡ። አያችሁ? በጣም ጥሩ። (አንደኛው መልአክ ግን ከአብራሃም ጋር ቆየ።) እነዚያ መላእክቶች፡ እነ ዘመናዊው ቢሊ ግራሃም እና ሌሎቹ **እዚህ** ጋር ሰብከው፡ አሰወጧቸው።

96 ከአብርሃም ጋር የቆመው መልአክ ግን ጀርባውን ወደ ድንኳኑ ሰጠና፡ እንዲህ አለ፡ “አብርሃም፡ ሚስትህ ሣራ፡ ወዴት አለች? ” ያገባች፡ ያገባ እንደነበረ እንዴት አወቀው? ሚስት እንዳለውስ እንዴት አወቀ? ስሙንስ እንዴት አወቀ፡ ስሟ ሳራ እንደነበረ እንዴት አወቀ? “ከኋላህ ባለው በድንኳኑ ውስጥ ናት፡” አለው።

97 እሱም እንዲህ አለው፡ “እነሆ፡ እኔ ቃል እገባልሃለሁ።” “እኔ፡” መልአኩ ማን እንደነበረ እዩት፡ “እኔ ቃል እገባልሃለሁ። የዛሬ ዓመት እጎበኝሃለሁ፡ ሳራም ይህን ወንድ ልጅ ትወልዳለች።”

98 ሣራም፡ ከኋላው በነበረው ድንኳን ውስጥ ሆና፡ በውስጧ ሳቀች። መልአኩም፡ ጀርባውን እንደሰጠ፡ “ሳራ ለምን ሳቀች? ” አለው፡ ለተመረጠች ቤተክርስቲያን የሚሰጠውን ምልክት አያችሁት?

99 በሰዶም የነበሩትን ያገኙትንስ ምልክትስ አያችሁትን?

100 እነሆ አሁንም ሶስት አይነት ምድቦች እናያለን፡ እንደገና ወደ እነሱ ተመለስን።

101 አሁን ያሉትን... ዓለምን በሙሉ የሸፈኑ እነዚህ ታላላቅ አገልጋዮች። ቢሊ ግራሃም መንፈስ ቅዱስን ከተቀበለ በኋላ፡ **ወደዚህ** መውጣት አልቻለም። ዕጣው **እዚያ** ማዶ ነው እርሱም አውቆታል፡ እግዚአብሔርም በዚያ አቆየው። አያችሁ? በዚያ ምሁራዊ አሰባበክ፡ እዚህ በሚሰማው ነገር፡ ሶዶምን ለመገሰጽ

ይጥራል፡ ለመገሰጽ ይጥራል፡ ወይም ለሰነፏ ድንግል ጸጋን ለመስጠት። አያችሁ?

102 **እዚህ** ግን አብርሃምና መደብ ነበሩ፡ ኢየሱስም እንዲህ አለ፡ "በሰዶም ዘመን እንደ ነበረ፡ እንዲሁ በሰው ልጅ መምጣት እንዲሁ ይሆናል።"

103 እነሆ፡ እነዚያ መላእክት አሁንም በምድር ላይ ተመሳሳይ ነገር ያደርጋሉ። አያችሁ፡ ቢሊ ወደ ባፕቲስቶች እና ወደ ሌሎች እየሄደ ያለበት ምክንያት ይህ ነው። ግድ ይለዋል! አያችሁ፡ እነ ጃክ ሹለር እና እነዚያ ታላላቅ ሰዎች—ሰዎች የሪቫይቫል አድራጊዎች... ሁሉ ጭምር ሄዱ፡ መሆንም አለበት—ምክንያቱ በከባድ እየገሰጿቸው ነውና። በነሱ መካከል ተአምራት አድርገው አያውቁም፡ ጥቂቶችን፡ የሰዎች አይን ያሳውራሉ። ወንጌልን መሰበክ ግን ዓይነ ሰውር አደረጋቸው፡ አያችሁ፡ መጽሐፍ ቅዱስም ይላልና።

104 **ይህ** ሌላኛው ሰው ግን በአብራሃም እና በመንጋው፡ ማለት በተመረጠችው-ቤተክርስቲያን ፊት፡ ምልክት፡ መለኮታዊ ምልክት ያደርጋል።

105 አሁን፡ 1914፡ ዓለም ወደ ጦርነት ገባች፡ እና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሰላም ሆነው አያውቁም፣ ያለማቋረጥ መወዝወዝ፡ መወዛወዝ፡ መወዛወዝ፡ አሁንም ተመሳሳይ ነገር እያደረጉ ይገኛሉ። እና ምን እያደረጉ ነበር? "ያዝ አድርጎታል!" አምላክ ሆይ፡ ማረን! ያንን በራእይ ያየሁት (ነገርን ሁሉ የሚያጠፋ) ታላቅ ነገር ያዝ ተደርገዋል፡ አቶሚኩ ያዝ ተደርገዋል፡ አጥፊ መጥቶ እራሱን እስኪያጠፋው ድረስ እራሳቸውን እንዳይጠፋፉ ጦርነቶች ያዝ አድርጓቸዋል፡ ይህም እስራኤል ተመልሣ እራሷን አንድ እስክታደርግ ድረስ፡ እና መልእክቱ ወደ እርሷ ገብቶ እስራኤል በመንፈስ ቅዱስ ማኅተም እስክትታተም ድረስ ነው። አያችሁ፡ አሕዛብ ከተጠሩ በኋላ፡ ስለ ስሙ የሚሆነው ህዝብ ደግሞ ይጠራል፡ እነርሱም **እዚህ** ጋር ባለው ዘመን ይጠራሉ። ከዚያም እስራኤል ለሶስት-አመት-ከ-ስድስት-ወር ብቻ መልእክት ትቀበላለች።

106 ዳንኤል እንዲህ ይሆናል፡ ይሆናል፡ እንዳለው፡ ስለ ሰባው፡ ኧህ፡ ወይም፡ ወይም፡ "አይሁድ መዳን ይሆንላቸው ዘንድ፡ ሰባት አመታት እንደቀረ ትንቢት ተናገረ።" እንዲህ አለ፡ "መሲሕ፡ እርሱም ልዑል፡ ክርስቶስ፡ በሰባው ዓመት መካከል... ሰባት አመት መካከል መጥቶ ትንቢት ይናገራል፡ ከዚያም ይቆረጣል።" ኢየሱስም መጥቶ ለሦስት ዓመት ተኩል ሰበከ ተቆረጠም፡ ዳንኤልም እንዳለው የዘወትሩ መሥዋዕት ተወገደ። በጣም ጥሩ።

107 ከዛ ጊዜ በኋላም ለአሕዛብ ጊዜ ተሰጣቸው፡ እስከዚህ ዘመን ድረስም ደረሱ። አሁንም ለአይሁዶች የቀረላቸው ሦስት ዓመት ተኩል አለ። አሁን ወደ ራዕይ 11 ከሄድን፡ መጨረሻ ላይ በትክክል እንገነዘበዋለን (ቤተክርስቲያን እስከ ራዕይ ምዕራፍ 19 ድረስ አትታይም።)፡ የዚያ ፍጻሜ ግን፡ ኤልያስና ሙሴ ተመልሰው እንደገና ለአይሁድ ይሰብካሉ። በዚያ መንፈስ የተቀቡ ሁለቱ ሰዎች፡ ምናልባትም እነዚህ ሁለቱ፡ አልሞቱም ይሆናል። ገድለውም ጌታችን በተሰቀለበት **ሰዶም** "እየሩሳሌም፡" በምትባል ጎዳና ላይ ጣሉአቸው። ከሦስት ቀንም በኋላ፡ እነሆ፡ ሕይወት (የሕይወት መንፈስ) ገባባቸውና ተነሡ፡ ወደ ላይም ተወሰዱ። በዚያን ጊዜም የምድር አንድ ሦስተኛ ያህሉ ተበታተነ። ከአይሁድ ጋር ተአምራትንና ምልክትን አደረጉ።

108 እንግዲህ ሊሰብኳቸው የወጡትን አይሁዶች እነሆ እነዚህ ናቸው። ዓለማት ሁሉ... አይችሉም... አንዱ ሌላው ላይ መተኮስ ወይም መገዳደል፡ ወይም ጥፋት ሊመጣ አይችልም፡ ይህም እነዚያ አይሁዶች ወደዚያ ሰፍራ እስኪደርሱ ድረስ ነው፡ መጽሐፍ ቅዱሰም እንዲሁ ያስቀምጠዋልና፡ አራት መላእክቶችን አየ። ምን መቀበል እንዳለባቸው አሁን ተከታተሉ፡ ልክ እንዳደረጉት መቀበል ያለባቸው መንፈስ ቅዱስ ነው።

109 ያ የቀለም ጸሐፊ ቀንድ የያዘው ሰው መንፈስ ቅዱስ ከሆነ፡ (ሁሉም ሰው፡ መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚያነብ፡ እንገነዘባለን።) እንግዲህ፡ ይህ መልአክ "ከሕያው እግዚአብሔር ማኅተም፡" ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተመልሶ ይመጣል። ኤፌሶን 4፡30፤ "... የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ... እስከ ቤዛችሁ ቀን ድረስ የታተማችሁበት።"

110 ስለዚ እነዚያ አይሁዶች እስኪመለሱ ድረስ ምንም ማድረግ አይችሉም። እና ከጥቂት ሳምንታት በፊት ሁሉንም ነገር አንድ ላይ ከፋፍለው በU.N. ውስጥ ተሰብሰበዋል ተዘጋጅተዋል! መጨረሻ ላይ ነን፡ አሁን ሁሉም ነገር ታትሟል።

111 አሁን፡ አሁን ተከታተሉ፡ አይሁዳውያን መሆናቸውን ለማረጋገጥ፡ አሁን፡ እነዚህን እወሰዳለሁ፦

> ምድርን፡ ወይም **ባሕርን፡ ወይም ማንኛውንም ዛፍ አትጉዱ፡ አላቸው፡ የአምላካችንን ባርያዎች** በግምባራቸው **እስክናትማቸው** ድረስ።

112 አሁን፡ ይህ ራዕይ ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ፡ ይህንን 4ኛውን ቁጥር፡ ይህን ተመልከቱ፦

> **ቁጥራቸውንም ሰማሁ... የታተሙትን፤ የታተሙትንም ቍጥር ሰማሁ ከእስራኤል ልጆች ነገድ** ሁሉ **የታተሙት መቶ አርባ አራት ሺህ** ነበሩ**።**

113 "እስራኤላውያን።" የት አሉ? አሁን ተሰብሰበዋል። የማኅተም ጊዜ እስኪመጣ ድረስ እየጠበቁ፡ ተዘጋጅተው እዚያ ናቸው። "ከይሁዳ ነገድ አሥራ ሁለት ሺህ ታተመ። የሮቤል ነገድ፡ አሥራ ሁለት ሺህ። የጋድ ነገድ፡ አሥራ ሁለት ሺህ። አሴር፡ አሥራ ሁለት ሺህ። ንፍታሌም፡ አሥራ ሁለት ሺህ።" እያለ ይቀጥላል፡ ሰምዖን እና ኦህ፡ እስከ... ብንያም ድረስ፡ አስራ ሁለቱ ነገድ ይደርሳል። አሥራ ሁለት ጊዜ አሥራ ሁለት መቶ አርባ-አራት ሺህ ነው። አያችሁ? አሁን ያ ነው...

114 አሁን ለአፍታ ያህል፡ እነሆ፡ 14ኛውን ምዕራፍ ከተመለከታችሁ፦

> **አየሁም፡ እነሆም፡ በጉ** በጽዮን **ተራራ ቆሞ ነበር፡ ከእርሱም** ጋር**... መቶ** አርባ-አራት **ሺህ ነበሩ፡ የአባቱ ስም** በግምባራቸው **ተጽፎ ነበር።**

115 "ሲና ተራራ።" በጉ ከንጥቀት ተመልሶ መጥቷል ማለት ነው። እነሆ ተመለስ፡ ዮሴፍ ከወንድሞቹ አጠገብ በቆመ ጊዜ አሕዛብን ሁሉ ማሰናበቱን፡ በቀደም ማታ እንዳየነው፡ "እኔ ወንድማችሁ፡ ዮሴፍ ነኝ!" አላቸው እነርሱም ፈሩ።

116 ባለፈው በቤተ ክርስቲያን ዘመን ላይ፡ መቼ እንደሚመለስ የተማርነውን ታስታውሱታላችሁ? እጆቹን የወጉትም እንኳ፡ "እነዚያን የሚስማር ጠባሳዎች ከወዴት አገኙህ፡" በማለት ይጠይቁታል?

117 እርሱም "በወዳጆቼ እጅ፡" በማለት ይመልስላቸዋል። እነርሱም ያዝናሉ። እና እያንዳንዱ ቤተሰብም አንዱን ከሌላው ተለይተው፡ ያለቅሳሉ ያለቅሳሉ ያለቅሳሉ፡ ይህም ክፉ ነገር ሰላደረጉ ነው። በአምላካቸው ላይ፡ በገዛ መሲሃቸው ላይ። እርሱም ዮሴፍ ለእስራኤል... ልክ እንደተናገረው—ይናገራቸዋል፡ እንዲህ በማለት፡ "በራሳችሁ ላይ አትቆጡ፡ እግዚአብሔር ይህን ያደረገው ሕይወትን ለማዳን ነውና።"

118 "እግዚአብሔርም... " ይህን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ ነው "አሕዛብ ዕድል እንዲያገኙ እግዚአብሔር የአይሁድን ዓይን አሳወረ (እኛን፡ ደግሞ)፡ ሰለ ሰሙ አንድን ሕዝብ ሙሽራይቱን፡ ከአሕዛብ ያወጣ ዘንድ ነው።" አቤት፡ ደሰ ሲል! አይደል? ይኸው እንግዲህ።

119 ይሄውላችሁ እንግዲህ መቶ አርባዎቹ-... አሁን ሙሽራይቱ ከዚያ በኋላ ሰትመጣ ማየት ከፈለጋችሁ፡ መቶ አርባ-አራት ሺህ ሙሽራ አለመሆናቸውን ለማሳየት፡ ከ 8 ኛው ምዕራፍ ጀምራችሁ ወደ ታች ማንበብ ቀጥሉ፡ ወይም፡ አዎን፡ 8ኛ ምዕራፍ፡ ማለት 8ኛው ቁጥር፡ ከ 7ኛው ምዕራፍ፡ ማለቴ ነው። በ 9ኛው እንጀምር—9ኛ ቁጥር፡ ምክንያቱ 8—8ኛው ቁጥር የብንያም መታተም ነው፡ አሥራ ሁለት ሺዎቹ።

> **በኋላ—ከዚህ በኋላ አየሁ፡ እንዲሁም፡ እነሆ፡ ማንም ሊቆጥራቸው የማይችል፡ እጅግ ብዙ ሕዝብ፡** (እነኋት ሙሽራይቱ መጥቶች።) **ከሕዝብና፡... ከነገድ፡... ከወገንም፡ ከቋንቋም ሁሉ፡ እጅግ ብዙ ሰዎች፡ በዙፋኑና በበጉ ፊት ቆሙ፡ ነጭ** ልብሰም **ለብሰው፡ የዘንባባንም ዝንጣፊዎች በእጆቻቸው ይዘው ነበር፡**
>
> **በታላቅም ድምፅ እየጮሁ፡ በዙፋኑ ላይ ለተቀመጠው ለአምላካችንና፡ ለ በጉ፡ ማዳን ነው አሉ።**
>
> **... መላእክቱም ሁሉ፡ በዙፋኑና በሽማግሌዎቹ በአራቱም እንሰሶቹ** ዙሪያ **ቆመው ነበር፡... በዙፋኑም ፊት በግምባራቸው ተደፉ—ተደፉ፡ ለእግዚአብሔርም እየሰገዱ፡**
>
> **አሉም፡ አሜን፡** በረከትና፡... **ክብር፡... ጥበብም፡... ምስጋናም፡... ውዳሴም፡... ኃይልም፡... ብርታትም፡ ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ** ለአምላካችን **ይሁን፡ አሜን።**
>
> **ከሽማግሌዎቹም** አንዱ **ተመልሶ፡ እንዲህም** አለኝ፡ **እነዚህ ነጩን ልብሰ የለበሱ እነማን ናቸው? ከወዴትስ** መጡ?
>
> **እኔም ጌታ ሆይ፡ አንተ ታውቃለህ፡ አልኩት። አለኝም፡ እነዚህ ከታላቁ መከራ** የመጡ ናቸው፡ **ልብሳቸውንም አጥበው፡ በበጉ ደም አነጹ።**
>
> **ሰለዚህ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት** አሉ፡ **ሌሊትና ቀንም** በ**መቅደሱ ያገለግሉታል፡...**

[በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።] አያችሁ?

120 ሚስታችሁ ምን ታደርጋለች? ቤት ውስጥ ታገለግላችኋለች። ቁጭ ስትሉ፡ ምግብ ትሰጣችኋለች፡ ልብስ ትሰፋለች። አያችሁ፡ ቀንና ሌሊት በቤት ውስጥ ታገለግላችኋለች። አያችሁ? እነዚህም ደግሞ፡ ከሕዝብ ሁሉ የተውጣጡ፡ ከአሕዛብ፡ እርሷም ሙሽራይቱ፡ ቀንና ሌሊት ከእርሱ ጋር፡ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ይሆናሉ። ትናንት ማታ የተነጋገርነውን፡ ሁሉም አስታወሳችሁ?

> **... በዙፋኑም ላይ የተቀመጠው በእነርሱ ላይ ያድርባቸዋል።**
>
> **ከእንግዲህ ወዲህ አይራቡም፡ ከእንግዲህም ወዲህ አይጠሙም፤ ጸሐይ—ጸሐይም** ወይም **ትኩሳት ሁሉ፡ ከቶ አይወርድባቸውም።**
>
> **በዙፋኑ መካከል ያለው በጉ እረኛቸው ይሆናልና፡** ወደ **ሕይወትም** ውኃ **ምንጭ... ይመራቸዋልና፤ እግዚአብሔርም... እንባዎችን ሁሉ ከዓይናቸው ያብሳል።**

121 እነሆ፡ መቶ አርባ-አራት ሺዎቻችሁ (እስራኤል) የጌታን መምጣት በመጠባበቅ ይገኛሉ አሕዛብ ፍጻሜ እስኪገባ ድረስ፡ ሙላት እስኪሆን ድረስ ግን መግባት አይችሉም።

122 ምናልባት፡ አሁን የግል ጉዳይ በሆነ ነግር ልናገር፡ እንደምትረዱት፡ ተስፋ አደርጋለሁ። በስቶክሆልም፡ ሰዊድን የሚኖረው ሌዊ ፔትረስ፡ የፋይላደልፊያ አብያተ ክርስቲያናት፡ -የበላይ ኃላፊ፡ ለአይሁዶች አንድ ሚሊዮን መጽሐፍ ቅዱስ፡ ትንንሽ ኪዳኖችን በላከ ጊዜ። ከሰጦታዎቹ አንዱ፡ ከእርሱ ዘንድ ለእኔም ደርሶኛል። አይሁዳውያን ሁል ጊዜ ከኋላ ወደ ፊት ያነቡታልና፡ ስለዚህ ቋንቋ—ቋንቋቸው እንዴት እንደሆነ ታውቃላችሁ። እናም እነዚህን መጻሕፍት አንብበው፡ እንዲህ አሉ፡ “እሺ፡ ይህ ኢየሱስ መሲህ ከሆነ፡ እናም ሞቶ መንፈሱ በመንፈስ መልክ ከተመለሰ፡ የነቢዩን ምልክት ሲያደርግ እንመልከተው፡ ከዛ በኋላ እናምንበታለን።”

123 እንዴት ያለ ፍጹም ዝግጅት ነው! “ጌታ ሆይ፡ ጊዜው አሁን ነው። አሁን ጊዜው ነው፡ ይኸው ነው፡” በማለት አሰባለሁ። እና በአውሮፕላን ሄድኩ፡ ቢሊ፡ እኔ፡ እና ሎይስ፡ ተነሳን።

124 ወደ ህንድ እየሄድኩ ነበርና፡ እንዲህ አልኩኝ፡ “አሁን፡ ከሄድኩበት ስመለስ፡ ወዲያው ወደዚያ ገብቼ መልእክቱን በአይሁዶች ፊት አቀርበዋለሁ፡ በዚያም እነርሱን አውጥቼ፡ ‘እውነት ነው ወይ? ’ እላቸዋለሁ”

125 ሁላችንም እንደምናውቀው፡ አይሁዶች ሁልጊዜ ነቢያቶቻቸውን ያምናሉ። ምክንያቱም እግዚአብሔር መሲሑ ነቢይ እንደሚሆን ነግሮአቸው ነበርና፡ በዚህም ምክንያት ነቢያቶቻቸውንም ያምናሉ፡ እግዚአብሔርም አለ፡ “በእናንተ ዘንድ ነቢይና፡ ባለ ራእዩ የሆነ ሰው ቢኖር፡ እነሆም እርሱ... ከእርሱ ጋር እኔ በራእይ እና በሕልም እናግረዋለሁ። እና—እኔ ከእርሱ ጋር ነኝና፡ የሚናገረው ከተፈጸመ፡ እናንተ ሰሙት።” አያችሁ? “ይህ ካልተፈጸመ ግን፡ ከዚያ ነቢይ ጋር ምንም ግንኙነት አይኑራችሁ፡ ምክንያቱም እኔ—አይ—እኔ ከእሱ ጋር አይደለሁምና። እሱ የሚናገረው፡ ከተፈጸመ ግን፡ እኔ ከእርሱ ጋር ነኝና፡ እርሱን ሰሙት።” አይሁድም ይህን ያውቃሉ።

126 እኔም እንዲህ አሰብኩ፡ “ኦህ፡ ማይ! እንዴት ያለ ድንቅ ጊዜ ይኖረን ይሆን! አራት ወይም አምስት ሺህ ያህሉ ሰብስቤ እዚያ እቆማለሁ፡ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያነቡና እንዲህ እንዲሉም—አደርጋቸዋለሁ፡ ‘ይህ መሲህ ከሆነ፡ የነቢዩን ምልክት ሲያደርግ እንመልከተው።’” “እንዴት ያለ ድንቅ ዝግጅት ይሆናል!” የአረብ አውሮፕላን መሰመር ላይ የበረራ ሰዓት ከመጥራታቸው፡ ከሰላሳ ደቂቃ በፊት ትኬቴን በእጄ አዘጋጅቼአለሁ። ስለዚህ ግብፅ፡ ካይሮ ላይ ቆሜአለሁ፡ እናም እንዲህ ብዬ አሰብኩ፡ “እግዚአብሄር ይመስገን! በሁለት ሰአታት ውስጥ አይሁዶች በጴንጤቆስጤ ዕለት የተቀበሉትን ተመሳሳይ ነገር እንደሚቀበሉ፡ ያለ አንዳች ጥርጥር እርግጠኛ ነኝ።” እንዲህ አሰብኩ፡ “በዚያ ቆሜ እንዲህ እላቸው እሆን፡ ‘ሄዳችሁ በእናንተ ዘንድ ያሉትን ታላላቆች ሰዎችን ጥሩ፡ ወደዚህ አምጧቸውና፡ አሁንም እሱ መሲሕ ካልሆነ እዩ።’ እያችሁ፡ በተጨማሪም እንዲህ እላቸዋለሁ፡ ‘አሁን፡ አባቶቻችሁ ይህን መሲሕ በተቃወሙበት ምድር ላይ፡ እነሆ አሁን ተቀበሉት፡ እጆቻችሁን ወደ ላይ አንሱና መንፈስ ቅዱስን አሁን ትቀ—ትቀበላላችሁ።’ ያን ነገር እንዴ ከተቀበሉ… እነርሱ በሚኖርበት ክፍለ ዓለም ላይ ወንጌሉን ይሰብኩታል። ሽማግሌዎቻቸውን ጠርተው፡ የነርሹ ማዕከላዊ… ዋናውን፡ መሪዎች ያሉበትን፡ ይጀምሩታል።”

127 ና ድንገት የሆነ ነገር መጣና አሁን አትሁድ አለኝ፡ “ጊዜው አልደረሰምና፡ አሁን እንዳትሄድ።” ኧሃ-ሃም። ይየአሕዛብ ሙላት አልሆነም፡ እያችሁ፡ ቀናቸው አልተፈጸመችም።

“ኦህ፡” “ከራሴ መሆን አለበት፡” አልኩኝ።

128 እንደገናም ቀጠልኩበት፡ እና መቋቋም እስከማልችል ድረስ በጣም ተጫነኝ። ከመጋዘኑ በሰጀርባ ዞርኩኝና እራሴን ዝቅ አደረግኩ፡ ከዛ፡ “አባት ሆይ፡ የተናገርከኝ አንተ ነህን? ”

129 እርሱም “ሰዓቱ ገና አልደረሰምና፡ አሁን ወደ እስራኤል አትሂድ፡” አለኝ። በቃ ገባሁና፡ ትኬቴን ቀይሬ፡ እንደገና ቀየርኩት፡ በሌላ መንገድ ሄድኩ። እያችሁ፡ ሰዓቱ ገና አልደረሰምና።

130 ነገር ግን ከእነዚህ ቀናት አንድ ቀን መልእክቱ ወደ እስራኤል ይደርሳል፡ ይህ የሚሆነው ሰለ… በራዕይ 11 መሰረት፡ እግዚአብሔር ሙሴንና ኤልያስን ይልካቸዋል፡ ተአምራትንና ድንቅን የእግዚአብሔርንም ምልክት ያደርጋሉ። አሕዛብ እየጨረሱ ሳሉ፡ የጸጋው… የጸጋው ቀን ከአህዛብ ቤተክርስቲያን ይሸሻልና፡ የጴንጤቆስጤ ዘመን ይሄዳልና። የኃይማኖት ተቋማት ሁሉ እንዲሁ ይቀጥላሉ ምክንያቱ ከሰንፏ ድንግል ጋር እዚህ ጋር ይመጣሉና (ከአፍታ በኋላ ወደዚያ እንገባለን።)፡ ብቻ ግን በዚያ ምድብ ውስጥ ይመጣሉ።

131 እነርሱ ይህን ከፈጸሙ በኋላ፡ ያንን ሲፈጽሙ፡ አይሁዶች የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ይቀበላሉ በእነዚያም “ዝናብ አይዝነብ!” በማለት ሰማይ መዝጋት በሚቻልባቸው ወራት ሪቫይቫል ይሆናል፡ ሁሉንም ዓይነት ተአምራትን እና ምልክቶችን ያደርጋሉ። በመጨረሻም የሮማውያን የስልጣን ተዋረድ… አይሁዶች የአለም ሀብት ስለሚቆጣጠሩት፡ ስለዚህ የ— የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያንም ይህ ነገር ካለቀ በኋላ ከአይሁዶች ጋር ያለውን ስምምነት ያፈርሳል በዚያም እንዲህ ይሆናል… (በመካከላቸው

የተፈራረሙት ሰምምነት)፡ እርሱም ወደዚያ ይወርዳል፡ በድሮ ዘመን እንዳደረገው—እነሆ እግዚአብሔር ሰለ እነርሱ ይቆማል፡ ሰለ እሰራኤል ይዋጋል። በመጨረሻ ሁለቱን ነቢያት ይገድሏቸዋል፡ እናም በመንገድ ላይ ይጥሏቸዋል፡ ይተፉባቸዋል።

132 ልክ ከጥቂት ሳምንታት በፊት በጴንጤቆሰጤው አገልጋይ እና በሚስቱ እና በልጆቹ ላይ እንዳደረጉበት አይነት፡ የልጆቹ ትንንሽ ሆዳቸው፡ **እንዲህ** እሰኪሆን ድረስ አብጦ፡ በአጠገባቸው እያለፉ ሲተፉባቸው ነበር፡ ሳይቀብሩ ለሦሰት ወይም ለአራት ቀናት በጠራራ ፀሐይ ላይ ጥለዋቸዋል።

133 ተመሳሳይ ነገር ያደርጋሉ! መጽሐፍ ቅዱስ ተናግሯልና። በእነዚያም ተመሳሳይ ነገር ያደርጉባቸዋል። ይህንም ባደረጉ ጊዜም፡ ከሦሰት የመውደቅ እና የሞሞት፡ ቀናት በኋላ፡ የሕይወት መንፈሰ ወደ ሁለቱ ነቢያት ይመጣል ተነሥተውም ወደ ክብር ይወጣሉ። እና፡ ይህ ነገር ሲሆን፡ ያኔ ርችቶች መተኳኮሰ ይጀመራል። የዘመን ፍጻሜም ያኔ ይሆናል። መጨረሻዋም ያኔ ይሆናል።

134 ያ ከመሆኑ በፊት ግን፡ ከአሕዛብ ዘንድ፡ የተመትረጠች ሙሽራ... እንዳንዶቻችሁ በጠረጴዛው ላይ ተቀምጣችዋል፡ በእነዚህ ማለዳዎች አንድ ቀን፡ አንዱ ይወሰዳል፡ ሌላኛው ይቀራል። በሰተመጨረሻው ላይ "ምን ተፈጠረ? " ብላችሁ ትገረማላችሁ፡ መኪና ተሳፍራችሁ አንድ ላይ እየተጓዛችሁ፡ ከሰው ጋር እያወራችሁ ሳላልችሁ፡ ሚሰት ወይም ፍቅረኛ ወንበሩ ላይ ተቀምጣ ነበር፡ ድንገት መልሰ የለም፡ ተወሰዷልና። ወደ ማቃብር ቦታ ትሮጣላችሁ፡ እንዳንድ መቃብሮች ተከፍተዋል፡ ሌሎቹ ግን ዝግ ናቸው፡ "የቀሩት ሙታን ግን ለአንድ ሺህ ዓመት ያህል አልኖሩም።" አሰታውሱ፡ ያኔ አልቋል!

135 ምሰጢራዊ አመጣጥ ይሆናል፡ እንጂ ይህ መቼ እንደሚሆን አንድም ሰው አያውቀውም። ዝግጁ እንድንሆን እና እንድንነቃ ታዝዘናል። በምን ሰዓት እንደሚሆን አናውቅም። ምንም ቢሆን፡ ግን፡ **እነዚህን** ፊተኞችን እንዳቸውም ቢሆን አንቀድማቸውም፤ ምክንያቱ፡ ልክ ኢየሱሰ በሚታይበት ቅጽበት፡ ሁሉም ነቅተው ይነሣሉ። ሙታን ይሁን ህያው፡ ልዩነት አይፈጥርም።

136 ቀድመን ከእሱ ጋር አ—እንገናኝም፡ ከሁሉ በፊት እርሰ በርሰ እንተያያለን። መጽሐፍ ቅዱሰ፡ ኤፌሶን፡ 5ኛው ምዕራፍ፡ እንዲህ ይናገራል፡ "እኛ ሕያዋን ሆነን ጌታ እሰኪመጣ ድረሰ የምንቀር፡ እዚህ የምንቆይ፡ ያንቀላፉቱን እንቀድምም ወይም እንከለክልም።" በገዛ ደማቸው ማኅተም ያደረጉትን የተወደዱ ሁሉ... በገዛ ደማቸው ምሰክርነታቸውን አተሙ። "እንቀላፍተው ያሉትን እንቀድምም እንከለክልም፡ መለከት ይነፋልና።" የሆነ ነገር ይከሰታል፡ "የወንጌል **አንድን ነገር** ይሰማል፡" ይህም የመምጣቱ አዋጅ ነው። "በክርሰቶሰም የሞቱ አሰቀድመው ይነሣሉ። ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንቀረው እንለወጣለን።" በቆመበት፡ ለውጥ ሲመጣ ይታወቀዋል፤ ሸበቱ ሸሽቷል፡ የፊት መጨማደዱም የለም፡ በቅጽበት አይን፡ ሁሉም ተቀያይሯል። እና በመጀመሪያ የምንወዳቸውን ሰዎች እንገናኛለን፤ "እማማ፡ ፓፓ፡ ጓደኛዬ። አቤት፡ ሃሌ ሉያ፡ ተዘጋጅተናልና! ከዚያም፡ እንቀላፍተው ከነበሩት ጋር፡" ይላል መጽሐፍ፡ "ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር በደመና እንነጠቃለን።" የአመጣጡ ቅደም ተከተል ይህ ነው።

137 አቤት፡ ያን ሽማግሌ አባቴን ማየት! ኦህ፡ ማይ! በእምነት ተሻግረው የሄዱ የድሮ ወዳጆቻችን እናያቸዋለን፡ እናገኛቸዋለን። የእግዚአብሄርን መልካምነት እናያለን፡ ቀድመን እሱን ካገኘነው ግር ይለናልና፡ "እናቴ ድናለችን? እማዬ—እማዬስ ድል ነሳችን? እጅግ ሰብከናቸው ነበርና፡ ሞ—ሞክረናል። እሷ እዚህ ገባችን? አጎቴ ጆ እዚህ ገብቷል? ወ—ወንድማችን እዚህ ገብቷል? **አገሌ-እና-አገሌስ**?" እያችሁ? "ጌታ ሆይ፡ እንወድሃለን፡ እንወድሃለን፡ ግን…" አስቀድመን እርሰ በርሳችን እንተያያለን! ኦህ—ኦህ—ኦህ! ግር አይለንም፡ ሁላችንም እንገባለንና።

138 ቆመውም "አሜን፡ ክብር፡ ጥበብ፡ ውዳሴም፡ ኃይልም፡ ብርታትም፡" ማለታቸው አይገርምም።

139 ሃያ አራቱም ሽማግሌዎች አክሊላቸውን አውልቀው በምድር ላይ ወደቁ፡ ሁሉም በምድር ላይ ወድቀው ሰገዱለት።

140 ከእነዚህ ቀናት ውስጥ አንድ ቀን ከምድር ባሻገር፡ ወዲያ ማዶ፡ በምድር አድማስ ላይ፡ በጠፈር ውስጥ በአንድ ጥግ ላይ እንቆማለን፡ ወደ ሰማይ ገና አንገባም፡ ነገር ግን እሱን ለመገናኘት በአየር ላይ እንነጠቃለን።

141 ርብቃ በወሰነች ጊዜ፡ በፍጥነት፡ ከኤሊዔዘር ጋር እንደምትሄድ ወሰነች ያዕቆብን ለመገናኘት በግመል… ወይም ከዚህ በፊት አይታው የማታውቀውን፡ ባልዋ የ-ሆነውን ይስሐቅን ለመገናኘት ቸኮለች፡ እግዚአብሔር እየመራት እንደሆነ አውቃለችና። የያዕቆብ ልጅ፡ ማለት… ይስሐቅም አመሻሽ ላይ ወደ ሜዳ እየወጣ ነበር። አመሻሽ ላይ እንደነበረ፡ አስታውሱ። ርብቃም በግመሉ ላይ ተቀምጣለች። ኤሊዔዘርም "እነሆ እየመጣ ነው፡" አላት። ርብቃም ከግመሉ ወረደች፡ መሸፈኛዋም ከፊትዋ አነሣች። አይታው አታውቅም። አታውቀውም… ያ ባሏ ነበር፡ አይታው ግን አታውቅም። በእምነት ልታገኘው ትሄድ ነበር። (ምን እንደሚመስል አላውቅም፡ አቤት፡ ሳየው፡ ግን!) በዚያም እሱን ባየችው ቅጽበት፡ በመጀመሪያ እይታ አፈቀረችው። እሱም አይቷት አያውቅም ነበር፡ ባያት ጊዜም፡ በመጀመርያ እይታ አፈቀራት። በዚያ ሜዳም እነሆ እርሰ በርሰ ይገናኙ ዘንድ ወጡ። በአባቱም መንግሥት እንድትሆንለት ወሰዶ አገባት።

142 ቤተክርስቲያን በአየር ላይ የምትነጠቀው በዚህ መንገድ ነው፡ በአየር መካከል፡ ጌታ ሲወርድ መንገድ ላይ ይገናኛሉ። አቤት፡ እንዴት ያለ ድንቅ ይሆናል፡ ፍቅር በመጀመሪያ እይታ! እና በዚያ በምድር አድማሶች ላይ ቆመን እነዚያን የቤዛነት መዝሙር እንዘምራቸዋለን፡ ኦህ፡ ማይ! አቤት እንዴት እንደምዘምርለት እንዴትም እንደምናወድሰው… የቤዛነት ጸጋ ሰጥቶናልና። በዚያም መላእክቶች ሁሉ—በምድር አድማሶች ዙርያ አንገታቸውን ዝቅ ያደርጋሉ፡ ሰለምን እንደምናወራ አይገባቸውምና። መላእክቶች አልጠፉምና፡ መዳን ምን ማለት እንደሆነ አይገባቸውም። ጠፍተው የነበሩ እኛ ነበርን፡ እኛው ነን። ከፊታችን ምን አይነት አስቃቂ ነገር እንደነበረ እንረዳለን፡ እሱም በገዛ ደሙ ዋጀን፡ ከነገድ፡ ከቋንቋና፡ እና ከሕዝብ። አቤት እንዴት ያለ የደስታ ቀን ይሆናል!

143 እንዲህ የሚለውን ዝማሬ፡ እወደዋለሁ፤

> በአየር ላይ ሰብሰባ ይሆናል፡
> በዚያ መልከ መልካም፡ ከፍታ ላይ፤
> እነሆ እንገናኛለን ሰላም እላችኋለሁ

ከላይ በሚገኘው በሰማያዊው ቤት ላይ፡
እንዲህ አይነት ዝማሬ ተሰምቶ አያውቅም፡ በሟች ጆሮዎች፡
ክቡር ይሆናል፡ እነሆ አውጃለሁ!
የእግዚአብሔር ልጅ ብቻውን፡ መሪ ይሆነናል
በአየር በዚያ ሰብሰባ ላይ። (አቤት!)

በደንገል ውስጥ ስለ ህጻኑ ሙሴ ሰምታችኋል፡
የማይፈራው ዳዊትንና ስለ ወንጭፉ ሰምታችኋል፤
ስለ ዮሴፍ ሕልም ሲነገር ሰምታችኋል፡
ስለ ምንዘምረው ስለ ዳንኤል እና ስለ አንበሶቹ።
አቤት፡ ሌሎችም ብዙ፡ ብዙ አሉ በመጽሐፍ ቅዱስ፡
ሁሉንም ለማግኘት እጓጓለሁ፡ እያልኩ አውጃለሁ! (ትክክል ነው!)
እነሆ ከእነሱ ጋር ስንገናኝ ምንኛ ደስታ ይሆናል
በአየር በዚያ በሰብሰባ ላይ። (ያን ቀን እየጠበቅን ነው!)

144 እነሆ መቶ አርባ-አራት ሺህ መጡላችሁ፡ ወንጌሉን ከእኛ በኋላ ይቀበሉታል... ብርሃን በአሕዛብ ዘንድ ሳለ በተመሳሳይ ጊዜ ልንቀበለው አንችልም። አይሁዶች ክደው እየደበቁት ነውና። አሁን፡ ብርሃኑ ሲመጣ... አሕዛብ ከተወሰዱ በኋላ፡ መንፈስም ይመሰክርላቸው ዘንድ በሁለቶቹ ላይ ይወርዳል፡ ይያኔ አይሁዶች ይቀበሉታል፡ ከጠፉት ከእስራኤል ነገዶች መካከል አንድ መቶ አርባ-አራት ሺዎቹ ውወንግጌሉን ይቀበላሉ፡ ሙሽራይቱ ያኔ ተወሰዳለች።

145 አሁን "አሰር ደናግል፡" አሉ። እስኪ ቶሎ ብለን፡ ማቴዎስ 21 እንክፈት። እያችሁ፡ አሁንም ጥቂት ጊዜ ይኖረናል። አቤት፡ መጽሐፍ ቅዱስን ሰወደው።

የእረፍት ጊዜዬን በገነት ሳደርግ፡
እንዴት ያለ አስደናቂ ጉዞ ይሆናል፤
በሰማይ ኳየሮች ኮንሰርቶችን እንሰማለን፡
በሮቹም ሁሉ... የአዳኜ ፊት እያለሁ፡
በወንዙ ዳርቻ ላይ ተቀምጬ፡
ከለመለመው ዛፍ ጥላ በታች፡
የእረፍት ጊዜዬን በገነት ማሳለፍ እፈልጋለሁ፡
እናንተስ ከእኔ ጋር አታርፉም ወይ?

146 አሁን፡ በ—መጽሐፍ—ቅዱስ ማቴዎስ፡ ምዕራፍ 25 ይመስለኛል፡ እንደሆነ እምናለሁ። 21 አልኩ፡ አይደል? እዚህ 21 ምልክት ተደርጎበታል፡ ግን ስህተት ነው። 25 ነው። ዛሬ ጠዋት መቸኮል ነበረብኝ፡ እና... ደክሞኝ ተነሳሁ፡ እና አርፍጄ እና—እና እየ—ቸኮልኩ ነበር። አንዳንድ ቅዱሳት መጻሕፍትን እየጻፍኩ ነበር፡ እና—25 ለማለት 21 ብዬ ጻፍኩ።

**የዚያን ጊዜ መንግሥተ ሰማያት መብራታቸውን ይዘው፡ ሙሽራውን ሊቀበሉ የወጡ፡ አሥር ደናግል ትመሰላለች።**

147 አሁን፤

**ከእነርሱም አምስቱ ሰነፎች፡ አምስቱም ልባሞች ነበሩ።**

ሰነፎቹ **መብራታቸውን ይዘው፡ ከእነርሱ ጋር ዘይት አልያዙምና፤**

**ልባሞቹ ግን ከመብራታቸው ጋር በማሰሮአቸው ዘይት ያዙ።**

**ሙሽራውም በዘገየ ጊዜ** (ይህ ማለት በቤተ ክርስቲያን ዘመን ነው)፡ **ሁሉ... እንቅልፍ እንቅልፍ አላቸውና ተኙ።**

148 በዚህ ሁሉ ዘመን፡ ሁሉም ሞቱ፡ እንቅልፍ እንቅልፍ አላቸውና ተኙ፡ አያችሁ፡ በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ ሲያልፉ። አሁን፡ "እንቅልፍ አላቸውና ተኙ" እንጂ፡ አልጠፉም፡ አያችሁ፡ እየጠበቁ ነበሩ። "እንቅልፍ አላቸውና ተኙ" ነው እንጂ፡ እንደሞቱ አልተናገረም። አያችሁ?

**እኩል ሌሊትም ሲሆን፡ እነሆ፡ ሙሽራው ይመጣል፡ ትቀበሉት ዘንድ ውጡ የሚል ውካታ ሆነ።**

በዚያን ጊዜ **እነዚያ ደናግል ሁሉ ተነሡና፡ መብራታቸውን አዘጋጁ።**

**ሰነፎቹም—ልባሞቹን፡ መብራታችን ሊጠፋብን ነው፤ ከዘይታችሁ ስጡን አሉአቸው።**

**ልባሞቹ ግን፡ መልሰው፡ ምናልባት፡ ለእኛና ለእናንተ ባይበቃስ፤ ይልቅስ ወደሚሸጡት ሄዱችሁ፡ ለራሳችሁ ግዙ አሉአቸው።** (ይቅርታ አርጉልኝ።)

**ሊገዙም በሄዱ ጊዜ፡ ሙሽራው መጣ፤ ተዘጋጅተው የነበሩትም ከእርሱ ጋር ወደ ሰርግ ገቡ፤ ደጁም ተዘጋ።**

በኋላም ደግሞ **የቀሩቱ ቈነጃጅት መጡና፡ ጌታ ሆይ፡ ጌታ ሆይ፡ ክፈትልን፡ አሉ።** (እንግዲህ፡ ተመልከቱ፡ የማያምኑ አልነበሩም፡ መልካም ሰዎች ነበሩ።)... **ክፈትልን።**

**እርሱ** ግን መልሶ... **መልሶ፡ እውነት እላችኋለሁ፡ አላውቃችሁም አለ።**

**እንግዲያውስ፡ የሰው ልጅ** የሚመጣበት **ቀኒቱንና ሰዓቲቱን** አታውቁምና **እንግዲህ** ንቁ።

149 አሁን አምስቱ "ልባሞች" ደናግል። አሁን፡ በመጽሐፍ ቅዱስ **ዘይት** የሚያመለክተው "መንፈስ ቅዱስን" ነው። ሁላችንም እናውቀዋለን። ለዚያም ነው የታመሙትን በዘይት የምንቀባው፡ ዘይት ደግሞ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነው። ስለዚህ ጠቢባን በመብራታቸው ውስጥ ዘይት ነበራቸው፡ እርሱም መንፈስ ቅዱስ ነውና፡ ወደ ሰርግ እራት ለመግባት ተዘጋጁ። አሁንም ወደ—ወደ—ወደ ሕዝቄል 9፡ መመለስ እንችላለን፡ አውጥተን ማየትም እንችላለን፡ ይሁን እንጂ አስራ አምስት እና ከዚያ በላይ የሚሆኑ ቃላት ይዣለሁ። ስለዚህ የዘይት ምሳሌ-... በዚህ ሳምንት በትምህርታችን ውስጥ እንዳየነው አምናለሁ፡ **ዘይት** ማለት፡ ምሳሌው "መንፈስ ቅዱስ" ነው። ሁላችንም እናውቀዋለን።

150 አሁን ተከታተሉ፡ ሁለቱ... "ደናግል" ነበሩ። አሁን እንዲህ ላድርግ። እዚህ ጋር፡ እነዚህ ሁለቱ ወዲህ እናምጣቸው። **ይህች** ድንግል ናት **ይህችኛይቱም**

ድንግል ናት፡ **ይህች** ስነፍ ድንግል ነበረች **ይህችኛይቱ** ልባም ድንግል ነበረች፡ ሁለቱም ደናግል ናቸው።

151 **ድንግል** የሚለውን ቃል ብትመረምሩት፡ "ቅዱስ፡ ንጹሕ፡ የተቀደሰ" ማለት—ማለት ነው። **የተቀደሰ** የሚል ቃል መነሻው "ቅዱሳን፡" ከሚል ቃል የመጣ ነው፡ ትርጉሙም "ንጹሕ" ማለት ነው። እንደ ዕብራይስጥ ቃል... አሁን፡ **መቀደስ** ማለት "ንፁህ" ቃሉ፡ የግሪክ ቃል ነው። ወደ ዕብራይስጥ ሲመጣ፡ ቃሉ "ቅዱስ" ሆነ። እያችሁ? ወደኛ ሲሆን ደግሞ "ንጹህ" ይሆናል። አሁን፡ ሶስቱንም ቃላት ይወስዳሉ፡ ማለት እያንዳንዱ ቃል ተመሳሳይ ትርጉም ቢኖረውም አነጋገሩ ይለያያል፡ ቃሉም እ—እንደ "ንጹህ፡ ቅዱስ፡ የተቀደሰ፡" ሶስቱም አንድ ቃል ናቸው።

152 ልክ አንድን ቃል **ውሻ** ብንል። "ዶግ፡" ካልኩኝ፡ ኢንግሊሽ ነው። ፍሬድ፡ በጀርመንኛ **ዶግ** ለማለት፡ "ሁንድ" ነው። ልክ ነው? ወንድም ኖርማን፡ በስፓኒሽ **ዶግ** ካልኩ፡ "እጆ" ነው። **እጆ፡ ሁንድ**፡ እና **ዶግ** ለእኛ ሁሉም **ውሻ** ነው፡ እያችሁ። እያችሁ፡ ልክ እንደ—እንደ፡ አባባል ነው።

153 ስለዚህ፡ በግሪክኛ **ንጹህ** ለማለት "የተቀደሰ" ይላሉ፡ የዕብራይስጥ ቃል "ቅዱስ" ነው። ቅዱስ፡ ንፁህ፡ እና የቀደሰ፡ ሁሉም አንድ ቃል ነው። ስለዚህ ይህች የበከተች፡ የቆሸሸች ቤተ ክርስቲያን አልነበረችም፤ የተቀደሰች፡ ንጹህ ቤተ ክርስቲያን ነበረች፡ "ሙሽራውን ሊቀበሉ አሥር **ደናግል** ወጡ።" ምን ማለት ነው? **አብያተ ክርስቲያናት** በሙሉ። አሁን... አይደለም፡ **እዚህ** የሮማውያን ጋር አይደለም፤ ነገር ግን በኃይማኖት ተቋማት፡ በኒቆላውያን። ባፕቲስት ስለ ክርስቶስ ዳግም ምጽዓት ይሰብካሉ፤ ሜቶዲስት የክርስቶስን ዳግም ምጽዓት ይሰብካሉ፤ ፕሬስባይቴሪያን የክርስቶስን ዳግም ምጽዓት ይሰብካሉ፤ ናዝራውያን የክርስቶስን ዳግም ምጽዓት ይሰብካሉ፤ ፒልግሪም ቅድስና የክርስቶስን ዳግም ምጽዓት ይሰብካሉ። ልክ ነው? "ሁሉም ሙሽራውን ሊቀበሉ ወጡ።" እንግዲህ—ሙሽራውን—ለመቀበል ሁሉም መንገዳቸውን እንደጀመሩ አስታውሱ። እንግዲህ፡ እግዚአብሔር የሚያከብረው ያ ብቻ ቢሆን ኖሮ፡ እነርሱን ለመቀበልም፡ ይገደድ ነበረ።

154 ነገር ግን የዚህን ተመሳሳይ ነገር፡ በቀደም ማታ የተማርነው ትዝ ይበላችሁ፡ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ዘመን "በለዓም፡ የበለዓም ትምህርት" ሲለን አስታውሱ። እና፡ እነሆ በልዓምም፡ የተደራጀ እና ትልቅ ህዝብ ሆኖ፡ በጥሩ ሁኔታ ላይ የነበረ ነው። በእግዚአብሔር የሚያምኑ ነበሩ፡ ምክንያቱ ባላቅ፡ ማለቴ... በልዓም በወረደ ጊዜ ያደውረገውን ተመልከቱ። የእስራኤል አምላክ ለሆነው፡ ለእስራኤል አምላክ ለጆሆቫ፡ አንድ አይነት መሥዋዕት አቀረበ። ሰባትም መሠዊያዎች ሠራ። ሰባት የእግዚአብሔር ሙሉ ቁጥር ነው።

155 "ስድስት ቀን ስራ፡ ሰባተኛውም ዐረፈ፡" ይህ ሙሉ ነው፡ እያችሁ፡ ሰባት። ስድስት ቀናት በዓለም ላይ ስራ። የመጀመሪያ ሁለት ሺህ ዓመታት፡ በውኃ ጠፋ፤ ሁለተኛ ሁለት ሺህ ዓመት፡ ክርስቶስ መጣ፤ እና ይህ ሦስተኛው ሁለት ሺህ ዓመት ነው። በየሁለት ሺህ ዓመት መጨረሻ ላይ፡ አንድ ነገር ይከሰታል፡ ዓለም እንደገና ትናወጣለች። በስድስት ሺህ ዓመታት ውስጥ፡ ዓለምን ሠራ፤ ስድስት ሺህ ዓመታት ቤተ ክርስቲያን ዓለምን አማጠች፡ ሰባተኛውም ሺህ የሺህ ዓመት መንግስት ነው። አሁን ገባችሁ?

156 አሁን፡ ቤተ ክርስቲያንም ሰባት የቤተክርስቲያን ዘመናት፡ አሏት። እግዚአብሔር... ይህም የቤተክርስቲያኑ ዘመን ሙሉ ቁጥር ነው፡ ይህ ሁሉ፡ ሰባት ነው። **ሰባት** የእግዚአብሔር የሙላት ቁጥር ነው። ሰባት የቤተክርስቲያን ዘመናት፡ ሰባት ሺህ የፍጥረት ዓመታት፡ ነገር ሁሉ በሰባት ውስጥ ይፈጸማል።

157 እንግዲህ፡ ሊቀበሉት የወጡ ደናግል ነበሩ። እና እነዚያ "ሰነፍ" ደናግል፡ በመቅረዛቸው ውስጥ፡ ዘይት አልያዙም ነበር፡ ሌላ ነገር ሁሉ ግን ነበራቸው፤ ንጹሐን ነበሩ፡ በክርስቶስ ያምናሉ፡ ያመኑትን ቃል ሰብከውታል፡ ዳግም ምጽአቱን፡ ስለ መሰዋዕቱ፡ ስለ ማስተሰሪያው፡ የኃይማኖት ተቋማቸው ሰበኩ ይሏቸዋል፡ እነሱም ሰብከውታል። ያምናሉ። እሰኪ አንድ ቀን ከአንድ ጥሩ የባፕቲስት ምሁር ጋር ተገናኙ፡ (ሃህ) የምታወራውን ነገር በደንብ የሚያውቅ መሆን ይኖርብሃል፡ ኧሃ-ሃህ፡ በትክክል።

158 ግን፡ ተመልከቱ፡ ማቴዎስ በ 24 ላይ "እጅግ ይመሳሰላሉ፡" ብሏል፡ ማቴዎስ 24፡24፤ ፈጥናችሁ አንብቡት እና ትረዱታላችሁ። ኢየሱስ ስለ መጨረሻው ዘመን ሲናገር የሚቻል ቢሆን ኖሮስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ሁለቱ መናፍስቶች እጅግ ይመሳሰላሉ አለ። እጅግ ስለሚመሳሰል እንደ ማንም ሰው ጴንጤቆስጤዎችን ያወዛውዛቸዋል። በትክክል! አሁን፡ ማቴዎስ 24፡24፡ የከፈተ ሰው አለ? እዚህ አላገኘሁትም። እህቴ፡ አገኘሽው፡ ወይም ሌሎቻችሁ? ማቴዎስ 24። እሺ፡ ቤን? በጣም ጥሩ፡ አንብቢው።

> [አንዲት እህት አነበበች፤ **እነሆ ሐሰተኞች ይነሣሉ** ክርስትያኖች፡ **ሐሰተኞች—ሐሰተኞች ክርስቶሶች፡**—አርታዒ።] **ሐሰተኞች ክርስቶሶች**! [**እና ሐሰተኞች ነቢያት፡**] **ሐሰተኞች ነቢያት**! [**ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ፤ ቢቻላቸውስ፡ የተመረጡትን እንኳ፡ እስኪያስቱ ድረስ**።]

159 ይኸው እንግዲህ። እሺ፡ ማን ይነሳል? ሐሰተኞች ክርስቶሶች ይነሣሉ፡ ሐሰተኞች ሰዎች "እኔ የክርስቶስ ነኝ፡" እያሉ ይነሳሉ። ሐሰተኞች ነቢያት፡ "እኔ **ይህ** ነኝ እኔም **ያ** ነኝ፡" ይላሉ። ቢቻል ኖሮ የተመረጡትን ያታልላሉ ማለት ይቻላል። እናም መዳን የሚቻልባት አንድ ብቸኛ መንገድ ብቻ አለች፡ ያም አለም ሳይፈጠር በፊት ከተመረጣችሁ ከሆናችሁ ብቻ ነው፤ ይህም፡ አስቀድሞ በማወቅ፡ ለተመረጡት ነው፡ ያኔ ስሞቻችሁ በመጽሐፍ ተጽፈዋል። "ታላላቅ ምልክቶች!"

160 አሁን እነዚህን ሁለት አብያተ ክርስቲያናት ተመልከቱ። ብችል፡ ኖሮ... ህዝቡ እንዲያየው ማድረግ የሚቻልበት የሆነ መንገድ ቢኖር። በነፍሴ ውስጥ ይቀጣጠላልና! ይህም... **እነዚህ** አብያተ ክርስቲያናት **እንደነዚህ** ንጹሓንና ቅዱሳን ናቸው፤ ሁሉም ድንግሎች ከሆኑ፡ ሁሉም ድንግሎች ናቸው፡ **እንዲሁ** ንጹሃን ናቸው። ብቸኛው ልዩነት—በመቅረዙ ውስጥ ያለው ዘይት፡ እሱም መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ፡ በዚያ ውስጥ ካለ፡ በጴንጤቆስጤ ዕለት የነበረውን ዓይነት እሳት ያመነጫል። ይሁን እንጂ በመቅረዛቸው እሳት አልነበረም፡ ዘይት አልነበራቸውም። የቤተክርስቲያን ሥርዓት አላቸው፡ ቤተ ክርስቲያን—የቻለችውን ያህል የሥርዓት ሆነች፡ ባለ ጥሩ ጥሩ ድግሶች (እሱም ቢሆን ችግር አልነበረውም)፡ ሕሊናህን የሚያናውጥ የሃይማኖት

መግለጫዎች፡ እና እንደ መላእክት ዝማሬ ያሉ መዝሙሮች። እና በእነርሱ ላይ... እናንተ... በሕይወታቸው ላይ... ጣታችሁን መቀሰር፡ አትችሉም። ይህም ቢሆን ስህተት ነው! እንዲህ አይደለም... የሱ—አካል ነው እንጂ፡ **በሙላት** አይደለም። መነጠቅ የሚያመልጣቸው ምድብ እነዚህ ናቸው። አያችሁ? ዝም ብለው...

161 አሁን ተመልከቱ። እነሆ ሞዓብ መጣ። ምናልባት እንድታዩት ከዚህ ደግሞ ልውሰድ። እነሆ ይህ ሞዓብ ነው፡ ታላቅ ድርጅት ነበረ፡ "**የ**" ድርጅት የነበረ እዚህ አደርገዋለሁ፤ እነሆ እስራኤል፡ ድርጅት "አልነበረም።" እነሆ ሞዓብ፡ አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት፣ ስድስት፣ ሰባት መሠዊያዎች አቆመ። እስራኤልም አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት፣ ስድስት፣ ሰባት መሠዊያዎች ነበራቸው። በጣም ጥሩ። ሞዓብ በዚህ ሰፍራ አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት፣ ስድስት፣ ሰባት ወይፈኖች አኖረ፤ እስራኤልም፡ አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት፣ አራት፣ አምስት፣ ስድስት፣ ሰባት ወይፈኖች። በጣም ጥሩ። ሞዓብ እንዲህ አለ፡ "እነሆ (ክርስቶስ) የተባለ ሰው ወደ ምድር የሚመጣበ ጊዜ ይመጣል፡ እርሱም የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ ይሆናል፡ ሰባት እንደረድራለን" (ምን? ) "በመሰዊያው ላይ በጎች"፤ እስራኤልም አለ፡ "በመሰውያው ላይ ሰባት በጎች መሆናቸው፡ ይህ ትክክል ነው።" አያችሁ?

162 አሁን፡ በመጀመሪያው፡ ቃየን መሠዊያ አቆመ፡ መሰዋዕቱንም ሠዋ፡ ሰገደ፡ አቤልም ያደረገውን ሁሉ አደረገ፡ መላው ቤተ ክርስቲያን በዚያ መገለጥ ላይ የተመሠረተች፡ ሰትሆን፡ ያለ... (አቤት፡ ይህን ተቀበሉ!)... ያለ እግዚአብሔር መገለጥ አደረገ። ኢየሱስም "በዚህች ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ፡" ብሏልና። በመንፈስ የተገለጠ የኢየሱስ ክርስቶስ ልዑል አምላክነት እውነት፡ "በዚህች ዓለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ።"

163 አሁን፡ እግዚአብሔር እንደ ሜቶዲስትነታችሁ፡ ባፕቲስትነታችሁ፡ ጴንጤቆስጤዎች እና እንደ ሌሎች፡ የሆነውን ስርአቶቻችሁ፡ ልማዶቻችሁ ብቻ፡ የሚያከብር ከሆነ፡ ዳግም ምጽአትንና እነዚህን ሁሉ ነገሮች እንድትሰብኩ፡ ያንን ብቻ እንድታደርጉ የሚጠብቅ ከሆነ (ይህም፡ ፍጹም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነውና)፡ እንደ ባፕቲስት፡ ፕሬስባይቴሪያን፡ እና የመሳሰሉት፡ ቅድመ ሁኔታው ያ ብቻ ከሆነ እንግዲያውስ እግዚአብሔር ሁለቱን የመውሰድ ግዴታ አለበት። ግን፡ እንዳያችሁት፡ ሰነፏ ድንግል፡ **እነኋት** ያለ መገለጥ፡ ልባሟ ድንግልም **እዚህ** አለች። ድርጅት፡ ታላቅ ሕዝብ ነበሩ።

164 ባለፈው ማታ፡ እንዲህ የሚለውን አንብበናል፡ "እነዚህ ህዝብ ድርጅት አይሆኑም፡ በምድር ላይ ተቅበዝባዦች፡ በድንኳን ውስጥ የሚኖሩ፡ ድሆች፡ ትሑታን ይሆናሉ።" ይሁን እንጂ "እኔ በመካከላቸው ነኝና፡ አትርገማቸው፡" ተባለ። አሁን ተመልከቱ! እነዚህ ሰዎች እነዚያ በሚያምኑት ተመሳሳይ ሥርዓት ያምናሉ፡ ተመሳሳይ አምላክ ያመልካሉ። አያችሁ? ነገር ግን የሚከተሏቸው ምልክቶች እና ድንቆች አልነበሯቸውም! እስራኤል ግን የናስ እባብ፡ የተመታው ዓለት፡ የንጉሡ ደስታ፡ መለኮታዊ ፈውስ፡ ነቢያት፡ እነዚህ ሁሉ **በዚያ** ነበራቸው። እነርሱ ጋር ግን አልነበረም፡ በረከት የሌለው፡ ማለት ዘይት የሌለው—ሥርዓት ነበራቸው።

165 በልባሟ ድንግል እና በሰነፏ ድንግል መካከል አንድ አይነት ነው፡ ሁለቱም የተቀደሱ ነበሩ። **አንደኛዋ** ግን ዘይት ይዛ ነበር። **ሌላኛዋ** ዘይት አልነበራትም፡ እነርሱም "እኛም እንደ እናንተ እንዲሁ ነን፦" አሉ። ያ ነው… እንደውም፡ ማናችንም ብንሆን ጥሩ ነገር የለንም። "ለምን፡ የሆሊ-ሮለር ጉባኤ ስለሆናችሁ!" እሺ፡ ይሁን፡ ኧሃ-ሃህ፡ ምንም ችግር የለውም። ማንኛችንም ጥሩ ነገር የለንም፡ ሁላችንም ኃጢአትን ሰርተናል የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎናል። የምታውቁበት ብቸኛው መንገድ ግን፡ ቤተክርስቲያንን በመቀላቀል፡ ወይም መልካም ኑሮ ለመኖር በመሞከር ሳይሆን፡ ክርስቶስን በመቀበል ነው። በነበረኝ ነገር ሳይሆን፡ በነበረው ማንነት ነው። ባለኝ ነገር ሳይሆን፡ ባለው ማንነት ነው። እኔ በጸጋው፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ እርሱን እሆን ዘንድ፡ እርሱ እኔን ሆነ። አያችሁት?

166 እንግዲህ፡ እነሆ ሰነፎቹ ድንግሎች፡ እና በመቅረዛቸው ዘይት የያዙ ልባሞቹ ድንግሎች። አሁን፡ በድንገት፡ ድምፅ መጣ፡ "እነሆ፡ ሙሽራው ይመጣል፡ እሱን ለመገናኘት ውጡ!" ሁሉም ነቁ፡ በነቁ ጊዜም፡ **እነዚህ** በመቅረዛቸው ዘይት ስለያዙ መግባት ቻሉ። ልዩነታቸው ያ ነበረ።

167 **እነዚህ** ግን መግባት አልቻሉም፡ በመቅረዛቸው ዘይት አልነበራቸውና፤ መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል፡ ወደ መጸለይ ተመለሱ። እነሱ በሄዱ ጊዜ፡ ግን፡ ሁሉም ነገር አለቀ። የኃይማኖት ተቋማት እንዲህ አሉ፡ "እንግዲህ፡ ምናልባት ተሳስተን ይሆናል። ምናልባት ተመልሰን፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት እንፈልግ።" አሁን ለማድረግ እየሞከሩ ያሉት ያ ነው። ይህ ነገር አስተውላችሁታል? ፕሪስባይቴሪያኖች… ቴፕህን ለአንድ ደቂቃ አጥፋልኝ፡ ይህን ሰም መጥራት አልፈልግም። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]… ?… ሙሽራው መጣ። እና፡ ታዲያ፡ እነሱ ለመግዛት በሄዱ ጊዜ፡ የመምጣቱ ጊዜ ምን ያህል ቅርብ ይሆን! በጣም ጥሩ፡ ቴፕህን ክፈትልን፡ ጂን። አሁንስ፡ ገባችሁ? "ለመግዛት ሲሄዱ፡" አሁን ለመግዛት እየሞከሩ ናቸው፡ አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ ሪቫይቫል፡ ሪቫይቫል ይላሉ፡ ወደ ኋላ ለመመለስ ይሞክራሉ።

168 እንግዲህ፡ ዶክተር ቢሊ ግራሃም ሳይቀር፡ **በሄራልድ ኦቭ ፌይዝ**፡ ከቺካጎ የጻፈውን፡ አይታችኋል፡ "የጴንጤቆስጤውን እንቅስቃሴ ችላ ማለት አይገባንም" አላቸው። አያችሁ? "በአንድ አመት ውስጥ ሌሎች አብያተ ክርስትያናት ሁሉ ተደምረው ከቀየሯቸው ይልቅ የሚበዛ ነፍሳት ስለቀየሩ ልናከብረው… -አንችልም።"

169 የሚያንቀጠቅጥ፡ የሚገርዝ፡ መረቡን ጥሎ የሚጎትት፡ እና የሚቀጣጠል እሳት ማለት ይህ ነው። መረብ ስትጥሉም… ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ "የእግዚአብሔር መንግሥት ሰው ሄዶ መረቡን ወደ ባሕር የጣለ ይመስላል፡ በሳበውም ጊዜ፡ ኤሊዎች፣ እባቦች፣ እንቁራሪቶች፣ እባቦች፣ ሌሎች ነገሮች ነበሩበት፡ ጥቂት ዓሣዎች ደግሞ፡ ነበረው።" የጴንጤቆስጤ መልእክት እያደረገ ያለው ይህ ነው፡ ምድሪቱን እየጠራረጋት ነው፤ ወደዚያም ወርውሮ፡ ኤሊዎች፣ ክራውፊሽ፣ ክራውዳዶች፣ ታድፖሎች፣ የውሃ ውሾች፣ ሄልዳይቨሮች፣ በዚያ የተገኙትን ሁሉ ይጎትታቸዋል። ታዲያ ምንድነው፡ በዚያ ውስጥ፡ ጥቂት ዓሦች ደግሞ አሉ። የጌታ የሆኑትም እነዚያ ናቸው።

170 እሺ፡ ለእናንተ በዚህ ቴፕ ውስጥ ላላችሁ አንዳንድ ወግ አጥባቂያን-

አማኝ ወንድሞች፡ ይህን ማጥፋት ለምትፈልጉ፤ ዓሳ የሆኑት መቼ ነው? መረቡ በላያቸው ላይ ሲያልፍ? ከመጀመሪያ ላይ ዓሣዎች ነበሩ! በትክክል። ከዓለም መሰረት ምሰረታ ጀምሮ የተመረጡ! ጌታ እንዲጠቀምባቸው በጭራሽ መጥተው አያውቁም።

171 ያ'ማ የእናንተ እንቁራሪት ነው። አንድ እንቁራሪት ወሰዳችሁ ዳርቻው ላይ ወርውሩት፡ "ውፕ፡ ውፕ" እያለ ወደ ውሃው ይመለሣል።

172 ክራውፊሽም ጥግ ላይ ሆኖ፡ "ኧሃ፡ እነዚህ ሆሊ-ሮለሮች ናቸው፡" ይላል። "ኧሃ—ኧሃ—ኧሃ—ኧሃ—ኧሃ። ኦህ፡ ኖ!" ተመልሶ ይሄዳል፡ በቻለው ፍጥነት ወደ ጭቃው ዘው ይላል። እውነት ነው።

173 እባቡም ዙርያውን እንዲህ እያፏጨ፡ "የተአምራት ዘመን አልፏል ብዬ አምናለሁ፡ ዶክተር **እገሌ-እና-እገሌ** እንዲሁም **እገሌ-እና-እገሌ** ነግሮኛል።" አለውም፡ "ኧሃ—ኧሃ—ኧሃ—ኧሃ—ኧሃ—ኧሃ—ኧሃ፡ ልታታልለኝ አትችልም!" እነሆ እንደገና፡ ወደዚያ ትገባለች፡ አያችሁ።

174 ከጅምሩ፡ እንቁራሪት ነው! ከጅምሩ፡ እባብ! ጳውሎስ በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ስለ እንዲህ አይነቶቹ፡ እንዲህ ሲል ተናግሯል። "ከመጀመሪያ ከእኛ ጋር ስላልነበሩ ከእኛ ዘንድ ወጡ።" አያችሁ? አሃ! እሺ፡ ሰነፏ ድንግል።

175 ልባሟ ድንግል፡ በመብራቷ ዘይት አዘጋጅታለች።

176 አሁን፡ "ዘይት ፍለጋ በወጣች ጊዜ፡" አሁንም እያደረጉ ያሉት ነገር ይህ ነውና። እነዚህ ታላላቅ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት፡ እነዚህን ታላላቅ ነገሮች ለማግኘት እየሞከሩ፡ አያችሁ፡ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ... ይመለሳሉ፡ እንደገና፡ "የጴንጤቆስጤ በረከት እንፈልጋለን" ይላሉ። ለምን፡ ምን አይነት አገልግሎት ሊኖራቸው እንደሚችል መገመት ትችላላችሁ፡ አያችሁ። መቼም በላያቸው ላይ የቀባቡትን ማኒኩር፡ እና ሌላ ሁሉ አያስወግዱትም። ኦህ፡ ኖ። መቼም ቢሆን ማሕበራቸው እና ማሕበረሰባዊነታቸው እንዲሁም ሌሎች ነገሮቻቸውን አይተውም። እንደ ዔሳው በአንድ እጁ ዓለምን፡ በሌላኛው በኩል እግዚአብሔርን፡ ለመያዝ ይሞክራሉ። ይህን ማድረግ አትችሉም። ታውቃላችሁ፡ እግዚአብሔርን እና አለምን ለማየት፡ ዓይነ-ሸውራራ ክርስቲያን መሆን አትችሉም። ቀራንዮን ማዕከላችሁ ማድረግ አለባችሁ፡ ያንን ይዛችሁ ጽኑ።

177 አሁን ግን፡ እነሆ ሄደዋል፡ ወደ ኋላ ለመመለስ ይሞክራሉ። ምን ያህል እንደቀረብን አስታውሱ! እነዚያ ለመግዛት በወጡበት ቅጽበት፡ ሙሽራው የመጣው ያን ጊዜ ነው።

178 ወንድም ስቲከር ሆይ፡ እነሆ፡ ተቃርበናል! ቤታችን አጠገብ ደርሰናል። እነሆ፡ ከእነዚህ ማለዳዎች በአንደኛው ላይ፤

> የጌታ መለከት ሲነፋ፡ ጊዜውም ሲፈጸም፡
> ግሩም እና ድንቅ ጎህ፡ ሲቀድ ለዘለአላም፡
> ከምድር የዳኑ ሁሉ በሰማይ ሲሰበሰቡ በፊቱ፡

እንዴት ያለ ድንቅ ጊዜ ይሆናል!

179 አዎን፡ ሰነፏ ድንግል። አሁንስ... ይህች ሰነፍ ድንግል፡ ምን እንደምትሆን ማወቅ ትፈልጋላችሁ። ልክ ነው? አንድ ነገር ማብራራት እፈልጋለሁ። እነዚህ

አብያተ ክርስቲያናት ምን ይሆናሉ? ከክርስቶስ ጋር የመንገዱ ግማሽ ያህል ተጉዘው ያልደረሱ፡ ወይም ከክርስቶስ ጋር እስከ ፍጻሜ ያልሄዱ ሰዎች፡ ምን ይሆናሉ?

180 አሁን በሮሜ፡ 2፡22፣ ይመስለኛል፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡ "የእግዚአብሔር መንፈስ በእናንተ ውስጥ ከሌለ፡ የእግዚአብሔር ወገን አይደላችሁም፡" ይላል ጳውሎስ። የድርጅት እንጂ የእግዚአብሔር አይደላችሁም። የእግዚአብሔር መንፈስ በአንተ ውስጥ ከሌለ፡ የእግዚአብሔር ወገን አይደላችሁም። አያችሁ። ከእግዚአብሔር ለመሆን የእግዚአብሔር መንፈስ ሊኖራችሁ ይገባል። በትክክል!

181 እሺ፡ ወዳጄ፡ "ታላቁ መከራ።" እንግዲህ፡ እንግዲህ... በዚያ ማለፋቸው አይቀርም... እንግዲህ፡ አስታውሱ፡ እንዲህ አለ... አሁን የቀሩ ነገሮች ውስጥ ልግባ፡ "በውጭ ወዳለው ጨለማ ተጣሉ፡ በዚያም ልቅሶ፡ ዋይታ፡ እና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።" እሺ፡ ያም ታላቁ መከራን ነው። አይደል? ታላቁ መከራ! እንግዲህ፡ ከዚህ መከራ በኋላ፡ እነዚያ ሰዎች...

182 አሁን፡ እዚህጋ እንደገና ልያዘው፡ ቅሪቶች ናቸው። አሁን ተመልከቱ! **እዚህ** ጋር አንድ ጥሬ ዕቃ ታስቀምጣለች። እሺ፡ ሴቲቱ **እንዲህ** ያስቀመጠችው ነው። እንግዲህ ለራሷ የሆነ ነገር፡ ማለት፡ ልብስ ልትሰራ ነው። እንግዲህ ያላት፡ ጥሬ ዕቃ—ይህ ብቻ ነው። እንግዲህ፡ ያላው ጥሬ ዕቃ አንድ እና ተመሳሳይ ዓይነት ነው። ልክ ነው?

183 ሁለቱም ደናግል ነበሩ። አያችሁ? እሺ። በክርስቶስ እምነት ነበራቸው፡ የአምልኮት መልክ ነበራቸው፡ ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ፡ መልካም ነገር ያደርጋሉ፡ ፍቅር፡ በስራቸው እና በተግባራቸው ላይ አንዳች አይወጣቸውም። በእያንዳንዱ ዘመን ላይ፡ "ስራህን አውቃለሁ" ይላቸዋልና። "ሥራህን አውቃለሁ፡ ነገር ግን ባለ ጸጋ ነህ።" አያችሁ?

184 አሁን፡ አንድ ሴት... ምን ዓይነት ንድፍ እንደሚያስፈልጋት በአእምሮዋ ትወስናለች፡ እና ንድፉን በየትኛው መንገድ እንደምትቆርጠው፡ ከምን እንደሚቆረጥ በአዕምሮዋ ትወስናለች። ልክ ነው? መልካም፡ በቂ እና ምርጥ ነው ብላ የምታስበውን የንድፉን ምስል—ታዘጋጃለች። ልክ ነው? ምክንያቱም ሁሉም አንድ አይነት ጥሬ ዕቃ ናቸው፡ ነገር ግን **በዚህ** ምናልባትም **በዚያ** መልኩ፡ ትሰለዋለች። ከዚያም መቀስዋን ይዛ ትቆርጠዋለች። እንግዲህ ከዚያ የሚተርፍ ነገር፡ "ቅሪት" ይባላል። እሺ። አሁን፡ ይህ ንድፍ ምንድን ነው? እንዴት ይታወቃል? በ... ሴትየዋ ለመቁረጥ በመረጠችበት ቦታ።

185 እግዚአብሔር፡ ዓለም ሳይፈጠር በፊት፡ አስቀድሞ በማወቅ ከጥንት ጀምሮ ፍጻሜውን በማወቁ፡ የት መቁረጥ እንዳለበት **መረጠ**። በኤሳውና በያዕቆብ መካከል ያለውን ልዩነት ያውቃል። በኃጢአተኛ እና በቅዱስ መካከል ያለውን ልዩነት ያውቃል። ልዩነትን ያውቃል። የሁሉንም የልብ አሳብ ያውቀዋል፡ ስለዚህም ዓለም ሳይፈጠር በፊት መረጠን ስማችንንም በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ላይ አኖረ፤ ሊታረድ የነበረው በግም መረጠ (ከመታረዱ **በፊት** ስማችንን በዚያ ጻፈ)፡ መጽሐፍ ቅዱስም ክርስቶስ ዓለም ሳይፈጠር የታረደው በግ ነው ይላል። ያኔ የሚታረድ በግ ይሆን ዘንድ በተመረጠ ጊዜ—

ሰሞቻችንም በመጽሐፉ ላይ ተጻፈ፡ እርሱ የሚታረድላቸው እንሆን ዘንድ ተመረጥን። አያችሁት?

186 እንግዲህ፡ ሁሉም ድንግል ናቸው። እንግዲህ፡ ጥቂቶቹ ቅሪቶች **እነሆ** እነዚህ ናቸው፡ አልተጣሉም። ኧረ፡ በጭራሽ። ታሰቀምጠዋለች፡ ለሌላ ነገር ልትጠቀምበት ትችላለችና፡ እንደገና ትዘረጋዋለች። አያችሁ? **በዚያ** ግን ጥቅም ላይ አይውልም፡ በዚያ ተቆርጣ የወጣችው ቤተ ክርስቲያኒቱ ናትና። እንግዲህ፡ ፍርድ ፊት መቆማቸው አይቀርም (በመከራው ያልፋሉና)፡ እነዚያ ቅሪቶች ናቸው። አሁንስ ተረዳችሁት?

187 **ይህች**፡ ወደ ቤት የምትወሰደው፡ ቤተክርስቲያን ናት። **ይህች** ደግሞ ወደ ኋላ የቀረችው ቅሪት ናት። **እዚህ** ጋር ደግሞ አንድ መቶ አርባ-አራት ሺህ አይሁዶች፡ በሲና ተራራ ላይ ናቸው። ሶስት የተለያዩ ሙሽሮች አይደሉም። አሃ! ሙሽራይቱ፡ ቅሪቶች፡ እና መቶ አርባ-አራት ሺዎቹ ናቸው። በትክክል። ከመንፈስ ቅዱስ ምግብ በቀር ሌላ ነገር አልበላም፡ እንደውም፡ ጤነኛ ነበር እላለሁ፡ ዮሐንስ ምንም አልሆነም። አያችሁ? በዚያም—እነዚህ እንዲሁ ናቸው።

188 አሁን፡ በጊዜው መጨረሻ፡ መጽሐፍ ቅዱስ "ቅዱሳን በምድር ላይ ይፈርዳሉ" እንደሚል ሰንቶች ታውቃላችሁ? ጳውሎስም እንዲሁ ተናግሯልና። አሁን መጽሐፈ ዳንኤልን እንክፈትና—ወደ ነጩ ዙፋን እንግባ። ከራዕይ ልናየው እንችላለን ነገር ግን ከዳንኤል እንድናየው እወዳለሁ፡ ተመሳሳይ ነገር ነው። ዳንኤል 7 ላይ፡ እና ታላቁ የነጭ ዙፋን ፍርድ—እዚህ እንረዳዋለን። በዳንኤል 7ኛ ምዕራፍ 8ኛ ቁጥር እንጀምር፤

> **ቀንዶችንም ተመለከትሁ፡ እነሆም፡ በመካከላቸው፡ ሌላ** ትንሽ **ቀንድ ወጣ፡ በፊቱም ከቀደሙት ቀንዶች ሦስት ተነቃቀሉ፤** (እንግዲህ፡ እዚያ ሮም፡ እንዳለን እናውቃለን። አያችሁ? ) **እነሆም፡ በዚያ ቀንድ፡ እንደ ሰው... ዓይኖች የነበሩ፡** (አሁን፡ አስታውሱ፡ ይህ ቀንድ አክሊል አልተቀበለም፡ ተንኮለኛ ነገር ነበረ። ሌሎቹ ቀንዶች ወደ አውሬነት ተቀየሩ። ይህ ተንኮለኛ ነበር፡ ሰው ነበር፡ ከአረማዊነት ይልቅ ጳጳስ ሆነ፡ አያችሁ።) **ዓይኖች በትዕቢትም የሚናገር አፍ ነበሩበት።**

189 አሁን፡ 9ኛ ቁጥር ተመልከቱ፤

> **ዙፋኖችም እስኪዘረጉ** ድረስ **እየሁ፡** (ነብዩ እየተናገረ ነው። እነዚህም የአሕዛብ መንግሰታት ሁሉ ናቸው። አሁን አስታውሱ፡ እነዚህ እሱ የተናገራቸው ነገሮች ሁሉ እስከዚህ መጨረሻው ነገር ድረስ ተከስተዋል፡ ይህም ነገር በታሪኮቻችን እናውቀዋለን።)... እነዚህ... ሁሉ—**ተዘረጉ፡ በዘመናት የሸመገለውም ተቀመጠ፡** ልብሱ**ም እንደ በረዶ ነጭ፡** (በቀደም ማታ በነገርኳችሁ ራዕይ መሰረት ይህበዚያ ማን እንደነበረ ታውቁታላችሁ? ኢየሱስ ነው።) **የራሱም ጠጉር እንደ... ጥሩ ጥጥ** ነበረ፡ **ዙፋኑ**ም **የእሳት ነበልባል ነበረ፡ መንኰራኵሮቹም የሚነድድ እሳት ነበሩ።**
>
> **የእሳትም ፈሳሽ ከፊቱ ይፈልቅና ይወጣ ነበር፤** ሺህ ጊዜ **ሺህ ያገለግሉት ነበር፡** (ይህች ከእርሱ ጋር የምትመጣው ቤተ ክርስቲያን ናት፡ አያችሁ።) እልፍ **ጊዜ** እእላፋትም **በፊቱ ቆመው ነበር፤**

(ይቺ የምትመጣው ሙሽራይቱው ናት፡ ሌላው አለምም በሙሉ።)
**ፍርድም ሆነ፡ መጻሕፍትም ተገለጡ።**

**... ፍርድም ሆነ፡ መጻሕፍትም ተገለጡ።**

**የዚያን ጊዜም ቀንዱ ይናገረው ከነበረው ከታላቁ ቃል ድምፅ የተነሣ** አየሁ፤ **አውሬይቱም እስክትገደል፡ አካልዋም እስኪጠፋ** ድረስ፡ በእሳትም **ለመቃጠል እስክትሰጥ** ድረስ **አየሁ።**

**ከቀሩትም** ሙታን፡ **እነዚያ ግዛታቸው** የተ**ወሰደ**ባቸው-... (ማለቴ)... **አራዊት** (ማለቴ)፡ **ግዛታ**ቸው **ተወሰደ**ባቸው፤ እና **የሕይወታቸው ዕድሜ ግን እስከ ዘመንና እስከ ጊዜ ድረስ ረዘመ።**

190 አሁን፡ ፍርዱ ተዘጋጅቶ መጽሃፍት ተከፍተዋል። ይህም ሙሽራይቱ ተመልሳ ፍርዱን የምትሰጥበት ጊዜ ነው፡ ማለት የተመረጠች ቤተ ክርስቲያን... የተነጠቀችው ቤተ ክርስቲያን ከሦስት ዓመት ተኩል በኋላ ትመለሳለች፡ እና ከጊዜ በኋላ... በራዕይ ላይ ደግሞ ያብራራል፡ እንዲህ—እንዲህ—በማለት "የቀሩት ሙታን ግን ለአንድ ሺህ ዓመት አልኖሩም።" እናንተስ፡ ሰንቶቻችሁ አንብባችሁታል? ብዙ፡ ለብዙ ዘመናት። "ለሺ አመት አልኖሩም።" ኢየሱስም ከሙሽሪት፡ ከሙሽሪት ጋር ይመለሣል።

191 አሁን አስታውሱ፡ እንደተናገርኩት፡ ነገር ሁሉ **በሶስት** ይሞላል። ምጽአቱም በሦስት ነው፡- መጀመሪያ፡ ሙሽራውን ሊቤዣት መጣ፤ ሁለተኛው ጊዜ፡ ሙሽራውን ሊወስዳት መጣ። ልክ እንደ ፍቅር ጨዋታ፡ አመሻሽ ላይ መጥቶ ሰርቋት ሄደ፡ ከዓለምም አወጣት፡ "በአየር ላይ አገኘችው።" የጌታ ምጽአት ምስጢር፡ አያችሁ። በሁለተኛ ጊዜ የሚመጣው፡ ሙሽራውን ለመቀበል ነው። የመጀመሪያው፡ ሊበዣት፡ ሁለተኛው፡ ሊቀበላት፡ እና ሦስተኛውም፡ ከእሷ ጋር አብሮ፡ ንጉሥ እና ንግስት ይሆናሉ!

192 እዚህ ላይ ደግሞ በአሕዛብ ላይ ለፍርድ ተመልሶ ይመጣል። ጳውሎስ ሲናገር፡ "ከእናንተ አንዱ ከባልንጀራው ጋር ሙግት ቢኖረው ትንሽ ነገር ልትፈርዱ አትበቁምን? በቅዱሳን ፊት በመፋረድ ፋንታ፡ በዓመፀኞች ፊት ሊፋረድ ይደፍራልን? " ለክርስቶስ እና በጎኑ ላሉት የተሰጠ ፍርድ ይህ ነው፡ እነኛ ጠበቆች ናቸው፡ እነሆ እርሱም በዙፋኑ ተቀመጠ። እነኋት ጠበቃዋ፡ ሙሽራይቱ ናት።

193 እነዚያም ደግሞ እነሆ መጡ። መጻሕፍትም ተከፈቱ፡ ሌላ መጽሐፍ ማለት የሕይወት መጽሀፍም ተከፈተ።

194 እንግዲህ፡ የተጣለው የመጀመሪያው መጽሐፍ፡ የኃጢአተኞች መጽሐፍ ነው። እሺ። ከጅምሩ የተወገዘ ነውና። እነሆ ፍየ—ፍየሎች ናቸውና። ተስፋ የለውም፡ አያችሁ፡ ከጅምሩም ኃጢአተኛ ነውና። እሺ፡ በቃ፡ ተጣለ።

195 በጎቹ ግን፡ ፍርድ ፊት ቆሙ። መፈረድም ነበረባቸው፡ ቅዱሳንም ይፈርዱባቸዋልና። እግዚአብሔር አመጻኛ አይደለም። በምድሪቱ ጥግ ላይ አረማውያን እያሉ፡ እኛ ግን መልእክቱን እነርሱ ጋር ከማድረስ ይልቅ የሰምንት-እና የአስር-ሚልዮን-ዶላር የወርቅ መቅደሶችን እዚህ አሜሪካ ላይ ብንገነባ፡

እግዚአብሔር እኛን ተጠያቂ ያደርገናል፡ እነርሱን ግን ያድናቸዋል። አዎን! እግዚአብሔር አመጸኛ አይደለም።

196 እናንተ—እናንተ ራሳችሁ፡ ይህ ነገር ከዚህ በፊት ባትረዱት ኖሮ፡ ተጠያቂ ባልሆናችሁ—ነበር፡ አሁን ግን ተጠያቂ ናችሁ! አያችሁ? ሁላችሁ ተጠያቂ ናችሁ... እኛ ይህን መልእክት ለማድረስ እንጠየቃለን፡ እናንተም ስለመስማታችሁ እና አለመስማታችሁ ትጠየቃላችሁ።

197 አሁን፡ አረማውያን፡ ማለት በዚያ በቤተ መቅደስ የሚያመልኩ ይነሣሉ። ከዚህ የተሻለ አያውቁም። ምንም ነገር አያውቁም። እግዚአብሔር አመጸኛ አይደለም፡ እድል ካላገኙ በቀር አይኮንናቸውም። እና ቦታ ይመደብላቸዋል።

198 በቤተክርስቲያንም ውስጥም፡ እያንዳንዱ ዘመን በዚህ የቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ ከ—ከኤፌሶን ወደ ታች **ወደዚህ፡** መልእክቱ፡ እውነተኛው የክርስቶስ መልእክት መጀመሪያ ላይ እንደነበረው (የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ ኃይሉ፡ ትንሣኤ፡ በልሳኖች መናገር፡ በልሳኖች መናገር፡ የፈውስ ስጦታ፡ በጌታ በኢየሱስ ስም መጠመቅ፡ እነዚያ እሱ ያስተማራቸው ነገሮች)፡ በሙሽራዋ ውስጥ ያለ እያንዳንዱ አካል እንደ ጠበቃ ይቆማል።

199 እነሆ የአንድ ሰው ጉዳይ ይነሣል፦ "**በእገሌ-እና-እገሌ** ዘንድ ጉባኤ አካሂዳችሁ ነበር፡ እሱን ነግረኸዋልን? "

200 አሁን ጠበቃው፦ "አዎ፡ ነግሬዋለሁ።" በመጽሐፉ ውስጥ ስለሚኖር፡ ማታለል አትችሉም፡ ሃሳቦቻችን ሳይቀር በዚያ ውስጥ ናቸው። አያችሁ? በዚያ ማታለል አትችሉም። "አዎን፡ መጠመቅ እንዳለበት በደንብ ነግሬዋለሁ።"

"በጄፈርሰንቪል፡ በዚያ፡ በተበርናክሉ ውስጥ? "

"አዎን፡ ጌታዬ፡ እ—እ... አንተ... "

201 "አዎን፡ እዚህ መጽሐፉ ላይ አለ፡ ማድረግ **ያለባቸው** ነገር ነግራሃቸዋል። እንዲያውም ቅዱሳት መጻሕፍትን መርምረው ትክክል እንደሆነ አውቀውታል፡ ይሁን እንጂ አልታዘዙም።"

202 "ከእኔ ራቁ፡ እናንተ ዓመፀኞች፡ አላውቃችሁም።" አያችሁ?

203 ፍየሎችን ከበጎች የሚለየው በዚያ ነው፡ አያችሁ፡ ከፊሎች በቀኝ በኩል ከፊሎቹም በግራ በኩል አቆማቸው። አሁንም እነሆ ሶስቱ መደቦች ታያላችሁ።

204 ነገር ግን፡ **ይህ** ምድብ ግን **ከዚያ** ምድብ ጋር በጭራሽ አብሮ አይሆኑም፡ ያቺኛዋ ሙሽራ ነች። አሁንም፡ አስተውሉ፡ ሙሽራይቱ ከእርሱ ጋር በቤተመቅደስ ውስጥ ናት። ሌሎቹ ይሰራሉ ወደ መንግስቱም ክብር ይሰጣሉ፡ ሙሽራይቱ ግን ዘወትር ከሙሽራው ጋር ናት። ሌሎቹ በጭራሽ አይወርሱም፡ እንደ **እነዚህ** ያሉቱ፡ አይጣሉም፡ አገልጋይ ይሆናሉ፡ እንደ በጎች ከፍየሎች መካከል ለይቷቸዋልና። እሱ ግን...

205 ፍየሉ ግን ስለዚያ ነገር ምንም ግንዛቤ የለውም፡ ምንም ግድም አልሰጠውም። ፍየል ነበር፡ በፍየልነቱ የረካ ነው፡ እናም እንደ ፍየልነቱ ይሞታል መጨረሻውም ያ ነው። ያ ብቻ ነው፡ አያችሁ።

206 በጉ ግን፡ እርሱ ከሆነ... እግዚአብሔር ይዞኝ ምንም ነገር ከማይሰሙ አሕዛብ ጋር በዚያ ቆሜ ነበር። ስለዚህ ይህን ወንጌል ለሰዎቹ ስትሰብኳቸው...

207 እኔም መቅረቤ አይቀርም። በቅርብ ጊዜ ያሳየኝ ያንን ታላቅ መነጠቅ ትዝ ይላችኋል፡ በእዚያም ከሕዝቡ ጋር አብሬ ነበርሁ—ሰለ እነርሱም እኔ ተጠያቂ እንደነበርሁ ታስታውሳላችሁ? እኔም እነዚያን ሚሊዮኖች በዚያ ቆመው አይቼ፡ እንዲህ አልኩ፡ "እነዚህ ሁሉ የብራንሃም ልጆች ናቸውን? "

አለኛም፡ "አይደሉም።" "እነዚህ በአንተ ሰብከት የተቀየሩ ናቸው፡" አለኝ።

እኔም እንዲህ አልኩ፡ እ—እ "ኢየሱስን ማየት እፈልጋለሁ፡" አልኩ።

እንዲህ አለኝ፡ "አሁን አትችልም። ለመምጣት ጥቂት ጊዜ ይቀረዋል። አስቀድሞ ግን ወደ አንተ ይመጣል በሰበክከው ቃል መሰረት ትፈርዳለህ፡ እምነታቸውም በዚያ አርገዋልና።"

እኔም "በሁሉም እንዲሁ ይደረጋልን? ጳውሎሰሰ ይቀርባልን፡" በማለት ጠየቅኩት?

"አዎን፡ ጳውሎሰም፡ ከሰበካቸው ወገኖች ጋር አብሮ ይቀርባል፡" አለኝ።

እኔም "እሱ የሰበከው መልእክት እኔም ሰብኬዋለሁ፡" አልኩት።

208 ሚሊዮኖች እጃቸውን ወደ ላይ አነሱና እንዲህ አሉ፡ "እኛም እምነታችን በዚያ አሳርፈናል!" ይኸው፡ አየህ፡ ይህ ነው! አዎን። አለኛም፡ "ከዚያም በኋላ የሚበላ፡ እና የሚጠጣ አካል ያላቸው ሆነን ወደ ምድር እንመለሳለን፡ በዚያም ማለቂያ ለሌላቸው ዓመታት አብረን እንኖራለን።" ያ ማለት የጌታን መምጣት ነው። እሺ።

209 አሁን፡ አንድ ደቂቃ ብቻ። አሁን፡ እ... እየተጠጋሁ ነው፡ ምክንያቱ እየደረሰ ነው... ወንድማችን ለጥምቀት አገልግሎት ወይም ለሚጠቀምበት ጊዜ እየደረሰ ነው።

210 እሺ፡ አሁን፡ በዚህ የቤተክርሰቲያን ዘመን ውሰጥ ነው። ኦህ፡ በጣም የሚገርም ነገር አለው። በጣም ተመችቶኛል። በእነዚህ የቤተ ክርሰቲያን ዘመናት መካከል፡ **እዚህ** ጋር እስከ መጨረሻ ድረስ ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ሥራ የሚሠሩ ሁለት መናፍሰት አሉ፡ አንደኛው የኃይማኖት ተቋም ሲሆን፡ ሁለተኛው መንፈስ ቅዱስ ነው። ኢየሱስም "የሚቻል ቢሆን ኖሮሰ የተመረጡትን እንኳ እሰኪያስቱ ድረስ እጅግ ይመሳሰላሉ፡" አለ። እነዚህ ሁለት መንፈሶች ለወደፊቱ ፍርድ በህዝቦቻቸው ላይ ምልክት እያደረጉ ይገኛሉ። ሰይጣን ቃል እንደገባ... ከክርሰቶሰ የበለጠ እሰበሰባለሁ አለ፡ እንዲሁም ነው። አሁን፡ ይሄን ተመልከቱ፡ አሁን ወደዚህ ሰንገባ በደንብ ተከታተሉ፡ ከአቅሙ በላይ፡ ሰዎችን ምልክት ያደርግባቸዋል።

211 ብዙዎች እንደ ሔዋን ናቸው። ሔዋን ለመታለል አልዘገየችም። ባትቆም ኖሮ፡ ማታለል በጭራሽ አይኖርም ነበር። ሔዋን ግን ቆመች፡ በቆመች ጊዜ፡ የሚያታልላት ነገር ተቀበለች። መንገዷን ከመቀጠል ይልቅ... እየ—እየተከታተላችሁ—በደንብ እየተከታተላችሁኻ ነው? ሰሙኻ! ሔዋን የተታለለችበት ምክንያት... እንደተረዳችሁት እርግጠኛ እንድሆን፡ አብረን እንበለው፡ "ሔዋን የተታለለችበት ምክንያት፡ የእግዚአብሔርን ቃል በሙላት ሰላልጠበቀች ነው።" ሰይጣን ነገሩን ጠቅሶላታል፡ ነገር ግን እውነቱን **በሙሉ** አልነገራትም። የኃይማኖት ተቋሙም እንዲሁ ነው። እያችሁ? የቃሉ አካል ለመሆን ግን እጅግ ዘገየች፡ ቃሉንም **በሙላት** አልተቀበለችም።

212 የዛሬ ችግርም እንዲሁ ነው፡ ሰነፏ ድንግል የቃሉን ክፍል ለማግኘት እጅግ ዘገየች ቃሉን **በሙላት** ግን አይደለም። የተታለለችው ቤተ ክርስቲያን የቃሉን ክፍል ለማግኘት እጅግ ዘግይታለች ቃሉን **በሙላት** ግን አይደለም፡ እጅግ ቅኖች እና የቀኑ ነበሩ። ሔዋን ተታላለች! መጽሐፍ ቅዱስ “ተታለለች፡” ይላልና።

213 አዳም አልተታለለም። አዳም ስህተት እየሰራ መሆኑን በትክክል ያውቅ ነበርና፡ ሚስቱ ግን፡ የምታደርገውን በማድረግ፡ እርሱ ከተከለከለው እንዲካፈል—ታባብለው ነበር። ለምን፡ ሰው ነበር፡ አያችሁ፡ እና—ለእርሱ እጅግ... ገብቷችኋል፡ አያችሁ፡ እሱ ስህተት እየሰራ እንደሆነ ያውቅ ነበር፡ ሔዋን ግን ትክክል እየሰራች እንደሆነ አሰበች።

214 አቤት፡ አይታያችሁም ወይ? ለዚህ ነው ጳውሎስ ሴት በፍፁም ወንጌልን መሰበክ የለባትም ያለው። ኧሃ-ሃም። የተታለለችው... እሷ—እሷ ራሷ ነበረች። “ሴት ዝም እንድትል እንጂ፡ እንድታስተምር፡ ወይም ሥልጣን እንዲኖራት አልፈቅድም።” አያችሁ? “አዳም—ቀድሞ ተፈጥሯልና፡ በኋላም ሔዋን። አዳምም አልተታለለም፡ በመተላለፍ፡ ተታልላ ወደቀች።” እንዲህ አለ፡ “ቢሆንም፡ አሁን፡ እሷ አልጠፋችም፡ በመውለድ ትድናለች (ባል ካላት)፡ እና ሌላው፡ በእምነት እና በቅድስና እና ራሷን በመግዛት፡ ከኖረች፡ ትድናለች። ሰው እንድታስተምር ወይም ሥልጣን እንድትይዝ ግን ፈጽሞ አይፈቅድም!” አያችሁ? ጳውሎስ አለ፡ “እንዳታደርጉት!” አለም፡ “እንግዲህ፡ የጌታን አሳብ ያለኝ ይመስለኛልና፡” ብሏል።

215 እነርሱም “እንዴት፡ ለምን... እነዚያ፡ ነብያቶች ሁሉ ‘ሰበኩ’ ይሉናል፡” አሉት።

216 እርሱም፡ “ምነው? የእግዚአብሔር ቃል ከእናንተ ዘንድ መጣን፡ ወይስ ከእናንተ ዘንድ ወጥቷልን? ማንም ራሱን መንፈሳዊ ወይም ነቢይ የሆነ ቢመስለው፡ እኔ የምለው ነገር የጌታ ትእዛዝ እንደ ሆነ ይወቅ።” አያችሁ? ይህ እውነት ነው። የሚናገረውን ያውቅ ነበርና።

217 ግን አለ፡ “የማያውቅ ቢኖር ግን፡ አይወቅ። አለቀ። አይ—አልስማም የሚል ካለ፡ እንግዲህ፡ ይቀጥላል፡ ይሂድ ገደል ይግባ። አያችሁ፡ ቀጥል እንግዲህ።” እዚያ ግን፡ እነኚያ ሁለት መንፈሶች።

218 ምክንያቱ። ልክ በየጎዳናው፡ ሴቶችን በፖሊስ ሃይል እንዳስታጠቁ ነው። እናቶችን በመንገድ ላይ ማስታጠቅ፡ ለአሜሪካ ባንዲራ ነውር ነው። በአስር ሺዎች የሚቆጠሩ ወንዶች ሥራ አጥ ሆነው ሳሉ! ለምን፡ የሴት አገር ስለሆነች፡ የሴት ምድር ናት፡ ሴት ድል ታደርጋለች። የሴት-አምልኮ ነው። ይህ ሴትን እንደ አምላክ የማምለክ፡ የካቶሊክ ዶግማቲክ መንፈስ ነው። ይሄው ነው... በትክክል ተቀምጧል፡ ቅንብሩን አይታያችሁም?

219 እግዚአብሔር ለአንድ ሰው ከሚስት የበለጠ፡ ከእውነተኛ ሚስት የበለጠ ጣፋጭ ነገር አይሰጠውም። ከዚያ በላይ ልሁን ባለች ጊዜ ግን፡ ት— ትወጣለች። በትክክል ትክክል ነው። እግዚአብሔር ሴቶችን በእነዚህ ቦታዎች እንዲገቡ እና እነዚህን ነገሮች እንዲሠሩ ፈጽሞ አይፈልግም። እነዚህ ሴቶች፡ እንደው... ልጆች እንዲወልዱ እና ልጆቻቸውን ማሳደግ አለባቸው። ሁሉም ሰባኪዎች ናቸው፡ እያንዳንዳቸው፡ ከልጆቻቸው ጋር በቤታቸው የራሳቸው እረኝነት አላቸው፡ ይህም ልጆቻቸውን ማሳደግ ነው። እሺ።

220 አሁን፡ ሁለቱ መንፈሶች፡ ከሞላ ጎደል ይመሳሰላሉ። ልክ እንደ ሔዋን፡ ልክ... እንደ፡ ሰይጣን፡ እንዲህ አላት፡ “እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል... ”

“ኧሃ-ሃም።”

“እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል... ”

“ኧሃ-ሃም፡ ልክ ነው።”

“እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል... ”

“ኧሃ-ሃም።”

221 “እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል፡ ግን፡ ኦህ፡ በ ‘አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ፡’ ሰም ብንጠመቅ አይኮንነንም። ያንን ጽድቅ መሆን አይችልምን? ” አንተ ከንቱ ግብዝ! አዋን፡ ወዳጄ። እግዚአብሔር ፈጽሞ **እንዲህ** ብሎ አያውቅም!

222 ለማንኛውም፡ እንደዚህ ያለ ነገር የለም። ሙት ነው! እንደዚህ ያለ ነገር የለም! “አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ” የሚባል ሰም የማን ሰም እንደሆነ ንገሩኝ። እንደዚህ ያለ ሰም የለም፡ እንግዲያውስ ሙት ነው! ከየት የመጣ ነው? ከ “ከሞተው” ቤተ ክርሰትያን፡ ከ **ሰርዴስ** ነው። እንደዚህ ያለ ነገር የለም! “‘ህያው’ እንደመሆንህ ሰም አለህ፡ ‘የክርሰቲያን ቤተ ክርሰቲያን ነኝ’ ትላለህ፡ ሞተህማል!” እውነት ነው፡ “አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ” ተብሎ የሚጠራ ሰም የለም።

“ኦህ፡ እሺ፡ ታዲያ ያ ጥሩ አይደለምን? ”

223 አይደለም፡ ጳውሎስ አይደለም ብሏልና፡ እንዲህ በማለት፡ “ካመናችሁ ወዲህ መንፈስ ቅዱስን ተቀበላችሁን? ”

“መኖሩ አለመኖሩን እናውቅም... ”

224 “ታዲያ እንዴት ተጠመቃችሁ? ” አላቸው፡ “ኑ እና እንደገና በኢየሱስ ክርሰቶስ ሰም ተጠመቁ!” አላቸው፡ እንዲህ አለ፡ “መልአክ ከሰማይ ቢመጣ፡ ሌላ ነገርም ቢያሰተምር፡ የተረገመ ይሁን!”

225 እውነቱ ይህ ነው! ተጠያቂ የምሆነው ሰለ ተናገርኩት ብቻ ነው። ሰለ እናንተ አለመሆኑ፡ መቼም ይገባችኋል፡ እኔ የምጮህባቸው እነዚህ ቴፖች ላይ ነው፡ አያችሁ፡ ምክንያቱ (ወደ ሁሉ) አቅጣጫ ይላካሉና፡ ሰለዚህ ነገሩ ይህ ነው። እሺ። ሌላ አይደለም...

226 ሄዋን ተታለለች፡ የቃሉን ክፍል ብቻ አየች። ሞዓብ ተታለለ። ሰነፏ ድንግል ተታለለች። ቤተ ክርሰቲያን ተታልላለች። የኃይማኖት ተቋማት ሁሉ ተታልለዋል። አያችሁ?

227 ከቃሉ ጋር ወግኑ! ብቸኛው መንገድ ይህ ነው። በሱ ዘንድ ጽኑ፡ ከእሱም ፈቀቅ አትበሉ። በሱ ዘንድ ጽኑ፡ እግዚአብሔር ወደ ተናገረው ነገር አድሉ። ሌላ ሰው ምንም ቢናገር፡ የእግዚአብሔርን መሰመሮች ጠብቁ።

228 እንግዲህ፡ ሰለ ሰነፏ ድንግል፡ እንደምናውቀው፡ ሰፍራዋን ለቃለች። በፍርዱ ፊት ትቀርባለች። እውነቱን ሰምታ ከሆነች፡ ትወገዛለች። ይህ እውነት ነው። ኢየሱስን እናንተ በተዋችሁት ቦታ በቀር ሌላ ሰፍራ አታገኙትም።

229 ይሁዳም መጣ... አስታውሱ! “ሰለ ሰነፏ ድንግል’ ‘የምትመራው በዲያብሎስ ነውን፡’ ትላላችሁ? ” በትክክል! “አሁንም ኑሮዋ ንጹህ

ስትሆን?" አዎን፡ ወዳጄ። ይሁዳም እንዲሁ ነበርና፡ የዳነ፡ የተቀደሰ፡ የመለኮታዊ ፈውስ ሰባኪ፡ አጋንንት አውጪ ነበረ። ለምን፡ እሱም ልክ ነበረ፡ ከሞላ ጎደል ከሌሎቹ ጋር ተመሳሳይ ነው። ወደ ጴንጤቆስጤ ሲደርሱ ግን፡ ቀለሞቹን ያሳየው ያኔ ነው። መንፈስ ቅዱስን አልተቀበለም፡ ተረከዙን ሰበቅ አርጎ ጌታ ኢየሱስን ካደ። አብያተ ክርስቲያናት ያደረጉትም ይህንኑ ነው። ወደ ጴንጤቆስጤ በረከት ሲደርሱ፡ ከርሱ ራቁ። ኦህ፡ ተማሪዎች ሆይ፡ አይታያችሁም ወይ?

230 ኦህ፡ ዛሬ ማታ ታላቁ የማዕዘን ድንጋይ። እስኪ አንድ አፍታ፡ ምናልባት ጥቂት ጊዜ ስለሚኖረን፡ ሌላ ነገሮች ልዳስስ። እናንተን አንድ ነገር ማሳየት-... እፈልጋለሁ—የአውሬው ምልክትን። የአውሬው ምልክት፡ ለአፍታ ያህል፡ ወደ ራእይ 13 እንሂድ። ራእይ 13፡15 ላይ፡ ምን እንደሚያደርግ... የሚለውን እናንብብ። የዮሐንስ ራእይ 13:15፦

> **ለምስሉም ሕይወትን ሊሰጥ ሥልጣን ነበረው...** (አሁን፡ ማለትም፡ "ለፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት፡ ለፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት።")

231 እርሱ ሰልጣን ነበረው፡ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት፡ ምስልን ሰርተዋልና። ይህም በ—በ አብያተ ክርስቲያናት ካውንስል በኩል፡ የፕሮቴስታንት ህብረቶች ሁሉ አንድ ሆነው የሚያመልኩበት ቦታ እያዘጋጀ ነው። ለዓለም አብያተ ክርስቲያናት የገነቡት ታላቅ የአንድነት ሕንፃ እንዳለ የምታውቁ ወይም ያነበባችሁ አላችሁ? በትክክል። አያችሁ? እዚያ... እዚያ ነው አሁን፡ ልክ እንደ U.N. መንግስታት ነው። ሁሉም በዚያ ውስጥ አሉበት፡ እያንዳንዳቸው፡ አሴምብሊስ ኦፍ ጋድ ሳይቀር። በዚያ ውስጥ ናቸው! አሉበት፡ አያችሁ። ውሻውን-ውሻ-በላው ነገር ነው። "እርያ ወደ ጭቃው፡ ውሻም ወደ ትፋቱ እንደተባለ ነው፡" እንደ ድሮ ወደ ኋላቸው ሆኑ (በትክክል!)፡ የወንጌል አቋማቸውን መካድ ማለት ይቻላል። እነሆ እናንተም ደግሞ፡ ታላላቅ መሆን ተመኛችሁ፡ እስራኤል የሌሎች ነገሥታት አይተው እንዳደረጉት፡ እንደ ሌላው ዓለም መሆን ትፈልጋላችሁ "ንጉሥ አንግሰልን አሉ።" አያችሁ?

> **እርሱም...** **ለአውሬው ምስልን** ያደርጋል፡ **የአውሬው ምስል ደግሞ ይናገራል፡ እንዲሁም ደግሞ... ለአውሬው ምስል የማይሰግዱ ሁሉ...**

232 ይህ የአውሬው **ምስል**፡ "የፕሮቴስታንት ተቋም ነው፡" ካቶሊክ አይደለችም። እዚህ ጋር የሚናገረው ስለ አሜሪካ ነው፡ አያችሁ፡ ምክንያቱ 13ኛው ምዕራፍ ስለ አሜሪካ ነውና። የሚወጣው አውሬ... አያችሁ፡ አውሬዎች ሁሉ **ከውኃ** የሚወጡ ናቸው፡ ይህም "ከሰፊው ህዝብ እና ከወገኖች" መካከል ማለት ነው። እዚህ ያለው አውሬ ግን፡ ሰው ካልነበረበት ምድር፡ እንደ በግ ይመጣል፡ ሁለት ቀንዶች ነበሩት፡ እንደ ዘንዶም ይናገራል። በአውሮፓም ለነበረው የአውሬውን ምስል አደረጉ፡ ይህንም ምስል በዚህ ሰፍራ አደረጉለት። እና አብ-... አብያተ ክርስቲያናትን አንድ በማድረግ የፕሮቴስታንት ህብረት መሰረቱ፡ ከዚያም ሌሎቹን አብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ያስገድዳሉ፡ የዚህ የአውሬው ምስል ካልተቀበሉ መግዛትም ሆነ መሸጥ ወይም ሌላ ነገር ማድረግ እንደማይችሉ ይደረጋሉ።

233 አሁን እዚህ ምን እንደሚፈጠር ተመልከቱ፦

> **ሁሉንም ለዚህ** ይዳርጋቸዋል፡ **ታላላቆች እና ባለጸጎች... ድሆችም፡ ነጻ የሆኑት... የታሰሩትም፡ ሁሉ... ምልክቱን በቀኝ እጃቸው፡ ወይም በግንባራቸው፡ እንዲቀበሉ ያደርጋል፤**
>
> **ይህም ምልክቱን፡ ወይም የአውሬውን ስም፡ ወይም የሰሙ ቁጥር፡ እስኪቀበሉ** ድረስ... **ማንም እንዳይገዛ እንዳይሸጥ ይከለክላል።**
>
> **ጥበብ በዚህ አለ። አእምሮ ያለው የአውሬውን ቍጥር ይቍጠረው፤ ቁጥሩም... የሰው ቁጥር ነውና፡ ቁጥሩም ሰድሰት መቶ ሰልሳ ሰድሰት ነው።** (ማን እንደሆነ እናውቃለን፡ የሮም የሰልጣን ተዋረድ ነው፦ ጳጳሱ።)

234 እኔ በዚያ ሄጃለሁና እኔ ራሴ አይቼ፡ አውቄዋለሁ፡ በዚያ በቦታው ላይ (በዙፋኑ፡ በነበረው) **እዚህ** ጋር ልክ በካቶሊክ ዘመን መጀመሪያ ላይ ቦኒፌስ፡ ሣልሳዊ፡ በዚያ ላይ ሾሙት። በዚያም Vicarivs Filii Dei ተጽፎበታል፡ ትርጉሙም "በእግዚአብሔር ልጅ ምትክ" ማለት ነው። **ዴይ፡ ዴይ፡** "አምላክ" ነው፡ አያችሁ። አያችሁ፡ "በእግዚአብሔር ልጅ ምትክ።" በሌላ አባባል፡ "በምድር ላይ የተቀመጠ የእግዚአብሔር ልጅ ተወካይ ነው፡" አያችሁ፡ "መጽሐፍ ቅዱሰን ለመለወጥ ሥልጣን ሁሉ ያለው፡" የሚፈልገውን ነገር መለወጥ ይችላል። ስለዚህም፡ "'ሰላም ለኪ ማርያም' ይላሉ!" ጳጳሱ ምን አሉ? "'ሰላም ለኪ ማርያም'! እንበል አሉ" ያ በቂ ነው። ኧሃ-ሃም፡ ኧሃ-ሃም። "እሺ፡ **እንዲህ-እና-እንዲያ** እናደርጋለን።" ጳጳሱ ካለ፡ በቂ፡ በቂ ነው። "በእግዚአብሔር ልጅ ምትክ።"

235 በቅርብ ጊዜ "ማርያም አልተቀበረችም" የሚል ዶግማ ነበራቸው፡ (መቃብሯንና የተቀበረችበትንም ምልክት ሁሉ አለ።) "አይደለም፡ እንደገና ተነሳች እና አረገች፡" ይላሉ። ጳጳሱ "ይህ ነው፡" ካለ! ይህ ነው። "እሱ የማይሳሳት ነውና፡ አያችሁ፡" ጳጳሱ አዟልና። አያችሁ፡ "በእግዚአብሄር ልጅ ምትክ።"

236 እንዲህም አለ፡ "አሁን፡ አውሬው ማን እንደሆነ፡ ኃይሉ ከየት እንደመጣ ለማወቅ የሚፈልግ ቢኖር፡" "ጥበብ ያለው ቁጥሩን ይቁጠረው... " ይላል፡ ስለዚህ፡ ጥበብ፡ ከመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች አንዱ ነው። አያችሁ? ጥበብ ያለው የሰውን ቁጥር ይቁጠረው፡ ይህን... የአውሬውን ቁጥር ይቁጠረው፡ የሰው ቍጥር ነውና፡ ቁጥሩም ሰድሰት መቶ ሰድሳ-ሰድሰት ነው። አሁን፡ ይህን እንውሰድ... እና ያንን ሰም እንቁጠረው፡ V-i-c-o፡ እና—እንደ ቅላቶቹ መሰረት፡ እዚህ አንድ መሰመር እንሳል እና... የሮማን ቁጥሮቹን እንጻፋቸው፡ ከዚያ በኋላ ውጤቱ ሰድሰት መቶ ሰድሳ-ሰድሰትን ታገኛላችሁ። ይህ እውነት ነው።

237 "አሁንም ኑ የአውሬ ምሰል እንሥራ።" በዚህች አገርም ምሰልን ሠሩ፡ ይህም የኃያምኖት ተቋማት የአንድነት ኮንፌደሬሽን፡ ኒቆላውያን ተሰብሰበው ራሳቸውን ተቋም ማድረጋቸው ነው። በመጨረሻም ይህንን ወንድማማችነት አንድ ያደርጋሉ፡ እንደ ካቶሊክ አይመጡም፡ ነገር ግን ኮሚኒዝምን ለማጥፋት እንደ ወንድማማችነት ኅብረት ይሆናሉ።

238 መጽሐፍ ቅዱስ ኮሚኒዝምን እግዚአብሔር ያስነሳው እንደሆነና አሕዛብ በእግዚአብሔር ልጆች ላይ ስላደረጉት ነገር ለመበቀል ሊጠቀምበት እንዳስነሣው ይናገራል። ይህ በትክክል እውነት ነው። እንዲህ ይለዋል፡ “እነርሱም—ኃይላቸውንና ሁሉንም ነገር—ለአውሬው ለአንድ ሰዓት ይሰጡታል፡ እና ያፈሰሱትን፡ የ… ህዝቡን ደም ለመበቀል።” እና ያ የአቶሚክ ቦምብ ወይም ምንም ይሁን ምን የቫቲካን ከተማ ሲመታት፡ ከእንግዲህ ወዲያ የሮማውያን የሰልጣን ተዋረድ አይኖርም፡ እንዲህም እንደተባለ፡ “በእርሷም በዓለም ላይ የተገደሉትን የሰማዕታት ሁሉ ደም ተገኘባት።” እነሆ እሷ ይህች ናት። የተዘጋጀላትም ምስል ይህ ነው፡ የአብያተ ክርስትያናት ኮንፌደሬሽን።

239 እነዚያ ደጆች የምንዘጋበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም፡ ይህ እውነት ነው፡ ካልሆነ ግን የተቋም ምልክት እንቀበላለን። ደጆችን መዝጋታችን አይቀርም፡ ትክክል ነው፡ እንዲህ ይሆናል… ከዚያ የተሻለ እናውቃለንና።

240 አሁን፡ ከመሄዳችን በፊት፡ በሚቀጥሉት ጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ፡ አሁን የምፈልገው፡ የመጣበቡ ክፍልን ነው። አሁን፡ የእግዚአብሔር **ማኅተም** “መንፈስ ቅዱስ” ነው። ይሄን የማያውቅ የለም፡ አይደል? በጣም ጥሩ፡ መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር ማኅተም እንደሆነ፡ ሁላችንም እናውቀዋለን። አሁን ያን የምታገኙት… ራእይ 9 ክፈቱና—9፡1 እስከ 4 ድረስ፡ ሁሉም ግንባራቸው ላይ ማህተም እንደነበራቸው ታገኛላችሁ። 1ኛ ቆሮንቶስ 1:22፣ ጳውሎስ እንዲህ ይላል፡ “እስከ ቀኑ ድረስ በመንፈስ ቅዱስ አትሞናል… ” ኤፌሶን 4፡ 30 ላይ፡ እንዲህ ይላል፡ “መንፈስ ቅዱስን አታሳዝኑ፡” በግምባራቸው ላይ ለማተም የሚወጣው ያ መልአክ ነው። እንግዲህ፡ ይህ ማለት… ግንባራቸው ላይ ነጥብ ይቀባቸዋል ማለት አይደለም፤ ግንባራችሁ ማለት መገለጣችሁ ነው፡ አያችሁ፡ እጃችሁ ማለት የነገሩ ሰራችሁ ነው። አያችሁ፡ መንፈሳዊ ምልክት ነው። አያችሁ? ትልቅ ማኅተም ይዞ **እንዲህ** አያትማችሁም። ኡህ፡ ኖ።

241 ከጥቂት አመታት በፊት እነዚያ N.R.A. በወጡ ጊዜ፡ **ይህ፡ ያ** ነው፡ ወይም ሌላ እንደተናገሩት… ቀድሞውኑ ያለ ነገር ነውና፡ አትፈልጉት። መጽሐፍ ቅዱስ እዚያ መመለስ ጀምሯል፡ አሁን ሊያልቅ ተቃርቧል ብሎታል። አያችሁ? እውነት ነው።

242 እርሱ ግን የታተሙትን ምልክት አደረገባቸው። አያችሁ? አሁን፡ የመጀመሪያው ማኅተም እንዴት—እንዴት ነበር፡ ምን ይመስል ነበር? በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፡ በትክክል፡ ያን ጊዜም ስራቸው የክርስቶስ ስራዎች ነበሩ። በድውያን ላይ እጃቸውን ጫኑ እነርሱም ዳኑ፡ ምልክት ድንቅና ተአምራትን ሁሉ አደረጉ። በግምባራቸውም፡ በመገለጥ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታተሙ፡ ከእርሱ ጋር አብረው—አብረውት (የክርስቶስ—አምላክነት) ይሰሩ ነበር፡ ምልክቱ ያ ነው።

243 እናንተም እንዲህ የምትሉ፡ “እሺ፡ አሁን፡ እሱ ሶስተኛ አካል፡ ወይም ሁለተኛው አካል ነው-… ” ገና ማኅተሙን አልተቀበላችሁም፡ ስለዚህ በቃ—ተውት። አያችሁ፡ ጨርሳችኋል፡ እዚያው ከሉኮቹ መካከል ወጥታችኋል፡ ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲህ ብሎ ነገር የለም። “ክብር… በቅድስተ ስላሴ እናምናለን።” እጅግ ርቃችኋል… ሉኮቹ ላይ እንኳን አይደላችሁም፡

እያችሁ፡ ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ **ሥላሴ** የሚባል ነገር እንኳን አልተጠቀሰም። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ **ሥላሴ** የሚለውን ቃል ፈልጉትና ኑ።

244 [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]... ? ... በወልድ፡ ልጅነት ተብሎ በሚጠራ፡ አሁን እርሱ በእናንተ ውስጥ ነው፡ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ ያው አምላክ ነው። መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ነበር። "ትንሽ ጊዜ አለ ከእንግዲህ ዓለም አያየኝም፡" ኢየሱስም፡ "ከእግዚአብሔር ዘንድ መጥቻለሁ፡ ዳግመኛም ወደ እግዚአብሔር (ወደ መንፈስ ቅዱስ) እመለሳለሁ። እስከ ፍጻሜ ድረስ፡ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡ በውስጣችሁም እኖራለሁ (በፍጻሜው ላይ)። እስከ መጨረሻው ድረስ፡ ልክ እንደዚያ በእናንትየ ዘንድ እገኛለሁ... እኔ የማደርገውን ሥራ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ። እኔ እያደረግኳቸው የነበሩት ነገሮች በእናንተ ዘንድ ይሆናሉ፡ ይህም እስከ መጨረሻ ድረስ የአማኝ ምልክት ነው። ሂዱና ሰበኩ፡ በጌታ በኢየሱስ ስምም አጥምቁ፡ በመንፈሴም ይሞላሉ፡ እንዲህ ከሆኑ፡ ምልክቶቹ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ያመኑትን ይከተሉአቸዋል። እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ፡ ዘወትር ከእናንተ ጋር ነኝ።" ወደ ክብር አረገ። ያ ነው፡ እና አንድ ቀን እንዲመጣ እየጠበቅነው ነው። እንግዲህ፡ የእግዚአብሔር ማኅተም፡ ያ እንደሆነ እናውቃለን።

245 ስለዚህ አስታውሱ፡ ከአይሁድ መካከል የሚታተሙት አንድ መቶ አርባ-አራት ሺህ ብቻ ይሆናሉ፡ እነዚህም ከአይሁድ የተረፉ ቅሬታዎች ናቸው። በዚህ ውስጥ ግን፡ በአሕዛብ ሙሽራ፡ በአሕዛብ ሙሽራ ውስጥ ግን፡ በዚያ ከታተሙት መካከል፡ እልፍ አእላፋት ጊዜ እልፍ ነበሩ፡ ምክንያቱ እነዚህ ሁሉ በእነዚያ ባለፉት ዘመናት በሙሉ የመጡ ሰማዕት ናቸውና፡ በፍርድ ቀን ይነሳሉ።

246 ያንን እንደ ነሐስ የመሰለ የፍርድ እግር በዚያ ቀን ሲቆም ምን የሚሆን ይመስላችኋል ሰማዕታትም ሁሉ በእነዚያ በሮማውያን ፊት ሲቆሙ (እንደውም ኒቆላውያን ናቸው በእንጨት ላይ እንዲቃጠሉ ለአንበሶች እንዲወረወሩ እና ልዩ ልዩ ነገሮች የፈጸሙባቸው እነሱ ናቸውና)፡ እና እነዚህም እንደ ፈራ-... በወንበራቸው እንደሚቀመጡ ፈራጆች ጠበቆቻቸው በቆሙ ጊዜስ? ዳኛውም በዚያ ወንበር ላይ ተቀምጦ፡ "ወንጌልን ሰብካሃቸዋልን? "

"ስለ እነርሱ ህይወቴን በአንበሶች ጉድጓድ ውስጥ በማኅተም ዘጋሁ።"

247 አቤት፡ ወንድሜ ሆይ! እላችኋለሁ "ከእኔ ራቁ፡" ገሃነም ሲያንሳቸው ነው! ይህ እውነት ነው።

248 "አጥብቀህ ያዝ። እራሳቸውን እንዲህ ብለው የሚጠሩትን አውቃቸዋለሁ... (ኒቆላውያን)፡ ሳይሞሉ እራሳቸውን 'በመንፈስ-የተሞላን' ብለው የሚጠሩ።" ይኸው፡ እያችሁ፡ ይኸው ነው። ኦህ! ከባድ ሰዓት እየመጣ ነው፡ እንዴት ያለ አስፈሪ ጊዜ ነው። እግዚአብሔር ይበቀላል! "እኔ እበቀልለታለሁ፡" ይላል ጌታ፡ "እኔ እከፍላለሁ!" ክፉ ሥራ ሁሉ ፍርዱን ያያል... በህይወታችሁ ያደረጋችሁት ወይም ያሰባችሁት ነገር ሁሉ በፊታችሁ ይቆማል፡ በአእምሮአችሁ ውስጥ ያለፉትን ክፉ አሳቦቻችሁ ሁሉ በዚያ በመግነጢሳዊ ነገር ፊታችሁ ይመጣል። ልጆች ሆይ፡ ንስሐ ግቡ!

249 የምታመልጡበት አንድ መንገድ ብቻ አለ፡ ኑና ወደ ክርስቶስ ግቡ፡ በስውነቱ ውስጥ ወደ ቆሰለባቸው ወደ አምስቱ-ድንቅ ቁስሎች፡ ወደ ተወደዱት

የሰውነቱ አምስት ቁስሎቹ ደርሳችሁ፡ የሚደማውን ደም አይታችሁ በዚያ ስትሸሸጉ፡ "የጥንት አምባ፡ አቅም የለኻም። የጥንት አምባ ሆይ፡ አቤቱ ሸሸገኝ፡" ትላላችሁ። ድንቁን መንፈስ ቅዱስ ተባረኩበት፡ በቃ ሙቱ እና በክርስቶስ አካል ውስጥ ተዘዋወሩ፤ ስለ አዳዲስ ነገሮች፡ ተነሡ፡ ዙርያችሁ አዲስ ዓለም ይሆናልና። ድሮ የምትወዷቸው ሐጢአቶች ከኋላችሁ ቀርተዋል። እነሆ፡ የወደፊቱም ቢሆን፡ አሁንም ያለው ቢሆን፡ ሞትም፡ ከዚያ ሊለያችሁ የሚችል አንዳች ነገር አይኖርም። እስከ ቤዛችሁ ቀን ድረስ፡ በመንፈስ ቅዱስ ታትማችኋል። እሱ ማን እንደሆነ ተገልጦላችኋል። ከሞት ወደ ሕይወት እንደ ተሻገራችሁ በልባችሁ ውስጥ ታውቃላችሁ።

250 እንግዲያውስ የእጆቻችሁን ስራዎች ለማየት ንቁ፡ እያችሁ። ዳግመኛ አትሰርቁም፡ ዳግመኛ ክፉ አታደርጉም። እጆቻችሁ ከደም ሁሉ ንጹሓን ናቸው። ቁሙም፡ ወንጌልን ሰበኩ፡ እውነት የሆነውን ተናገሩ፡ እውነተኛውን ህይወት ኑሩ፡ እውነተኛውን ስራ ስሩ፡ መንፈስ ቅዱስም በእናንተ ዘንድ በየቀኑ ምልክትና ድንቅ ያደርጋል፤ እግዚአብሔር እንዴት እንደሆነ ያሳያችኋል፡ "አንተ የተባረከ ልጄ ነህ እኔም ካንተ ጋር ነኝ፡ ከ—ከጎንህ ነኝ። የትም ብትሆን፡ እኔ ካንተ ጋር ነኝ። በጨለማ ሰዓቶች ውስጥ የትም ቢሆን አብሬ እሆናለሁ።" አቤት፡ እንዴት—እንዴት ያለ መልሕቅ ነው!

> ነፍሴን በእረፍቱ መልሕቅ ሰወርኩ፡
> ክፉውን ባሕር ላለመዞር፤
> አቤቱ፡ የቁጣው የጥልቅ ማዕበል፡ ሊያጥረገርግ ይችላል፡
> በኢየሱስ ዘንድ ለዘላለም ሰላም ነኝ።

251 ሞትም በእነዚህ ቀናት አንድ ቀን እያንዣበበ፡ እንደ ንብ መንጋ በላያችሁ ላይ ሊዘምር ይመጣል፡ ያኔ እንዲህ በሉት፡ "ሞት ሆይ፡ መውጊያህ የት አለ? "

252 ህጻን ሳራ በቀደም ለት ጠዋት እንደጻፈችው፡ ትንሿ ልጄ አሁን ከኋላ ቁጭ ብላለች። እና እኔ የምናገራቸውን ነገሮች፡ እሷ እና የወንድም ኮሊንስ ልጅ፡ ትመስለኛለች፡ ማስታወሻ እየያዙ ነበር። እና እኔና እናቷ፡ ማስታወሻውን እያነበብን ነበር፡ እና "ዘ ቡክ ኦቭ ሪቮሉሽን፡" ይላል። አሜን። እንዲህ አለች... እና መጨረሻ ስለ **ሞት** የተናገርኩት ትንሽ ታሪክ ትዝ ይላችኋል፡ አይደል። **መውጊያ የለውም**፡ ስል ስምታችኋል። ያ ሲነገር እዚህ ነበራችሁን? እያችሁ፡ ሞት አንድ ጊዜ በውስጡ መውጊያ ነበረው፡ አሁን ግን...

253 ሰይጣን ያ ሰው የእግዚአብሔር ልጅ ይሁን አይሁን እርግጠኛ አልነበረም። ሰይጣን ወደርሱ ሲመጣ... እንዲህ ሲለው በዚያ አይታችሁታል፡ "እሺ፡ ተአምራትን ማድረግ ከቻልክ፡ ተአምር-አድራጊ ሰው ከሆንክ፡ እንግዲያውስ ያንን የእግዚአብሔር ልጅ ነህ። እላችኋለሁ፡ ያንን... በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፏል፡ እያችሁ፡ እና—እና እንዲህ—ከሆንክ ተአምር ስታደርግ ልይህ። እንግዲህ፡ ርቦሃል፡ ለአርባ ቀናት ምግብ አልበላህም፡ ለምን ያንን ድንጋይ ወስደህ እንጀራ አርገውና ተቀምጠህ ለምን አትበላም? ይህን ስታደርግ ልይህና የእግዚአብሔር ልጅ መሆንህን አምናለሁ።"

254 "ሰው በቃል ሁሉ እንጂ፡ በእንጀራ ብቻ አይኖርም፡" አለው። ኦህ፡ ማይ! እዚህ የገጠመው ሙሴ እንዳልሆነ አውቋል፡ አይደል'ዴ? ሙሴ ትእዛዛቶቹን ጥሎ ሰበራቸው፡ ከሙሴ የሚበልጥ እንደገጠመው ግን ገብቶታል።

255 ያን ጊዜም ወደ ላይ አወጣውና፡ እንዲህ አለ፡ "እነዚህን የአለምን መንግስታት ሁሉ አየሃቸው? እነ ዩናይትድ ስቴትስ፡ እነ ታላቋ ብሪታንያ፡ ወደፊት በሚመጡት ዓመታት ሊመጡ ያላቸው እነዚህ ሁሉ።" "ሁሉም የኔ እንደሚሆኑ፡ ታውቃለህ፡" አለው። (የሚገዛቸው እሱ ነው።) እንዲህ አለ፡ "የእኔ ናቸውና በእነርሱም እሰራለሁ፡ ወደ ጦር አዘምታቸዋለሁ፡ በእነርሱ የምፈልገውን ሁሉ አደርጋለሁ። የእኔ ናቸው።" "እኔን ብትሰግድልኝ ለአንተ እሰጣቸዋለሁ፡" አለው።

256 "ዞር በል፡ አንተ ሰይጣን፡" አለው። በፍጻሜውም፡ ወራሽ እንደሚሆንላቸው አውቆ፡ "ዞር በል፡ አንተ ሰይጣን፡" አለው።

257 በመጨረሻም አንድ ቀን ወደዚያ ሲያወርዱት፡ እነሆ—ጨርቅ አንሥተው ፊቱ ላይ **እንዲህ** አደረጉበት፡ ያረጀ የጎደፈ ሰካርፍ ይመስለኛል፡ እና... ጭንቅላቱ ዙርያ ጎተቱት። በዚያም ተጎድቷል፡ እየደማ ቁጭ ብሏል። ጠዋት ነው፡ ቀዝቃዛ ነፋስ ይነፍሳል።. ገርፈውታል፡ እና ደም ከተከሻው በኩል ይወርዳል፡ አጠገቡ ላይ የሆነ ነገር **እንዲህ** ጣሉበት፡ በዚያ በተቀመጠበት፡ ደሙ ከጀርባው ጋር ተጣብቋል፡ የእሾህም አክሊል እንዲሁ በፊቱ ላይ ጫኑበት። በተቀመጠበት፡ ይደማል፡ ወታደሮች፡ ፊቱ ላይ ይተፉበታል። እንግዲህ ይህ ቀፋፊ-እይታ አይደለምን? (አምላክ ሆይ!)

258 እናንተም "እንደው፡ እኔ በዚያ ብሆን ኖሮ፡ አንዳች ነገር አደርግ ነበር፡" ትላላችሁ። ታዲያ፡ አሁን ለምን የሆነ ነገር አታደርጉም? ምክንያቱ... አሁን የምታደርጉትን ተመሳሳይ ነገር ባደረጋችሁ ነበርና።

259 በዚያ እየተተፋበት፡ እና እየተሳለቁበት፡ ቁጭ ብሏል። በዚያም ደቀ መዛሙርት ከበስተጀርባው ቆመው፡ እንዲህ ይላሉ፡ "ኦህ፡ ማይ፡ እንዲህ እንዴት ይሆናል? የሞተውን ሰው ከመቃብር ማውጣት የቻለ፡ ያ ሰው፡ እስኪ አሁን ተመልከቱት።" ነገር ግን ቅዱሳት መጻሕፍትን ማወቅ ተሰኗቸዋል። እውነቱ ይህ ነው፡ አያችሁ።

260 እነሆ፡ ደም እና ትፋታቸው በፊቱ ነበረ። ዓይኖቹ ላይ ጨርቅ አሰረው፡ እንዲህ ይሉታል፡ "ታውቃላችሁ፡ እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ 'መንፈሳዊ የመለየት ጸጋ አለው፡ ታውቃላችሁ። ነብይ ነው፡ ህዝቡን መናገር ይችላል። በጉድጓዱ አጠገብ ለሴቲቱ ኃጢአቷን ነግሯታል። ሰምዖንም የአባቱ ስም ዮና እንደሆነ፡ ሌላም ነገር ሁሉ ነግሮታል።' እስኪ ምን ያደርጋል፡ ከቻለ አሁን እንየው።"

261 "ትንሽ ፈተና እንፈትነዋለን፡" ተባባሉ። በሰዎቹ ሲሰራ የነበረው ዲያብሎስ ነበር። በአይኑ ላይ ጨርቅ **እንዲህ** አሰሩበትና፡ ዱላ አንስተው በዱላ መኃል ራሱ ላይ መቱት፡ "ነቢይ ከሆንክ፡ ማን እንደመታህ ንገረን፡" አሉት። አፉን እንኳን አልከፈተም፡ ዝም ብሎ ተቀመጠ።

262 ሰይጣንም "ይህ ሊሆን አይችልም... ማለት—ይህ እግዚአብሔር ሊሆን አይችልም፡" አለ።

263 ዛሬ በዚህ ዘመን የኃይማኖት ተቋማት የሚሉት ነገር እንዲሁ ተመሳሳይ ነገር ነው፡ "እነዚህ የሆሊ-ሮሎሮች መንጋ፡ ይህ እግዚአብሔር ሊሆን አይችልም።" ነገር ግን አላወቁም። አላወቁትም። "ይህ ነገር አይምሮን የማንበብ ችሎታ ነው እንጂ፡ እግዚአብሔር አይደለም። ሟር—ሟርተኞች ናቸው።" በቃ፡ አላወቁትም።

264 እና ወደ ኮረብታው ለመሄድ ተነሱ—ሄዱ፡ ካባውን በላዩ ላይ አደረጉበት። እሱ ሰው በነበረ ጊዜ፡ የነበረችው ብቸኛ ልብስ፡ ማርያም እና ማርታ የሰሩለት ትንሿ ካባ፡ ትመስለኛለች፡ ያለ እንዳች ስፌት፡ ሙሉ ለሙሉ የተሸመነ ነበር። ጀርባው ላይ እንዲህ ጣል አደረጉበት። ያን መስቀል እየሳበ እና እየጎተተ፡ ወደ ኮረብታውም በሚወጣ ጊዜ፡ በልብሱ ላይ ትንንሽ ነጠብጣቦች ነበሩበት። ሲሄድ ሳለም፡ እንደዚያ እንዲሄድ እያስገደዱት፡ ትንሿ እና ደካማ አካሉ፡ ይገርፉታል፡ ሌላ ሁሉ ያደርጉበታል። ያንን መሰቀልም፡ "ገጭ-ጓ፡" እያለ ትከሻዎቹን ይልጡታል፡ ይንገዳገዳል፡ ይቀጥላል።

265 እና ትንንሽ ነጠብጣቦች እየሰፉ እና እየሰፉ ሄዱ፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሁሉ አንድ ትልቅ ወደ መሆን መጡ። ሰይጣንም እነሆ፡ እንደምታውቁት፡ ያንን **ሞት**፡ በ "ንብ" መልክ መጣ፡ እንደምታውቁትም፡ እንዲህ አለ፡ "አህ፡ አህ፡ አህ! ይሄኛው? አረ እግዚአብሔር እንዲህ አያደርግም።" "ይሄ'ማ ሲያካብድ ነው፡ ተራ ሰው ነው፡" አለ። እስከ አሁን ድረስ እንደዚያ ያሰባል። "ይሄ'ማ እያካበደ ነው፡ በደንብ እወጋዋለሁ። እግዚአብሔር ከሆነ አይሞትም። እንዲህ አደርጋለሁ—እንዲህ፡ እወጋዋለሁ ከዚያ አየዋለሁ። እስኪ—እስኪ አንድ ፈተና ልፈትነው።"

266 እና በመሰቀል ላይ ባገኘው ጊዜ፡ ያንን መውጊያውን ወደ ውስጥ አዘለቀ፡ ከወጋው በኋላ፡ መውጊያው ተወሰደበት። ያ ከሰው በላይ ነበር፡ በዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን ወጋ!

267 "ሞት ሆይ፡... " ያለበት ምክንያትም ይህ ነው፡ ጳውሎስ... ንብን፡ እንደ—እንደምታውቁት፡ አንዴ በደንብ ከወጋ በኋላ፡ በድጋሚ አይወጋም። ንብ ያኔ ያልቅለታል። መጮህና ጥዝዝ ማለት ይችላል፡ መ—መ—መውጋት ግን አይችልም፡ መውጊያ የለውምና። ስለዚህ ሞት ከአሁን በኋላ መውጊያ የለውም። ጳውሎስ፡ ራሱን ሊቆርጡ ግንብ በሰሩ ጊዜ፡ ሞት ነድፎ ስለነበር-... በዙሪያው ጠዘዘ፡ እሱም "ሞት ሆይ፡ መውጊያህ የት አለ? " አለ፡

268 ሲኦል እንዲህ አለው፡ "ጳውሎስ ሆይ፡ አገኛሃለሁ። እንከባልልሃለሁ።" (ጭንቅላቱን ቆርጠው እርሱን የጣሉበት የፍሳሽ ማስወገጃ ውስጥ ጎብኝቼዋለሁ።) ሲኦልም "ሰውነትህን እ—እ—እበሳሳዋለሁ፡ አበሰብሼ እጥለዋለሁ፡" አለው።

269 እርሱም እንዲህ አለ፡ "ኦህ—ኦህ፡ ሲኦል ሆይ፡ ድል መንሣትህ ወዴት አለ? " እያችሁ? "ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድል መንሣትን ለሰጠን እግዚአብሔር ምስጋና ይሁን!" ሞት መውጊያውን አጣ። እንዲህ አለ፡ "መልካምን ገድል ተጋድያለሁ፡ ሩጫዬን ጨርሻለሁ፡ እምነቴን ጠብቄአለሁ። እነሆ ከአሁን በኋላ የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶልኛል ጻድቅ ፈራጅ የሆነው እግዚአብሔር በዚያ ቀን ለእኔ ያስረክባል። ለእኔ ብቻ ሳልሆን፡ መገለጡን ለሚወዱ ሁሉ ጭምር።" አሜን! "ከፈለጋችሁ አሁን ቁረጡ።" ኧሃ! ኦህ፡ ይኸው—ይኸው ነው። ወንድሜ ሆይ፡ መንገዱ ይህ ነው። እውነተኛው የ—የክርስትያን መንፈስ ይህ ነው።

270 አሁን—አሁን፡ ዕጣውን ከደረሰባችሁ፡ የአውሬውን ምልክት የምትቀበሉት እንዴት ነው? ይህን መናገር የፈለግኩት ይህን በማለት መዝጋት ስለፈለግኩ ነው። የአውሬውን ምልክት የምትቀበሉት እንዴት ነው?

ማወቅ ትፈልጋላችሁን? ውጤቱስ ምንድ ነው? የአውሬው ምልክት ምንድን ነው?

271 የእግዚአብሔር ማኅተም ምን እንደሆነ እናውቃለን። የእግዚአብሔር ማኅተም ምንድን ነው? እሺ፡ ኤፌሶን 4:30 እንከፍታለን፡ ከዚያ—ከዚያ ታውቁታላችሁ፡ እስኪ እናንተ ራሳችሁ አንብቡት። ወይ—ወይም አንዳችሁ ደግሞ ከራእይ—ራእይ 9፡1 እስከ 4 ድረስ ትከፍታላችሁ። ሌላኛው ደግሞ፡ ሁለተኛ ቆሮንቶስ 1፡22። ብዙ ቦታዎች አሉ። ጥቂቶች ግን ጽፌ ይዣለሁ። እስኪ ኤፌሶን 4፡30 እንክፈት፡ ከዚያም የእግዚአብሔር ማኅተም፡ እና እነዚህ ሌሎች ወይም የትኛውም ይሁን፡ ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ። **ማኅተም** የሚለውን ቃል በማጣቀሻችሁ ውስጥ እስኪ ፈትሹት፡ እና ወደ ፈለጋችሁት ውሰዱት። እሺ፡ ኤፌሶን 4፡30 ላይ፡ ይህን ሰሙ፡-

> እስከ **ቤዛችሁም ቀን ድረስ የታተማ**ችሁበትን፡ **ቅዱሱን የእግዚአብሔርን መንፈስ አታሳዝኑ።**

272 የእግዚአብሔር ማኅተም ምንድን ነው? መንፈስ ቅዱስ ነው። በትክክል። ስለዚህ፡ አሁን፡ "የእግዚአብሔር መንፈስ የሌለው የእኔ ወገን አይደለም።" መንፈስ ቅዱስ ካላችሁ፡ የእርሱ ስለሆናችሁ የእግዚአብሔር አካል ናችሁ። በእናንተ ውስጥ ሆኖ፡ ስራውን ስለሚሰራ—እርሱ በማኅተም አተማችሁ፡ ስለዚህ እርሱ የሚሰራቸው ስራዎች ታደርጋላችሁ። እሺ፡ ተማሪዎች፡ ይህ ነገር የገባው አንድ አለን? የእግዚአብሔር ወገን ለመሆን መንፈስ ቅዱስን ይጠይቃል፤ መንፈስ ቅዱስ። የመንፈስ ቅዱስ ከሆናችሁም፡ ኢየሱስ የሠራውን ሥራ ትሠራላችሁ። አያችሁ? ፍቅራችሁ...

273 ፊታችሁ ላይ ሲተፋባችሁ እና ሲደበድቧችሁ፡ መራራ ስር አይኖራችሁም። እርሱ ቁልቁል እያያቸው፡ እንዲህ አለ፡- "አባት ሆይ፡ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው።" አያችሁ፡ አያውቁም።

274 ይህን መገመት ትችላላችሁን? የገዛ ልጆቹ ደሙን ለማፍሰስ ይጮኻሉ! የሰማይና የምድር ፈጣሪ እራሱን በፈጠረው መስቀል ላይ ተንጠልጥሎ፡ ከመሬት ከፍ ከፍ አለ። የገዛ ልጆቹም! (እሰቲ አሰቡት የገዛ ልጆቻችሁን፡ አባቶቻችሁን፡ ልጆቻችሁ።) እንዲወገድ ይጮኻሉ፡ "አሰወግደው! ሌባውን በርባንን፡ ፍታልን።"

275 አቤቱ፡ በርባን እኔ ነበርኩ፡ መሞት የተገባኝ እኔ ነበርኩ እርሱ ስለ እኔ ሞተ። ያን ማለዳ በርባን እርሱ የነበረበት በር ለመክፈት ወደ እርሱ የሚመጣ የታጣቂው ኮቴ በሰማ ጊዜ፡ እንዴት ሆኖ ይሆን። ምስኪን በርባን፡- "ወይኔ፡ ጉዴ! ከአፍታ በኋላ ያልቅልኛል። ነፍሰ ገዳይ ነኝና፡ እኔ—ሌባ ነኝና። ዛሬ ይገድሉኛል፡ እንደሚገድሉኝ አውቄአለሁ። ዛሬ የፋሲካ በዓል ነው፡ ስለዚህ በ—በትክክል... ዛሬ እንደምሞት አውቄአለሁ።" እንደ ማንኛውም ኃጢአተኛ ሁሉ፡ ሌሊቱን በሙሉ፡ በጭንቀት ሲኀራደድ አደረ። እና በመጀመርያ፡ እነሆ ጥበቃው መጣ። እርሱም እንዲህ አለ፡ "ወይኔ፡ ወይኔ፡ እነሆ መጣ። አሁን እውሰዳለሁ፡ አሁን እወሰዳለሁ።" እና የደጁን ቁልፍ ቀጭ አለ።

ጥበቃው በተጠንቀቅ ፊቱ ቆሟል፡ "በርባር ሆይ፡ ና ውጣ!"

"ኧሃ-ሃህ፡ አዎን። አዎን፡ መሄዴ ነው፡ መሄዴ ነው።"

“አይደለም፡ ውጣና የፈለግከውን አድርግ።”

“ምን? ”

“ወጥተህ የፈለግከውን አድርግ። ነጻ ነህ፡ ውጣ።”

276 “እኔ ነጻ ነኝ? ለምን፡ የሞት ፍርድ ፈረዳችሁብኝ።” እውነት ነው፡ እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን በሙሉ የሞት ፍርድ ይፈርዳል። “የሞት ፍርድ ፈርዳችሁኛል፡ እንዴት ነጻ እወጣለሁ? ”

277 “በርባን ሆይ፡ ወደዚህ ና። ተመልከት፡ ማዶ ላይ ያለውን ኮረብታ ሲወጣ እየው፡ መስቀሉ መሬት ላይ ሲንቋቋ ሰማው። ምስማሮቹ ወደ እጆቹ ሲከቱበት ሰማው። ደም የተቀላቀለበት ጨዋማ እንባ ፊቱ ላይ እየወረደ፡ እዚያ ማዶ የሚያለቅሰውን ትመልከተው። በርባን ሆይ፡ ሰለ አንተ እርሱ ሞተ፡ ሰፍራህን ተካ።”

“እኔ ነጻ እንድወጣ እርሱ ሞተ ማለትህ ነው? ”

“አዎን።”

278 “እንዴ፡ ይሁና፡ እንዲህስ ከሆነ እንደገና መግደል ልጀምር።” አቤት፡ እንዴት ያለ ምስጋና ቢስ ነው! ሞት ይገባችሁ ነበር።

> አስደናቂውን መስቀል—ሰቃኘው፡
> የክብር ንጉስ የሞተበት፡
> ዝናዬ ሁሉ ጉድፍ ብቻ ነው።

ኦህ፡ ማይ! ገጣሚው እንዲህ ማለቱ አይደንቅም።

> እየኖረ፡ ወዶኛል፡ እየሞተም፡ አድኖኛል፤
> ተቀብሮ፡ ሐጢአቴን አራቀ፤
> ተነሥቶም፡ በነጻ ለዘላለም ጸደቀ፡
> አንድ ቀን ይመጣል፡ አቤት—ያቺ ድንቅ ቀን!

279 ያደረገልኝን አቼ አረ እንዴት ልተወው እችላለሁ? እንዴት እችላለሁ? በምድር ያገኘሁትን ወዳጅ ሁሉ ባጣ ይሻለኛል። እንዴት፡ በ... ድርጅቶች ለመባረር ፈቃደኛ ሰሆን እና ሲያባርሩኝ፡ ሌላው ነገር ሁሉ ሲያደርጉብኝ። እነሆ አማትሬ ባየሁ ጊዜ፡ ሞት በተፈረደብኝ ጊዜ፡ እነሆ እሱ ፍርዴን ወሰደ! እውነት ነው፡ ጌታ ሆይ፡ ሌላውን ሁሉ፡ እንደ ጉድፍ እቆጥራለሁ። አቤቱ፡ ጌታ ሆይ፡ መስቀሉን ልሸከም።

> በሚስነጣጠቁ ዓለቶች እና በጨለመው ሰማይ መካከል፡
> አዳኜ አንገቱን ደፍቶ ሞተ፡
> የተከፈለው መጋረጃ መንገዱን ገለጠ
> ማለቂያ ለሌለው ቀን ወደ ሰማይ ደስታ።

280 አቤቱ፡ ኢየሱሰ ሆይ፡ ልጠጋህ ወደ አንተ—እንድጠጋ ፍቀድልኝ። አምስቱ ቁስሎችህ እየደማ እያየሁ፡ ከተወደደው ጎንህ አትለየኝ። የሰማይ አለቃ ሆይ፡ እንዴት እንደሞተ፡ ለእኔ ሞተልኝ! ሰለ እኔ ሞተ...

281 በኃጢአት ሰንሰለት፡ በገሃነም እሰር ቤት... ሰለተወገዘው፡ ጥፋተኛ ሆኜ፡ ተፈርዶብኝ፡ ዘለአለም ለመጥፋት መንገድ ላይ ሳለሁ፡ እነሆ አንድ ሰው ፍርዴን ተቀበለ። ከዚያ እነሱም... ገና ልጅ ሳለሁ እዚህ ሲያርሱ፡... ፤ የአሥራ ሰምንት፡

ሃያ ዓመት ገደማ ነበርኩ፡ አንድ ቀን መንፈስ ቅዱስ... እንዲህ አልኩት፡ "እሺ፡ እኔ ማን ነኝ? ከየት ነው የመጣሁት? ወዴት እየሄድኩ ነው?"

282 እርሱም "ይኸው፡ አንተ **ወደዚያ** ስትሄድ ሳለህ፡ እነሆ እርሱ፡ ፍርድህን ተቀበለ፡" አለኝ።

283 እኔም አልኩኝ፡ "የእግዚአብሔር በግ ሆይ! የእግዚአብሔር በግ ሆይ፡ እነሆ መጥቻለሁ! እነሆ መጥቻለሁ! በእጄ የያዝኩት ነገር ሳይኖረኝም፡ ለአንተ የምሰጥህ ሳይኖረኝ፡ ጌታ ሆይ፡ እንዲሁ ወደ መስቀልህ ተጣብቄአለሁ፤ ያለኝ ይሄ ነውና።" እርሱም ተቀበለኝ። እንደ ጠፋ ልጅ አባቱ እንደደረበለት አለበሰኝ፡ አዲስ ካባ በላዬ አደረገልኝ፡ የእኔ ያይደለ ካባ፡ የጽድቁን ካባ በእኔ ላይ ደረበልኝ፡ በጣቴም ላይ የሰርግ ቀለበት አደረገልኝ፡ ይህም በዚያ ቀን ከሙሽሪት ጋር እሆን ዘንድ ነው። የሰባው ጥጃ ታረደ፡ እናም አንድ ጊዜ ሞቼ ነበር አሁን በህይወት ስለተገኘሁ ደስ ብሎናል፡ ጠፍቼ ነበር አሁን ተገኘሁ።

ድንቅ ጸጋ ሆይ! አስደሳች ድምጽ፡
እኔንም ያዳነኝ! (ከበርባን የባሰ ሰው።)
ጠፍቼ ነበር፡ አሁን ተገኘሁ፡
አላይም ነበር፡ አሁን አየሁ።

በልቤ እንድፈራ ጸጋው አስተማረኝ፡
ጸጋው አሁንም ፍርሃቴን አሰወገደ፤
ጸጋው ምን ያህል ድንቅ ነው
ባመንኩት ቅጽበት የሆነልኝ!

አሰር ሺ አመታት በዚያ ሰንኖር፡
እንደ ጸሐይ ደምቀን ሰናበራ፡ (ከእንግዲህ ከዋክብት ሳንሆን፡ ጸሐይ።)
ሰለ ውዳሴ የምንዘምርበት ጊዜ አያጥረንም
መጀመሪያ ከጀመርንበት ጊዜ ይልቅ። (በዘላለም ውስጥ ነንና።)

284 አቤት፡ ኢየሱስን እንዴት እንደምወደው፡ እርሱ አስቀድሞ ሰለወደደኝ። አቤት፡ እንዴት ድንቅ ነው!

አሁን ከእኔ ጋር ዘጸአትን እንክፈት፡ ምዕራፍ 21 ላይ፡ እሺ።

285 የ "መንፈሱ" ምክር፡ እንዴት እንደምንቀበለው አሁን እንነጋገርበታለን... አሳይቼአችኋለሁ፡ ውጤቱንም ነግሬአችኋለሁ፡ "እነሆ እሱ **በዚያ** ነው።"

286 አሁን፡ "የአውሬውን" ምልክት የምትቀበሉት እንዴት ነው? **በዚያ** ውስጥ ጥፋታችሁ ምን እንደሚመስልም አሳያችኋለሁ። አሁን፡ የአውሬው ምልክት፡ በዘጸአት ምዕራፍ 21 ላይ። በዚህ ውስጥ ማየት እንድትችሉ ከብሉይ ኪዳን እናወጣለን። በአዲስ ኪዳን ውስጥም ሁላችንም የምናውቃቸው ብዙ ቅዱሳት መጻሕፍት ይዣለሁ። አሁን እናንብብ፦

**በፊታቸው የምታደርገው ሥርዓት** ይህ **ነው።**

**ዕብራዊ ባሪያ የገዛህ እንደሆነ፡** (አሁን፡ አሁን አስታውሱ፡ ዕብራዊ ነው፡ አማኝ ነው፡ አያችሁ።)... **ዕብራዊ ባሪያ፡ ሰድሰት ዓመት ያገልግልህ፤ በሰባተኛውም በከንቱ አርነት ይውጣ።**

**ብቻውን መጥቶ እንደሆነ፡ ብቻውን ይውጣ፤ ከሚስቱ ጋር መጥቶ** እንደ**ሆነ፡ ሚስቱ ከእርሱ ጋር ትውጣ።**

**ጌታው... ሚስት** አጋብቶት **እንደ ሆነ፡... ወንዶች ወይም ሴቶች ልጆች ብትወልድለት፤ ሚስቱና ልጆችዋ ለጌታው ይሁኑ፡ እርሱም ብቻውን... ይውጣ።**

287 ጊ—ጊ—ጊ—ጊዜዬ እንዳለቀ ተረድቻለሁና... አሁን አልቀጥልበትም። ይቅርታ አርግልኝ፡ ወንድም ኔቪል፡ ይህ ነገር ዘልቆ እንዲገባ ማድረግ—አለብኝ፡ ወንድሜ።

288 ይኸውላችሁ። ጉዳዩ እናታችሁ ማን ናት፡ አባታችሁስ ማን ነው አይደለም፡ አንተ ማነህ ነው! ሚስትህ አይደለም፡ አያችሁ፡ በሚስቱ አይቆጠርለትም፡ በልጆቹ አይቆጠርለትም፡ እሱ ራሱ ነው! ምንም ያህል... እናትህ ቅድስት ብትሆንም እንኳ፡ አባትህ ቅዱስ ቢሆንም እንኳ፤ የዔሳው አባትና እናትም እንደዚሁ ነበሩ፡ እርሱ ግን የጥረት ሰው ነበር። አያችሁ? ጉዳዩ፡ ግን... በእናንተ ውስጥ የግል **ጉዳያችሁ** ነው።

289 "አባቴ ሰባኪ ነው፡" ትላለህ። ያ ከዚህ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። "እናቴ ቅድስት ሴት ነች። ኦህ፡ እሷ'ማ ገነት ገብታለች።" ትክክል ሊሆን ይችላል፡ ግን አንተስ? አንተ ነህ!

**ባሪያውም...**

290 አሁን፡ ነገሩ እንዲህ ነው... ይህ የአውሬው ምልክት ተመልከቱት አሁን። እንግዲህ፡ አሁን ሃያ ጉዳይ ስለሆነ፡ ቅደም ተከተሉን ጠብቄ ለመሄድ—ጊዜ የለኝም። አንድ ነገር ልነግራችሁ ግን እፈልጋለሁ።

291 አሁን፡ በየሰባት ዓመቱ መጠርያ ያለው ጊዜ ይመጣ ነበር። ያም ስድስት አመታት ነበረ። በሰባተኛ ዓመት (የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች፡ አገልጋዮች፡ እዚህ የተቀመጣችሁ ሁሉ፡ ይህ እውነት እንደሆነ ታውቃላችሁ።) እንዲህ ይባላል... ሰባተኛው ዓመት፡ ሁሉም የሚያርፍበት ኢዮቤልዩ ዓመት ይባላል። በሰባተኛው ዓመት የሚዘራ ሰብል የለም፡ መሬቱ፡ እና ሌላው ሁሉ ያርፋል። ቃርሚያ ብቻ ይቃርማሉ፡ አያችሁ። ነገር ሁሉ በሰባተኛው ዓመት ያርፋል። በሰባተኛው ዓመትም—እነሆ አንድ ካህን መለከቱን ሊነፋ ይነሣል። ስለዚህ ባሪያ የነበረ ግለሰብ፡ ምን ያህል ዕዳ ይኑርበት ግድ አይሰጠኝም፡ ነጻ ይሆናል።

292 ያም፡ የወንጌል መለከት ጥሪ ነው። እናንተም በሰንሰለት ታሰራችሁ፡ በመጠጥ፡ በማጨስ፡ በቁማር እና በሃጢያት፡ በቆሻሻ ነገሮች፡ በእነዚህ ዓመታት፡ ዲያብሎስን ስታገለግሉ የኖራችሁ ልትሆኑ ትችላላችሁ፡ በደላችሁ ምንም ቢሆን፡ የወንጌል መለከት በሰማችሁ ጊዜ፡ ነጻ መውጣት እንደምትችሉ ምልክቱ ነው። መሄድ ትችላላችሁ! "እምነት የሚመጣው በ፡ [ጉባኤው "በመስማት፡" አለ።—እርታዒ።] መስማትም፡ የእግዚአብሔርን ቃል።" ከእንግዲህ የወንጌልን ሙላት ሰምተሃልና፡ ከአሁን በኋላ ታስረህ መቆየት አያስፈልግህም።

293 እንግዲህ፡ እንዲሁ ዝም ብላችሁ "ኦህ፡ ሰምቼዋለሁ፡ ግን አላዳመትኩትም፡" ትላላችሁ። አያችሁ? እሺ፡ እንግዲህ ለእናንተ አይደለም። ኧሃ-ሃህ። ለሚሰሙት ነውና። እንግዲህ፡ መስማት ከቻላችሁ ነው።

294 አሁን እዚህ ጋር የተናገረውን ተመልከቱ። አሁን ይህንን ለማረጋገጥ፡ አሁን በቅርበት ተከታተሉና ለሚቀጥሉት ሁለት ወይም ሶስት ደቂቃዎች ሀሳቦቻችሁን ጠብቁ።

> **ባሪያውም** (ማለት ነጻ—መውጣት የተገባው ሰው።) **በግልጽ፡ ጌታዬን እወድዳለሁ ቢል**፡...

295 "ኦህ፡ ወደ ጭፈራ መሄድ እወዳለሁ። ዳንሴን ለማንም አልተውም። **ይህን፡ ያንን፡** ወይም **ሌላ፡** ባለቤቴ፡ ልጆቼ፡ የምወዳቸው የዚህች ምድር ነገሮች፡ ለማንም አሳልፌ አልሰጥም ቢል። ቆይ፡ ይኸውልህ፡ ወንድም ብራንሃም፡ ልንገርክ እስኪ፡ ይህ እንዲህ ማቆም አለብኝ ማለትህ ነው... ? " ምንም ነገር ማቆም የለብህም። ብቻ አንተ ና፡ ሌላው በራሱ ጊዜ ይቆማል። ግን—አንተ ግን እንዲህ በል፡ "ከእንግዲህ፡ ይህን አላደርግም። ይህን ማድረግ የለብኝም፡ የቤተክርስቲያን ሰው ነኝ እንደ አንተ ወይም እንደማንኛውም ሰው ጥሩ ነኝ።" እሺ፡ ወንድሜ። ችግር የለውም፡ እውነትን እንደሆነ ሰምተሃል። "እሺ፡ አሁን፡ ይህን ሰሙ፡ 'አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ' አይደለም'ዴ... ? " ደህና፡ ያንን ፈለግ መከተል ከፈለግክ፡ ሂድ ቀጥል።

296 መለከት ሲነፋ ሰምታችኋል፡ የሚሰጠውን የድምጽ አይነት ለይታችኋል። መጽሐፍ ሲናገርም... (አምላክ ሆይ!) ይህን አሰተውሉ! ይህ ራሱ ለቀጣዩ አንድ ሰዓት የሚያቆየኝ ርዕስ አይወጣበትምን? "መለከት የማይታወቅ ድምጽ ቢሰጥ።" የኃይማኖት ተቋማችሁ "አብ፡ ወልድ፡ መንፈስ ቅዱስ፡" ሲል ድምጹ የመለከት ድምጽ አይመስልም። "መለከት የማይታወቅ ድምፅ ቢሰጥ፡ ለጦርነት ማን ይዘጋጃል? "

> **... ባሪያውም በግልጽ፡ ጌታዬን እወዳለሁ ቢል፡...**

297 "እነዚህ ነገሮችን—የሚያስደርገኝን ዲያብሎስን እ—እወደዋለሁ፡ ችግር የለውም። እኔ እንደማስበው... እንደማስበውም በዚያ—በዚህ ነገር ላይ ባለ-ጠባብ አእምሮ ትመስለኛለህ። እጅግ ጠባብ ትመስለኛለህ።" እሺ። "ነገሮቹን እወዳቸዋለሁ። ልክ **እነዚህ** የመሳሰሉ ታላላቅ ነገሮች ሊ—ሊኖሩን፡ እና **እነዚህን** ማድረግ ይገባናል ብዬ እሰባለሁ፡ ዓለም... በቸርቻችን ውስጥ ዳንሶች አሉን፡ ቡንኮ ጨዋታዎች፡ እና የመሳሰሉ ነገሮች አሉን፡ ሁላችንም ጥሩ ጊዜ እናሳልፋለን፡ እናንተ ጋር እንዳለ ህዝብ እዚህ ጋር ያለውም እንዲሁ ነው።" እሺ፡ ችግር የለውም። መልካም።

> ... እናንተም በምትናገሩት በዚህ መንፈስ አርነት **አልወጣም** ቢል፦

> **ጌታውም** (ዲያብሎስ) ወደ **ፈራጆች ይውሰደው፡ ወደ በሩ**ም **አቅርቦ**፡...

298 እህም! ወደ ምኑ? ደጁ ማን ነው? [ጉባኤውም፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ፡" አለ—አርታዒ።] "በፊትህ በር ሰጥቼሃለሁና።" የአውሬው ምልክት የመጣው መቼ ነበር? የተከፈተ በር በተሰጠበት በዚህ ዘመን። ይህ መዳ-... የአውሬው የመጨረሻ መዳረሻው።

> ... **ወደ በሩም፡** ወደ **መቃኑ... አቅርቦ፤** (ያም—ቀራንዮ፡ መልካም)... **ጌታውም ጆሮውን በወስፌ ይብሳው... ጆሮውን በወስፌ ይብሳው፤ ለዘላለምም ባሪያው ይሁን።**

299 “ወንድም ብራንሃም ሆይ፡ ምን ማለትህ ነው?” የወንጌልን እውነት ሰምታችሁ በእርሱ ለመኖር ፍቃደኛ ካልሆናችሁ፡ እግዚአብሔር ደግማችሁ የማትሰሙ አድርጎ ጆራችሁን ምልክት ያደርግበታል። በህይወት እና በሞት መካከል ያለውን ድንበር አለፋችሁት። ከዚያ በኋላ ቀሪ ዘመናችሁ፡… እና፡ ቀሪ ህይወታችሁ ከድርጅታችሁ፡ ከኃይማኖት ተቋማችሁ፡ ተከትላችሁ ትቀጥላላችሁ። (ልጆች ሆይ፡ በብርሃን ተመላለሱ። በእውነት።) ያንን ጌታ ለዘላለም ታገለግላላችሁ።

300 እንዲህ ይሁን… እንዲህ መሆን አይገባችሁምና… መለከት ሲነፋ ሰምቶ፡ ነጻ መውጣት ይችላል፡ ይህም የእግዚአብሔር ጸጋ ነውና። የኢዮቤልዩ ዓመት ነው፡ ሙላት ነው። የኃጢያት ቀን አልፎአል፡ ወንድሜ። የኃጢአት ባርያዎች የሆናችሁ ለሁላችሁ እላለሁ (በቴፕ፡ ወይም በዚህ ጉባኤ ያላችሁ ሁሉ)፡ እናንተ… የኃጢአትን ባሪያ የሆናችሁ ሁሉ፡ የኃጢአት ቀን አብቅቷል! ኢየሱስ ሞቷልና፡ ከእንግዲህ ኃጢአትን ማገልገል አይጠበቅባችሁም። ለተቋማት እና ለኃይማኖት መገለጫዎች መሰገድ የለባችሁም። “ልጁ አርነት ያወጣው በእውነት ነጻ ነው።” ነጻ መውጣት እና በልጁ አርነት መውጣት ከፈለጋችሁ፡ ከነገር ሁሉ ተላቃችሁ እርሱን አገልግሉ፡ ተው እንጂ!

301 ካልፈለጋችሁት ግን፡ ድርጅታችሁ፡ ወይም ጌታችሁ፡ ወይም ባሪያ የሆናችሁለት አካል፡ በጆሮአችሁ ላይ ምልክት ያደርጋል ከዚያ በኋላ መስማት አትችሉም። እግዚአብሔር ለልባችሁ ተናግሮ “ና፡ ይህ ጊዜው አሁን ነው፡” ቢላችሁና እምቢ ብትሉት፡ ምልክቱን ትቀበላላችሁ። ከእውነት ለደነደነ። የዲያብሎስ ማኅተም፡ የአውሬው ምልክት ተዘጋጅቶለታል። አያችሁ? የአውሬው ምልክት ምን ያደርጋል? ወስዶ ወደ ሮማኒዝም፡ ወደ ኃይማኖት ተቋምነት ይመልሳችኋል፡ በጭራሽ አርነት አትወጡም፤ ያንን ለዘላለም ታገለግላላችሁ እንጂ። የአውሬው ምልክት ይህ ነው።

302 ወዳጆች ሆይ፡ ይህ ይከብዳል፡ ይቆራርጣል፡ እውነቱ ግን ይህ ነው… በዚህ ጉዳይ ኃላፊነት አልወስድም… መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ነውና።

303 እንግዲህ፡ ያ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የምስራች ወንጌልን መስማትን የሚያመለክት ምሳሌ ነበር ይህም “ነጻ ነህ!” ከእንግዲህ መታሰር አይገባህም፡ በክርስቶስ ኢየሱስ ሙሉ ለሙሉ ነጻ ነህ የሚል ነው። ከእንግዲህ ኃጢአት እና ነገሮች የሉህም። የሉብህም…

304 መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር፡ ዓለምን የምትወድ ከሆነ፡ “ዓለምን ወይም የዓለምን ነገር የምትወድ ከሆነ፡ የእግዚአብሔር ፍቅር በአንተ ውስጥ የለም።” እውነት ነው? ዓለምን ወይም የዓለምን ነገር ብትወድ፡ የእግዚአብሔር ፍቅር በአንተ ውስጥ የለም። ታዲያ ዛሬ በሃይማኖት ስም በዓለም ላይ ስለሚከሰቱት እነዚህ ሁሉ ትልልቅ ነገሮችስ? የአለም ነገሮችስ! ሰዎች በአሳማ ጉሮኖ ውስጥ እንዳለ አሳማ ይዋልሉበታል፡ አያችሁ፡ “ኡህ፡ **ይህ** ጥሩ ነው። **ያ** ምንም ችግር የለውም!” አያችሁ፡ ምልክት ተደርጎባቸው የታተሙ ናቸው። አያችሁ?

305 አሁንስ የአይሁድ ቅሬታዎች፡ መቶ አርባ-አራት ሺዎቹ ምን እንደ ሆኑ ገባችሁ? ቁጭ ብለው፡ እየጠበቁ ያሉት የት ነው? ልክ በሰዓቱ። ሰነፏ ድንግል ይህን ነገር እንደማታገኝ ይታያችኋልን… ዘይቱን አታገኘውም፡ እና ተነስታ የምትለይበት ጊዜ እንደሚመጣ፡ በፍርድ ጊዜ እውነት ከውሸት እንደሚለይ

እያችሁን? የሰነፏ ድንግል ነገር፡ ይህን ነገር ተረድታችሁታልን—ልክ እንደ አሁኑ፡ ይህን እንደፈለገችው፡ ፍለጋም እንደወጣች፡ ሙሽራው የመጣው በዚያው ደቂቃ እንደነበር አወቃችሁን?

306 ታዲያ ምን ያህል ተቃርበናል? አሁኑኑ! አሁን የቀረን አጭር ጊዜ ነው፡ ምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ አላውቅም። መቼ እንደሆነ መናገር አልችልም፡ እኔም—አላውቅም። አንድ ዓመት ሊሆን ይችላል፡ አሥር ዓመት ሊሆን ይችላል፡ አርባ ዓመት፡ ምናልባት አርባ ደቂቃ ሊሆን ይችላል። እ—እንጃ አላውቅም፡ መናገር አልችልም። ቅርብ እንደሆነ ግን አውቃለሁ፡ በእርግጥ ቅርብ ነው። የጌታ መንፈስም...

307 ስለዚህ፡ ከሁሉ በፊት ማወቅ ያለባችሁ፡ ቤተ ክርስቲያኑ መቀዝቀዝ የምትጀምርበት፡ ጊዜ ይመጣል። እስኪ፡ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ የቤተክርስቲያኑ መቀዝቀዝ—ያስተዋላችሁ ስንቶች አላችሁ? በትክክል። ወደ ምን እየገባች ነው? ወደ ሎዶቅያ። ይህም፡ ዛሬ ማታ እንሰተን የሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያንን መልእክ እናየዋለን፡ መልእክቱ ምን እንደሚመስል እናንተም ታዩት ዘንድ፡ በፊታችሁ እናወጣዋለን፡ እና በሎዶቅያ ቤተክርስቲያን ዘመን መጨረሻ ላይ ስትደረብ ገብታ ወደ ዘላለም እንዴት እንደምትሰፋ ታያላችሁ።

308 ኦህ፡ እወደዋለሁ። እናንተስ? አዎን፡ ወዳጄ። ኦህ፡ ይህ... የእግዚአብሔር ማኅተም ምንድን ነው—ምንድን ነው? መንፈስ ቅዱስ ነው። የአውሬው ምልክት ምንድን ነው? መቃወም ነው። ሁለቱ እነዚህ ናቸው። አንደኛው ማየት ነው፡ ሌላኛው...

309 እሺ፡ እነዚህ ሁሉ... በምድር ካሉ ይህን ያልተቀበሉ ስንቶች ነበሩ? "ያልታተመው ሁሉ የአውሬውን ምልክት ተቀብለዋል።" የእግዚአብሔር መንፈስ የሌላቸው፡ በሙሉ፡ የአውሬው ምልክት አላቸው። የእግዚአብሔር ማኅተም መንፈስ ቅዱስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲሁ ይመሰክራል። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ያለው ሁሉ ስለ እሱ ይናገራል፡ የእግዚአብሔር ምልክት ነው ይላል፡ "የእግዚአብሔር ማኅተም።" ያልተቀበሉትም ሁሉ፡ የተቃወሙት እነሱ ናቸው። እንዴት የተቃወሙት? አንሰማም በማለት። ልክ ነው?

310 አሁን አስታውሱ፡ እምነት በምን ታገኛላችሁ? "በመስማት።" ምልክቱስ በምናቸው ላይ ተደረገባቸው? እጅ ላይ ነውን? አይደለም። ጭንቅላታቸው ላይ ነውን? አይደለም። በጆሮ ላይ ነው፡ አያችሁ። **በጆሮ** ላይ፡ "በመስማት።" ምን ያደርጋቸዋል? እንዳይሰሙ ያስፈራራቸዋል። "ከእንግዲህ አይሆነኝም፡" ትላላችሁ፡ "ከእንግዲህ ለእኔ አይሆነኝም። ከዚህ ጋር ምንም ማድረግ አልፈልግም። ከዚያ ጋር ምንም ማድረግ አልፈልግም።" በቃ እንዲህ ናቸው...

311 ወንድም ኔቪል፡ እ—እ—እስኪ—እስኪ ጥቂት ገፋ ላድርገው...

312 "በአንድ ወቅት ብርሃን ለበራላቸው" የሚለውን ነገር ተዘጋጅቼበት ነበር፡ አያችሁ፡ "ወደ መንግስቱ ለመምጣት—እና ለመግባት፡" አያችሁ። ልክ እንደ አስመሳይ አማኞች ናቸው፡-

ተመልከቱ፡ **አንድ ጊዜ ብርሃን የበራላቸውን፡... የመንፈስ ቅዱስ ተካፋይ** ሆነው **የቀመሱትን፡**

... ሊመጣ ያለውን **የዓለም—የዓለም ኃይል የቀመሱትን፡**

**በኋላም የካዱትን፡ እንደገና ለንስሐ** እነርሱን **ማደስ የማይቻል ነው፤** ለራሳቸው **የእግዚአብሔርን ልጅ ይሰቅሉታልና... ያዋርዱትማልና።**

**እና...** የተ**ቀደሰበትን፡ የቃል ኪዳኑን ደም፡ ርኩስ ነገር** ይቆጥራሉና፡...

313 እያችሁ፡ የተመረጠ ግን ይህን ሊያደርግ፡ በጭራሽ፡ በፍጹም የማይቻል ነገር ነው። ይህን አያደርግም፡ እያችሁ። ምክንያቱ ምን ይዳረጋል? እያችሁ? "የቃል ኪዳኑን ደም እንዲህ መቍጠር ግን... " አሁን፡ ተመልከቱ፡ የተመረጠ ከሆነ እና በዚያ ወገን ከሆነ፡ ያንን አያደርግም። ይህን ማድረግ ለእሱ የማይቻል ነውና።

314 አሁን፡ አይተነዋልና፡ እስኪ ወደ ታች ሰፋ እናድርገው፡-

... ብዙ ጊዜ፡ በእርሰዋ ላይ የሚወርደውን **ዝናብ... የምትጠጣ** መሬት...

... **እሾህ**ና ኵርንችትን ግን ብታወጣ... **የተጣለች ናት** ለመረገምም **ትቀርባለች፡ መጨረሻዋም መቃጠል ነው።** (ስንዴው ወደ ቤት ወደ ጎተራው ይወሰዳል።)

315 ይህ ሕይወት-ሰጪ ዝናብ ግን በእንክርዳዱም ሆነ በስንዴው ላይ ይወርዳል። ሁለቱም ዝናብ ሲወርድ በማየታቸው... ተመሳሳይ ስሜት ይሰማቸዋል። ከፍሬያቸው ግን ታውቋቸዋላችሁ፡ ፍሬያቸውን ከአረም ይሁን ወይም ከእህል ፍሬ (ማለት፡ ከሰንዴ)።

316 እንግዲህ፡ ማድረግ ያለብን ይህ ነው። ስለዚህ እነዚህ አሰመሳዮች የት እንዳሉ፡ እነዚህም የት... ይህች **ድንግል** ወደ እናንተ ለማቅረብ እየጣርኩ ነው፡ እያችሁ፡ ይህም እናንተ—ደግሞ እንድትረዱት ነው። እንግዲህ አሰመሳይ አማኞች ሰንል፡ የእስራኤል ልጆች ወደ ቃዴስ-በርኔ በመጡ ጊዜ፡ የሆነውን ተመልከቱ። በዘፍጥረት ላይ ወደ ፊት ወደ ኋላ፡ እንዲሁም በዘጸአት ላይ፡ እና በሌሎችም ሁሉ ወደ ፊት ወደ ኋላ አመላልሼዋለሁ፡ ይህም እናንተ ደግሞ እንዳትስቱት፡ እያችሁ፡ በጥላ መልኩ እናንተን ለማሳየት ነው።

317 አሁን፡ እነዚህ ሰዎች ሲገቡ—በዚህ... በዘጸአት፡ ወደ ቃዴስ-በርኔ በመጡ ጊዜ፡ ቃዴስ-በርኔ የዓለም ፍርድ ወንበር ነበረች፡ በዚያን ጊዜ፡ እስራኤል የፍርድ ወንበር የተቀበለችበት ቦታ ነበር። ያኔ የነበራቸው... ትእዛዙን ከተቀበሉበት ተራራ ፍርድ ፊት እስከቀረቡበት ጊዜ ድረስ የአስራ አንድ ቀን ጉዞ ብቻ ነበር፡ "በባሕር ዳርቻዎቹ ዘንድ የአስራ አንድ ቀናት ጉዞ ነበረ፡" ይላል መጽሐፍ ቅዱስ። የአሥራ አንድ ቀን መንገድ ተጉዘው፡ ወደ ቃዴስ መጡና በዚያ ተፈረደባቸው። እግዚአብሔር ከወሰዳቸው፡ ከአራት ቀናት በኋላ፡ እየተንገጫገጩ በመዞር እንደገና በምድረበዳ ለመቅበዝበዝ ተመለሱ፤ ትእዛዛትን ሁሉ—ሌላውም ይዘዋል፡ እና ተመለሱ፡ እና እንዴት፡ ምን ተፈጠረ። ከዚያም ወደዚህ መጡ... ከዚያም ከአሥራ አንድ ቀን በኋላ፡ በቃዴስ-በርኔ ወደ ፍርድ ቀረቡ።

318 ምን ሆነ? ከየነገዱ አንዱን ወሰደ፡ "ሄዳችሁ ምድሪቱን ሰልሉ፡ እና ምን አይነት ምድር እንደሆነች ተመልከቱ።" እና፡ ሁሉም ሄደው ተመለከቷት።

319 ከመካከላቸው ሁለቱ ገብተው ብዙ የወይን ዘለላ አገኙ። ኦህ፡ ትልቅ ክምር ነው፡ ይዞ ለመውጣት ሁለት ሰዎችን አሰፈለገ።

320 አሁን፡ ምን አይነት ምድር እንደሆነች አይተው ከተመለሱ በኋላስ ምን አደረጉ? አ—አ—አሞራውያንን እና ሌሎች ልዩ—ልዩዎቹን በዚያ—በተመለከቱ ጊዜ፡ እንዲህ አሉ፡ “ኧረ፡ እነሱ ግዙ ናቸው!” (በእርግጥ፡ በዚያ ምድር—ሰፍረው የነበሩት፡ የቃየን ልጆች ነበሩ።) እንዲህ አሉ፡ “እነርሱ ግ—ግ—ግዙፎች ናቸው!” እና እንዲህ አሉ፡ “እኛ ያንን መ—መ—መውረሰ—አይቻለንም። ም—ም—ም—ምድሮቻቸው በደንብ የታጠሩና፡ ታላላቅ ቅጥሮች ናቸው። እና፡ እነሆ፡ እኛም በፊታቸው፡ እንደ አንበጦች እንመሰላለን።”

321 ምን አደረጉ? እነሆ፡ ምድሪቱን—ፈጽመው አይተዋት ነበር። ፍሬዋንም ቀመሱ። አያችሁ፡ እነሆ ካሌብና ኢያሱ አልፈው ሄዱና—ማረጋገጫውን ይዘው አመጡ፡ በትከሻቸው ላይ አሰቀመጡት። ፍሬዋን ቀመሱ! ትክክል ነው። ክከዚህ በፊት ገብተው አያውቁም ነበር፡ ካሌብ እና ኢያሱ ግን ተሻግረው ገቡና፡ ማረጋገጫውን ይዘው ተመለሱ። ካሌብና ኢያሱም እንዲህ አሉ፡ “ልንወርሳት እንችላለን!” አያችሁ? ለምን? ምክንያቱማ ካሌብና ኢያሱ ቃሉን ይመለከቱ ስለነበር ነው።

322 እግዚአብሔርም አላቸው፡ “ምድሪቱ የእናንተ ናት። አሞራውያን እና ኤዊያውያን እና ሁሉም ዓይነት -ያውያን የተሞላች ነበረች፡ ግን” እንዲህ አላቸው “እናንተ ናት። እግራችሁ የሚረግጠው ቦታ ሁሉ፡ ለእናንተ እሰጣችኋለሁ።” ትክክል። “ብቻ ቀጥል ተራመድ፡ አየህ፡ የአንተ ነው።”

323 እነርሱ ግን እንዲህ አሉ፡ “ኧረ፡ በፍፁም! እንደዚህ አይነት ሪቫይቫል ሊኖረን አይችልም። ኧረ! ኧረ፡ ኧረ፡ ለምን፡ ለምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ሊቀ ጳጳሱ፡ ወይም ኤጲሰ ቆጶሱ፡ ወይም ቄሱ፡ ወይም አንድ ሰው መጥቶ ሁላችንም ያባርረናል።” ኧሃ! ቀጥል፡ ልክ ነው፡ እንወርሳታለን።

324 ከዚያም፡ እነሆ እነዚህ ሁለቱ ደግሞ መጡና እንዲህ አሉ፡ “እግዚአብሔር ተናግሯልና፡ እነሆ እኛ ከአሸናፊዎች በላይ ነን! እንሂድ እንውረሳት!”

325 አያችሁ፡ እነዚያ አሰመሳይ አማኞች፡ ግን፡ ፍሬዋን እሰከመቅመሰ ድረሰ—ተጉዘው ነበር። “አዎን፡ ትጣፍጣለች። ይሁን እንጂ፡ እነሆ እኛ፡ መውረሰ አንችልም።”

326 አሁን፡ ያ ምንድን ነው? እነሆ ዛሬ አማኝ ይህ ነው። አሁን፡ **ይህን** ሰው ተመልከቱት። እግዚአብሔር ጥሪ ሰጠው። ኧሃ-ሃህ። መልካም፡ እነሆ ድኗል። እናቱ ልብሰ አጥባ፡ ሰባኪ እንዲሆንላት ሰትል ኮሌጅ ውሰጥ ትምህርት እንዲማርላት አሰገብታዋለች። እና፡ እነሆ ይወጣና፡ አሁንም በአሳቡ... ሴሰኛ ልብሰ የለበሱ ሴቶች ባየ ቁጥር፡ ሰሜቱ... ይነካካዋል፤ የሚጤሰ ሲጋራ በሸተተው—ቁጥር፡ ከማጨሰ አይቆጠብም። ሰህተት እንደሆነ ያውቃል። መታዘዝ ግን አይፈልግም። እና “ጌታ ሆይ፡ ቀድሰኝ፡ ይህ ነገር ከእኔ አሰወግድልኝ፡” ይላል።

327 እግዚአብሔርም “መልካም፡ ልጄ ሆይ፡ አሰወግድልሃለሁ፡ አንተም ከአንተ ዘንድ አርቀው፡” ይለዋል።

328 አንድ ቀን ሌሊት ወደ አንድ ቦታ ለአገልግሎት ወጣ፡ ስለ መንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ይሰማል፡ ይላልም፡ “በል!”

329 የመጀመሪያውን እርከን ይነሣል፡ ጽድቅ፤ ሁለተኛውን እርከን ይነሣል፡ ቅድስና፤ አሁን ለጥምቀት ዝግጁ ነው። አያችሁ፤ አንድ፡ ሁለት፡ ሦስት። ለጥምቀት ዝግጁ ነው። በዚያም በደረሰ ጊዜ፡ እነሆ መጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ሲያነብ፡ እንዲህ ይላል፡ “አዎን ይህ እውነተኛ ነው ያደረጉትም ይህ ነው። አዎን፡ ትክክል ነው። ጥምቀት በኢየሱስ ስም፡ ያንን ነበር ያደረጉት። ትክክል ነው። ‘ይህን ሁሉ አነብቤዋለሁ’ ይላል፡ መጽሀፍ ቅዱስ በሙሉ አነብቤ ሁሉም አግኝቼዋለሁ።”

“ቢሾፕ፡ ምን ይመስልሃል... ”

“ሁልም ከንቱ ነገር ነው!”

“ኦህ፡ ገባኝ።”

330 “መንፈስ ቅዱስን ተሞሉ፡ በልሳኖች ተናገሩ፡ እነዚህን አደረጉ፡ ድውያንን ፈወሱ። ኦህ፡ አዎን፡ ያ ሁሉ ልክ ነው።” አያችሁ፡ አማትሮ ያያል፡ የምድሪቱን ድንበር ማዶ ይመለከታል።

331 “ኦህ፡ ያንን በቤተክርስቲያኔ ካስተማርኩ... ኦህ! እኔ ፕሪስባይቴሪያን ነኝ፡ እኔ ሜቶዲስት ነኝ፡ እኔ ባፕቲ-... ታውቃላችሁ። ኦህ፡ ቢሾፕ ያሰባርረኛል። ስለዝህ፡ ያንን ማድረግ አንችልም። በቤተክርስቲያናችን ውስጥ እንደዚህ ያለ ስብሰባ ማድረግ አንችልም፡ ሁሉም ተነስተው ይወጣሉ።”

332 “አንድ ጊዜ የበራለት፡ ከሰማያዊው ስጦታዎች ተካፋይ የነበረው፡ ከተጓዘው ጉዞ ቢመለስ፡ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሠርቷልና ወደ ንስሐ ራሱን ለማደስ ለመመለስ... ” ምንድነው—ኃጢአት ምንድን ነው? አለማመን! በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ሠርቷል። እና ምን አደረገ? የተቀደሰበትን ቃል ኪዳን፡ እንደምን ቆጠረ፡ እንደ እርኩስ ነገር፡ እዚህ ደርሰ ባደረሰው እና ባወጣው በጸጋው ስራ ላይ አመጸ። የሚያስፈራ የእሳቱን ፍርድ፡ እና ጠላትን ሊበላ ያለው መዓት መጠበቅ ነው እንጂ ከእንግዲህ ለሱ የሚሆን ሌላ መሥዋዕት አይቀርለትም። “በቀል የእኔ ነውና፡” ይላል ጌታ።

333 “የእግዚአብሔር ቃል የተሳለ ነውና፡ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ ኃያል ነው፡ አጥንትም እስኪሰነጠቅ ድረስ ይወጋል፡ የልብን እና የአዕምሮ ሀሳቦችን ያውቃል።” ይኸው፡ ይኸው። ብርሃኑን ስታዩት፡ በዚያ ተጓዙ! ተራመዱ! ወዴት እንደምትሄዱ አታውቁም፡ መመላለሳችሁ ግን ቀጥሉ። ቀራንዮን በአንክሮ እየተመለከታችሁ፡ በቀራንዮ ፊት ተመላለሱ። ተመላለሱ! ተመላለሱ!

334 አምላክ ሆይ፡ አንድ ቀን እንዲህ ይሁን... ቤተክርስቲያን፡ የሄኖክ ጥላው ነች። እነሆ እርሱ አምስት መቶ ዓመታት በእግዚአብሔር ፊት ተመላለሰ። ተመላለሰ! “እግዚአብሔር የተናገረውን ሁሉ፡ አደረገ፡” የሚል ምስክርነት ይዞ በብርሃን ተመላለሰ። እርሱን አላሳዘነም። ጌታ አድርግ ያለው ሁሉ፡ ሄኖክ አደረገ። ስለዚህ፡ እርሱ ጥላ እንደነበረ፡ አስታውሱ። መርከቢቱ የተሸከመቻቸው አንድ መቶ አርባ-አራት ሺህ፡ የአይሁድ ምሳሌ ነች፡ እነሱም ኖህ እና ቡድኑ ነበሩ፡ ሄኖክ ግን ከጥፋት ውሃ ትንሽ ቀደም ብሎ ወደ ቤት ተወሰዷል። ይህን ታውቃላችሁ። ሄኖክም በብርሃን መሄዱን ቀጠለ።

ታዲያ አንድ ቀን እግሩ ከመሬት ላይ ሲነሳፈፍ ተሰማው፡ ዝም ብሎ መሄዱን ተመላለሰና፡ እነሆ ሳይሞት ወደ ክብር ገባ። ትክክል ነው። በብርሃን ስለ ተመላለሰ እግዚአብሔር ወሰደው፡ "በእግዚአብሔር ብርሃን ተመላለሰ" ከሚል ምስክር ጋር። እነሆ ተመላለሰ፡ ተመላለሰ።

335 ቤተክርስቲያን ሆይ፡ የእግር ጫማችንን እንልበስ፤

በሚያምረው ብርሃን፡ ብብርሃኑ እንመላለስ፡
ብሩህ የምሕረት ጠል ወደኛ የሚያፈስስ፡
በቀንም በሌሊትም በዙሪያችን ያበራል፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን።

አሁን እንዘምር፤

በሚያምረው ብርሃን፡ ብብርሃኑ እንመላለሳለን፡
ኦህ፡ ብሩህ የምሕረት ጠል ወደኛ የሚያፈስስ፡
በቀንም በሌሊትም በዙሪያችን ያበራል፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን።

እናንተ የብርሃን ቅዱሳን እንዲህ በሉ፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን፡
ያን ጊዜ የሰማይ ቃጭሎች ድምጽ ያሰማሉ፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን።

በሚያምረው ብርሃን፡ በብርሃኑ እንመላለሳለን፡
ኦህ፡ ብሩህ የምሕረት ጠል ወደኛ የሚያፈስስ፡
በቀንም በሌሊትም በዙሪያችን ያበራል፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን።

336 አንገታችንን ዝቅ እናድርግ፡ እና በቃ—እንደው ለአፍታ ብቻ። እዚህ ውስጥ አንዳንዶች በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ልምድ እንዲኖራቸው የምትፈልጉ ካላችሁ፡ እንዲህ በሉ፡ "ወንድም ብራንሃም፡ አሰበኝ። ቤተ ክርስቲያን ሆይ፡ አሰቡኝ። በብርሃን መመላለስ እፈልጋለሁ። በውስጤ መራራ ስር ሳይኖር፡ ያንን መልካምነት እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ፡ የእግዚአብሔር ባሪያ መሆን እፈልጋለሁ።" እጃችሁን አውጡና፦ "አቤቱ፡ ጌታ ሆይ አሰበኝ፡" በሉት። አዎን፡ ሃያ ወይም ከዚያ በላይ እጆች፡ ተነስተዋል።

337 አሁን ዝማሬውን ለሰለስ አርገን እየዘመርን ሳለን ጭንቅላቶቻችሁን ዝቅ አድርጉ፦

ኦ፡ ኢየሱስ፡ የአለም ብርሃን።

በሚያምረው ብርሃን፡ ብብርሃኑ እንመላለሳለን፡
ብሩህ የምሕረት ጠል ወደኛ የሚያፈስስ፡
በቀንም በሌሊትም በዙሪያችን ያበራል፡
ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን።

ኑ፡ እናንተ የብርሃን ቅዱሳን፡ እንዲህ በሉ፡
ኦ፡ ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን፡
ያን ጊዜ የሰማይ ቃጭሎች ድምጽ ያሰማሉ፡
ኦ፡ ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን።

ኦህ፡ በሚያምረው ብርሃን፡ ብብርሃኑ እንመላለሳለን፡
ብሩህ የምሕረት ጠል ወደኛ የሚያፈሰስ፡
በቀንም በሌሊትም በዙሪያችን ያበራል፡
ኦ ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን።

338 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ይህን መዝሙር ሲያዜሙ፡ በወንጌል ብርሃን መመላለስ ሲፈልጉ ሳሉ፡ ጌታ ሆይ፡ እነዚያን ውድ ልቦች ተቀበላቸው። ያንተው ናቸው፡ ቀድሳቸው፡ ክፋት ሁሉ፡ አለማመንን ሁሉ አሰወግድ፡ የአለም ብርሃን ኢየሱስ ይግባ። ጌታ ሆይ፡ ለታመሙ እና ለተጎዱ፡ እነሆ መሀረቦች እዚህ ተቀምጧል። ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ወደ እነዚህም ና፡ በብርሃን እንዲሄዱ ፈውሳቸው። ይሁን፡ ጌታ ሆይ።

339 ስለ ትምህርታችን፡ ስለ መንፈስ ቅዱስ መገኘት፡ ቁጭ ባልንበት ከእኛ ጋር ስለነበረ እና ብዙ ሰዓታት፡ ስላቆየን፡ እናመሰግንሃለን። ሰዎች ሲጠባበቁህ በዚህ ሞቃት ክፍል ውስጥ ተቀምጠዋል። ጌታ ሆይ፡ አንተን በመጠባበቅ በመፈለግ፡ ተቅበዝብዘዋል። ቃሉ ሲነበብ ሲሰሙ፡ በመጨረሻው ሰዓት ላይ፡ መድረሳችን ተገንዝበዋልና። ከዓለም መናወጥ በቀር፡ የቀረ ነገር የለምና። በእነዚህ ቀናት ውስጥ አንድ ቀን እነሆ ማሰመሰል ሁሉ ይቀራል።

340 እኔም አምላክ ሆይ፡ እነሆ እጸልያለሁ፡ በመለኮታዊው መገኘትህ ፊት ያለውን ሰው ሁሉ አድን፡ በመንፈስህ አድናቸው። መንፈስ ቅዱስም በእያንዳንዳቸው ላይ ይውረድ እና ልባቸውንም በመልካም እና በሰላም ይሙላ፡ ይህም የመንፈስን ፍሬ፡ እርሱም ትዕግሥት፡ በጎነት፡ ሰላም፡ በመንፈስ ቅዱስ፡ ትዕግስት፡ የዋህነት፡ እምነት ያፈሩ ዘንድ ነው። ይሁን፡ ጌታ ሆይ። አሁንም አንተ እንድትገለገልባቸው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ልጅህ ስም፡ ለአንተ አደራ እሰጣቸዋለሁ። ኣሜን።

በብርሃን ውስጥ እንመላለሳለን...

እጃችንን አንስተን እንዘምረው።

... በሚያምረው ብርሃን፡
ብሩህ የምሕረት ጠል ወደኛ የሚያፈሰስ፡
በቀንም በሌሊትም በዙሪያችን ያበራል፡
ኦ፡ ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን።

እወደዋለሁ፡ እወደዋለሁ
ቀድሞ ስለወደደኝ
መዳኔንም ገዛሁ
በቀራንዮ ዛፍ ላይ።

341 አቤት፡ ድንቅ ነው አይደል? አሁን ለአሰር ደቂቃ ያህል፡ ወይም አሰራ አምሰት፡ ምንም ያህል ይሁን የጥምቀት ሰነ ሰርዓት ይኖረናል። እዚያ... እዚህ የምትጠመቅ አንዲት ወጣት ሴት ያለች ይመሰለኛል። ልክ ነው? [ወንድም ኔቪል “በርካታ ናቸው፡” አለ—አርታዒ።] በጣም ጥሩ፡ ማታ ላይ በምናደርገው የጥምቀት ሰነ ሰርዓት የማትገኙ ዛሬ ጠዋት ለመጠመቅ የተዘጋጃችሁ ሰንቶች አላችሁ? ዛሬ ከሰአት በኋላ መምጣት የማይችሉ አንድ፡ ሁለት፡ ሶስት፡ ሶስት ናቸው ወይም ከምሽቱ አገልግሎት በፊት በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ለመጠመቅ የወሰኑ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡ ልጆቼ።

እግዚአብሔር በፊታችሁ የተከፈተውን በር ስላዘጋጀ ደስ ብሎኛል። ታዲያ አሁን ለመግባት ዝግጁ ናችሁ፡ አሮጌው ነገሮች ሁሉ ሞተው ወደሚቀበሩበት፡ ወደ መቃብር ውስጥ ትገባላችሁ። አሁን፡ አስታውሱ፡ ጥምቀታችሁ **እዚህ** በውስጣችሁ አንድ ነገር እንደተፈጸመ የሚያሳይ ውጫዊ መግለጫ ብቻ ነው።

በብርሃን ውስጥ እንመላለሳለን፡ (ዝግጁ ናችሁ? )
በሚያምረው ብርሃን፡ (... ? ... )
ኦ፡ በቀንም በሌሊትም በዙሪያችን ያበራል፡
ኦ፡ ኢየሱስ፡ የዓለም ብርሃን።

342 አቤት፡ ድንቅ ታላቅ ህብረት! ጥሩ ስሜት አልተሰማችሁምን? ኦህ፡ በጣም ጥሩ ስሜት ይሰማኛል። እኔ በሆነ ነገር ውስጥ እንደቆየሁ ይሰማኛልና፡ እነዚህን የድሮ-ማሻ የገላ ብሩሽ ይዛችሁ፡ በላዬ ሳሙና የፈገፈጋችሁኝ ያህል ተሰምቶኛል።

343 ወንድሜ ምናልባት ዛሬ ጠዋት ልትጠመቁ የምትፈልጉ ሁሉ፡ ተዘጋጁ እያለ ነው። ልብስ እና ነገሮቻችሁ ዛሬ ማታ እርጥብ ይሆናሉ፡ ካስባችሁበት ግን ይሁን ግድ የለም። ዛሬ ጠዋት ለመጠመቅ ዝግጁ ከሆናችሁ ግን፡ መልካም ነው።

344 ይህንን ከዚህ ማንሣት እንዳለብን አምናለሁ፡ አይደል፡ ወንድም ኔቪል? እሺ፡ ወዳጄ። አሁን፡ ጥምቀቱን ለማየት መቆየት የምትፈልጉ ሰንቶች ናችሁ? እሺ ጥቂት ደቂቃዎችን ውሰዱ፡ እንደው፡ ምናልባት ከዚህ በፊት አይታችሁ የማታውቁ ትሆናላችሁ። መቆየት ካልቻላችሁ ግን፡ እንግዲህ፡ ወደ ማታ እንደምትመለሱ እርግጠኞች ሁኑ። እኔ ግን የጥምቀትን አገልግሎት ለመመልከት ጥቂት ደቂቃዎችን መቆየት በቻላችሁ፡ ብዬ እመኛለሁ። ይህንን እናንቀሳቅሰዋለን እና እያንዳንዱ ሰው ወደ ውስጥ መግባቱን የሚያሳይ አንድ ትልቅ መስታወት ከኋላው አለ። እርግጠኛ ነኝ፡ ያስደንቃችኋል። በጥምቀት ከጌታ ጋር እንቀበራለን። አሜን። እርሱ እንደ ሞተ፡ በሞቱ እንቀበራለን፡ በትንሳኤውም ደግሞ እንነሳለን፡ በአዲስ ሕይወት ለመመላለስ። ጌታ ይባርካችሁ።

345 የዛሬ ማታ ትምህርቱ ምን እንደሚሆን ሰንቶች ታውቃላችሁ? ሎዶቅያ፡ የቤተክርስቲያኑ ዘመናት መጨረሻ፡ እና መግቢደጃ ነው።

346 መልካም፡ የጥምቀቱን ስነ ስርዓት እናከናውናለን። ቴዲ፡ እባክህ ከቻልክ...

347 መጠመቅ ትፈልጋለህ-... ? [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]... ለካ ተጠምቀሃል። አንዳንዶቹ አሁን ወደ ቺካጎ የሚሄዱ አሉ፡ አያችሁ።

እንጸልይ፦

348 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ዛሬ ቁጭ ብለው እስከ ጉባኤው ፍጻሜ ድረስ አዳምጠዋል። ጌታ ሆይ፡ አሁን ወደ ቺካጎ ሲሄዱ፡ ለአንተ አደራ ሰጠናቸው። ጌታ ሆይ፡ ከእነርሱ ጋር ሂድ፡ እና እያንዳንዱም ይህን አስደናቂ ብርሃን ወሰዶ፡ ጌታ ሆይ፡ በቺካጎ ከተማ ይዝራው፡ እንዲሁም በሄዱበት ስፍራ ሁሉ። አብረሃቸው ሁን። እስክንገናኝ ድረስ፡ መንፈሳቸው በአንተ ዘንድ ይጽና። በኢየሱስ ስም። ኣሜን።

349 [ወንድም ኔቪል ትንቢት ተናገረ፦ “አዎን፡ ለአንተ፡ ለህዝቤ፡ ዛሬ ጠዋትም እንደገና፡ አዎን ለአንተም ለባሪያዬ እልሃለሁ፦ ባስተላለፍከው ቃሌ እነሆ ተቀብዬሃለሁ። እከተልሃለሁ በሰውር እናገርሃለሁ፡ አዎን፡ የጉዞህንም አሳይሃለሁ። አዎን፡ እነሆ ከአንተ ጋር እሆናለሁ እባርክሃለሁ።]

350 [“አዎን፡ ሕዝቤ ሆይ፡ ዛሬ ጠዋት እልሃለሁ፡ እኔ ሁሉን ቻይ አምላክ ነኝ። ዛሬ ጠዋት፡ ወደ አንተ ለመምጣት፡ እነሆ ይህንን ዕቃ ተጠቀምኩ። ከመንፈሴ ፈቀቅ አትበል፡ የሚናገርህንም ድምፅ አትተው እልሃለሁ። ከእኔ ጋር እንደሆንክ እነሆ እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ። ከመንገድህ ተመልሰህ ከሀሳብህ ተመለስ እኔም ከአንተ ጋር ነኝና እመነኝ። ወደ እኔ ብትመጣና በጥምቀት ብትከተለኝ፡ እነሆ እባርክሃለሁ እጠብቅሃለሁ፡ በፍጻሜው ሙላት እመጣሃለሁ። አዎን፡ እነሆ ተናግሬአለሁና፡ አልፈጽመውምን? አዎን፡ ይላል ጌታ።”—አርታዒ።]

እጆቻችንን አንስተን እንዲህ እንበል። “ተመስገን፡ ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ስምህ ይመስገን።” ተመስገን፡ ጌታ ሆይ።

351 ጌታ ሆይ፡ አንተ እንደሆንክ፡ እናምናለን... አንድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ቀን መንፈስ በአንድ ሰው ላይ ወረደ፡ እና ሊሆን ያለውን፡ የእግዚአብሔርን ምስጢር ሁሉ ነገረ። አባት ሆይ፡ አንተ አሁንም ያው አምላክ እንደሆንክ እናውቃለን። አሁንም፡ በዚህ ጥዋት፡ በዚህ ትሁት ፓስተር ላይ፡ እነሆ ወርደሃል፡ እርሱም ያኔ በኒቆላውያን መንደር ነበረ፡ አንተ ግን ዳሰስከውና፡ እነሆ ብርሃንህም አይቶ ወጣ። እነሆ አሁንም ልቡ የተከፈተ ነው አንተ እስክትናገርበት ድረስ፡ ምን እንደሚናገር እስከማያውቅ ድረስ፡ ተነስቶ መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ዘንድ እንዲሰራ የትንቢት ድምጽ ወደ እኛ እንዲያመጣ ቆሟል። ተመስገን፡ አባቴ። እነሆ እኔ—እኔም ጉዞዬን እንድታሳየኝ እጠብቅሃለሁ። አሜን።

352 [አንዲት እህት በልሳን ተናገረች። በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ። ሌላዋ እህት ተረጎመች—አርታዒ።] አሜን። ሰምታችሁታል፡ አይደል? ያ ምን እንደሆነ ተገንዝባችኋል? የዚያን ሴት ድምጽ ስትነገረው ሰሟት፡ እና ትርጉሙም በተመሳሳይ ድምጽ ሲመለስ ተመልከቱ። አያችሁ? እነሆ ሁለቱ ሴቶች የተለያዩ ናቸው፡ እረ እንደው መተዋወቃቸው እና አለመተዋወቃቸው እጠራጠራለሁ። ሁለቱም አይ—አይተዋወቁም። እነሆ መንፈስ ቅዱስ፡ እንዲህ ያለውን ድምጽ የሚያውቅ ነው። እዚህ በሰዎች መካከል ያለው ክርስቶስ መሆኑን አስተውላችኋልን? ትክክል ነው።

353 ወንድም ፓት፡ ማንበብ የምትፈልገው ነገር አለህ? ቀጥል፡ አያችሁ። [ወንድም ፓትም አለ፡ “የዮሐንስ ራእይ 22፡16 በጌታ በኢየሱስ ስም እነበዋለሁ፦ እኔ ኢየሱስ በአብያተ ክርስቲያናት ዘንድ ይህን እንዲመሰክርላችሁ መልአኬን ላክሁ።”—አርታዒ።] አሜን።

354 እንግዲህ፡ መንፈሳዊ፡ መለኮታዊ ምሪት ነው። አያችሁ፡ መንፈስ ቅዱስ በምእመናን መካከል ሲመላለስ፡ እየተናገረ፡ ሲንቀሳቀስ። ኦህ፡ አይደንቅም ወይ? ወዳጆች ሆይ፡ መጽሀፍ ቅዱስ የተናገራቸውን ያው ነገሮች፡ ማሰቡ ራሱ። እነሆ ዛሬ እየነው፡ ከእንግዲህ አንቅበዘበዝም። እነሆ፡ የተወደዳቹ ወገኖቼ ሆይ፡ ኑና ተቀበሉት። ኑ፡ ተቀበሉት።

355 ቴዲ፡ ለጥምቀት ስንዘጋጅ ሳለን፡ (እግዚአብሔርም ልባችሁን እንዲያዘጋጅ እጸልያለሁ) **ወደሚመራኝ ሁሉ እከተላለሁ።**

356 ወንድሞቼ ሆይ እዚህ ላይ ላግዛችሁን? እሺ፥ እንግዲህ—ማይኮቹን ማቋረጥ አለባችሁ። ኧሃ-ሃም። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]

357 እነሆ መጥታችሁ እንድትጠመቁ በህያው አምላክ እና በቃሉ ምክር አምላችኋለሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አስታውሱ መጽሐፍ ቅዱስ ያንን እንድናደርግ ስለሚያስገድደን ነው የተናገርኳችሁ። እንዲሁ—ጳውሎስም ደግሞ እንድናደርግ ተናግሯል፡ ከዚህ የተለየ መልአክም ቢሆን ሌላ ነገር ቢያስተምር፡ የተረገመ ይሁን። እኔም—ልክ እሱ እንዳደረገው በመንገዴ መጨረሻ ላይ ይህንን ማወጅ እፈልጋለሁ፦ የእግዚአብሔርን ምክር ሁሉ ለእናንተ ከመናገር አይታክተኝም፡ በትክክል። የማንም ደም በእኛ ላይ የለም።

358 ኦህ፡ አትወዱትምን? እሺ፡ የማሰናበቻ መዝሙራችን ቆመን እንዘምረዋለን። እሺ፡ እስከዚያ ድረስ እንዲህ ይሁን፦

የኢየሱስ ስም ከአንተ ጋር ይሁን፡
የሀዘንና የዋይታ ልጅ።
ደስታ እና ምቾት ይሆንሃል፡
በሄድክበት አብሮህ ይሁን።

ድንቅ ስም፡ (ውብ ስም!) ኦ የሚደንቅ! (ኦ የሚደንቅ!)
የምድር ተስፋ የሰማይ ደስታ።
ድንቅ ስም፡ (ውብ ስም!) ኦ የሚደንቅ! (ኦ የሚደንቅ!)
የምድር ተስፋ... ደስታ

አሁን አንገታችንን ደፍተን እንዘምራለን፦

ለኢየሱስ ስም ስገዱ፡
በእግሩ ስር ውደቁ፡
የነገሥታት ንጉሥ አክሊል ያጠልቃል፡
ሩጫችን ሲጠናቀቅ።

60-1211M አሰሩ ደናግል፡ እና መቶ አርባ-አራት ሺዎቹ አይሁዶች
ብራንሃም ተበርናክል
ጀፈርሰንቪል, ኢንዲያና ዩ.ኤሰ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

VOICE OF GOD RECORDINGS
P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰብያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው®።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org